## ቅደም-ተከተላዊ

# የክርስቶስ ሕይወት

## ቅጽ 2

## ከገሊላ እስከ ክብር

በማርክ ኢ. ሙር

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት
የኤስ ኣይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል


የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው
Copyright © 1997
College Press Publishing Company
Second Printing 1998
Fourth Printing (Revised Edition) 2005
Moore Mark E. (Mark Edward) 1963-
The Chronological Life of Christ/Mark E. Moore
Includes text from: The NIV Harmony of the Gospels/Robert L. Thomas, editor and Stanley N. Gundry, Associate Editor
Contents: V.2 from Galilee to Glory

ደራሲ ፡ ማርክ ኢ. መር
ትርጉም ፡ ተስፋዬ መስፍን፣ደርበው አዱኛ፣ሚናስ ብሩክ
አርታኢ ፡ ገበየሁ አየለ
የኮምፒውተር ጽሑፍ ፡ ፍቅርተ ፀጋዬ

አሳታሚና አከፋፋይ ፡-
ኤስ.አይ.ኤም ኢትዮጵያ
የመ.ሣ.ቁ. 127
አዲስ አበባ
የመጀመሪያ እትም ፡ 2001 ዓ.ም




# በኅዳግ ላይ የቀረቡ ምልክቶች መፍቻ


ምሳሌዎች


ጸሎት (ዓበይት ትምህርቶችና ምሳሌዎች የቀረቡበት)


የተፈጸሙ ትንቢቶች


የክርስቶስ መለኮትነት (ራሱ ያረጋገጠበትና ሌሎችም የመሰከሩለት)


የነገረ-ፍጻሜ ትምህርቶች


ፈውሶችና ሌሎች ታምራቶች


የእግዚአብሔር መንግሥት/ቤተ ክርስቲያን

## ማውጫ

ምድብ ስምንት፡ ኂለኞቹ የክርስቶስ አገልግሎቶች (የቀጠለ)......8

ምድብ ዘጠኝ፡ ኂለኛው የዮርዳኖስ ማዶ አገልግሎት ...............79

ምድብ አሥር፡ የመጨረሻው ሳምንት ...................................245

ምድብ አሥራ አንድ፡ ለክርስቶስ ሞት የተደረገ ዝግጅት ..........332

ምድብ አሥራ ሁለት፡ የክርስቶስ ሞት ...............................483

ምድብ አሥራ ሦስት፡ የኢየሱስ ትንሣኤና ዕርገት ..................581



## መግቢያ

እ.ኤ.አ. ሚያዝያ 1996 ዓ.ም. ታሪክ ሠራ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ ታይም፣ ኒውስዊክና ዩናይትድ እስቴትስ ኒውስ እንዲሁም ወርልድ ሪፖርት የተባሉት መጽሔቶች ሁሉም አንድ ዐይነት የዜና ዘገባ አቀረቡ፤ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ:: እነዚህ ታሪኮች ሌላው ቢቀር ስለዚህ ሰው፣ በእያንዳንዱ ሰው የዕለት ተዕለት ንግግር ውስጥ የሚብላሉ ስሑት ሐሳቦችና ከፊል እውነቶች መኖራቸውን ያሳያሉ:: ይሄው ነው . . . ኢየሱስ በፓለስቲና ምድር ከተመላለሰ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ብዙ የተለወጠ ነገር የለም:: በጸጉር ቤቶችና በቍርስ ቤቶች ውስጥ ርእሰ ጉዳይ የሚሆነው አሁንም እርሱ ነው:: ስለ እርሱ ይወራል፤ እርሱን በመቃወምም ሐሳብ ይቀርባል:: ጉጉታችንን ይማርካል:: ምናባችንን ያቀጣጥላል:: ብዙ ጊዜም ቅሬታችንን ያስተናግዳል::

በእርግጥ እርሱ ማን ነው? የፖለቲካ ሰው አለመሆኑ ይታወቃል:: ዛሬም ቢሆን ሕፃናትን ይባርካል፤ ሕዝቦችንም ይለውጣል:: የአንድ እንቅስቃሴ አነሣሽ አይደለም፤ ነገር ግን ስንት ሐኪም ቤቶች፣ ስንት እጓለ ሙታን ድርጅቶች፣ ምን ያህል ጉልቍ መሳፍርት የሌለው ቸርነትም እንዳለ የሚያውቅ ሰው ነው:: አዝናኝ ባለሙያ አይደለም:: ግን ዕለታዊ ሕይወቱ በሰዎች የተጨናነቀበት እንደ እርሱ ማን ነው? የአእምሮ ሐኪም ይሆን? ከቶ አይደለም:: ነገር ግን ግራ ተጋብተን የነበርነውን ስንቶቻችንን ነው መልሶ ሰው ያደረገን? ይህ አናጺ-ገበሬ ምድራዊ ጠላቶቹ ሊያስቡት ከሚቻላቸው በላይ የሆነውን መንግሥት ራሱ መሥርቷል::

*በእውነት* እርሱ ማን ነው? ገለል ባሉ ቦታዎች በሽሉክታ የሚወራውን ብታደምጥ «ታሪካዊውን ኢየሱስ መፈለግ» ስለሚለው ሐረግ ሊቃውንት ሲወያዩ ትሰማለህ:: ውጤቱም ከወንጌሎቹ ውስጥ ታምራዊና «ተረታ ተረት ነው» የሚሉትን አስወግደው፣ ጸሐፊው

በትክክል ያለውን መስመር በመስመር ለማንበብ መሞከር ነው። በብዙዎቹ ጽሑፎቻቸው ውስጥ ኢየሱስ ተጠራጣሪ ፈላስፋ፣ ቀናተኛ ዐማፂ፣ ወይም አስቸጋሪ፣ ቀስስተኛ፣ ጮሌ፣ ጉረቤትን ወደ በጎ የሚመራ መልካም አድራጊ ሆኖ ይታያል።

እንግዲህ የምሥራቹና ለዚህ መጽሐፍ መነሻ የሆነው ሐሳብ የሚከተለው ነው፡- ከዚህ ቀደም እንዳየናቸው ሁሉ ወንጌሎቹ ታሪካዊ ኢየሱስን ያቀርባሉ። ምንጮችን ለመፈለግ አዩኝ አላዩኝ ማለት የለብንም። መላምታዊት ቤተ ክርስቲያንን በነገረ ልቦናዊ ስልት መፈለግ አይኖርብንም። የሁለተኛው ምእት ዓመት ዐርታዒ ያደረገውን የአርትዖት ሥራ እንኳን እንደገና መተርጐም የለብንም። በእጅህ የሚገኙት ወንጌሎች ተአምራትና ሌሎችም ሁሉ ስለ ኢየሱስ እውነት የሚናገሩ ናቸው። በእውነት እርሱ ማን ነው? እርሱ ለኀጢአታችን የሞተ፣ እኛን ለማጽደቅም የተነሣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህ መጻፍ የሚገባው ነው።

የጊዜን ቅደም ተከተል ጠብቆ የሚጓዘው ይህ የክርስቶስ የሕይወት ታሪክ ሁለተኛው ቅጽ ክርስቶስ በዚህ ምድር ላይ ካሳለፋቸው የመጨረሻዎቹ ሦስት ወራት በመነሣት ይጓዛል። እንደዚህ በብዛት የተነገረ ታሪክ የለም። ይሁን እንጂ ከቶ አሰልቺና ጊዜው ያለፈበት አይደለም። ድግግሞሽን በሚገባ ዐዝሎ ይገኛል፤ ባየኸው ቍጥር ለእይታ እንደ ቀረበ አብረቅራቂ ትእይንት እያብረቀረቀ ያስደንቅሃል። ስለዚህ ይህ ታሪክ መልእክቱን አሁንም ያስተላልፋል። አሁንም ተወዳጅና ኗሪ በመሆን በጊዜ ሂደት ውስጥ በአቧራማ ጐዳናዎች እና በወይራ ጥሻዎች ውስጥ ያስጉዘናል፤ አንዳንድ ጊዜም እስከ መንግሥተ ሰማያት መዳረሻ ያዘልቀናል። ይህ መጽሐፍ ይህን ታሪክ ዳግም እንድትሰማ፣ ምናልባትም ለመጀመሪያ ጊዜ እንድትሰማ እንዲያደርግህ ጸሎቴ ነው።



እንደ ቅጽ 1 ይህም ቶማስና ጉንድርዩ የተባሉት ሰዎች ለኤን አይ ቪ (New International Version) ስምምነት ጽሑፍ ጋር አብሮ ተጓዳኝ ነው። ***የወንጌላት ስምምነት*** የሚለው ጽሑፍ የወንጌሎችን ጽሑፍ በአራት ዐምዶች አሳትሞአል፤ እኛ ግን በአንድ ላይ ጨምቀን ነው ያሳተምነው። የአራቱ ወንጌሎች ጽሑፎች አንድ ወጥ ታሪክ ሆነው ይነበቡ ዘንድ ልዩ በሆነ መልክ ተጣምረው ታትመዋል። ማቴዎስን፣ ማርቆስን ሉቃስን፣ ዮሐንስን (ዐልፎ ዐልፎ) እንደዚሁም የሐዋርያት ሥራን ለመተካት ማቴ፣ ማር፣ ሉቃ፣ ዮሐ፣ ሐሥ የሚለውን ዲበ ጽሑፍ አኅጽሮት በመጠቀም አንባቢ የትኛው ወንጌላዊ ምን እንዳለ በቅጽበት ለመለየት ይችላል። ይህ አቀራረብ አራቱን ወንጌሎች በአንድ ጊዜ እንድታነብ ያስችልሃል። የእያንዳንዳቸውን ምስክርነት በማነጻጸርና በማቀናጀት ሙሉና አሸብራቂ በሆነ ዝርዝር ትዕይንቱን ዳግም ለመቅረጽ እንችላለን። ጠለቅ ያለ ታሪክን እውን ለማድረግ ይቻል ዘንድ ከልዩ ልዩ ትረካዎች ከፊል ሐሳቦችን በማጣመር፣ ፍሰቱ ተፈጥሮኣዊ የሆነና ሰዋሰዋዊ ሽግግርም ያለው ዐረፍተ ነገር እንዲሆን ቃላትን መጨመር፣ መለወጥ ወይም ሥርዐተ ነጥብን መቀየር አስፈላጊ ነበር። ቃሉ፣ ሥርዐተ ነጥቡ፣ አንድን ፊደል አጉልቶ በማሳየት ረገድም (Capitilization) ከመጀመሪያው ጽሑፍ ማለትም ከኤን አይ ቪ ጋር አንድ ዐይነት ካልሆነ፣ በቅንፍ ውስጥ ([...]) በማስቀመጥ ያደረግነውን ለውጥ አሳይተናል።

ከእርሱ የተነሣ፣
ማርክ ኢ. ሙር

# ምድብ ስምንት (የቀጠለ)
# ኋለኞቹ የክርስቶስ አገልግሎቶች በይሁዳ

**§ 104**
**ኢየሱስ ወደ ማርያምና ማርታ ቤት መሄዱ**
**(ሉቃ 10፥38-42)**

ማንም መጥፎና መልካሙን በትክክል ለይቶ ለመምረጥ ይችላል:: ትልቁ ፈተና የላቀውን ከተሻለው መምረጡ ላይ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ማርታ፣ አለ የተባለች የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞቻችን መስታወት ናት:: ቀዳሚ ጉዳዮችን ትታ በምልካም ሥራ ላይ የተጠመደች ሴት ናት:: ታሪኩ ቀላል፣ ትምህርቱ ግን ጥልቅ ነው::

**(ሉቃ 10፥38-40)**

38ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ መንገድ ሲሄዱ፣
ኢየሱስ ወደ አንድ መንደር ገባ፤ ማርታ የተባለች
አንዲት ሴትም በቤቷ ተቀበለችው:: 39እርሷም ማርያም
የተባለች
እኅት ነበረቻት፤ ማርያምም ቃሉን እየሰማች በጌታ እግር ሥር ተቀምጣ ነበር::
40ማርታ ግን በሥራ ብዛት ትባክን ነበርና ወደ እርሱ ቀርባ፣ «ጌታ ሆይ፤ እኅቴ
ሥራውን ለእኔ ብቻ ጥላ ስትቀመጥ ዝም ትላለህን? እንድታግዘኝ ንገራት እንጂ»
አለችው::

የታሪኩ ዳራ የቢታንያ መንደር ነው:: ከደብረ ዘይት ተራራ ጎን በምሥራቅ ኢየሩሳሌም በኩል ከሦስት ኪሎ ሜትር ባነሰ እርቀት ይገኛል:: አልዓዛር እኅቶች፣ ማርያምና ማርታ ቤት ኢየሱስ የነበረ ስለ መሆኑ ሲወሳ ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው:: እርሱን ሲያገኙት ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ አለመሆኑ ግን የታወቀ ነው:: የኢየሱስ ቅርብ ወዳጆች ናቸው (ዮሐ 11፥1-3):: ኢየሱስ ወደ ወዳጆቹ ወደ አልዓዛር፣



ማርያምና ማርታ ቤት በግልጽ ሳይጋበዝ አልቀረም::[1] ላለፈው አንድ ዓመት ተኩል ኢየሱስ በገሊላና በዙሪያዋ ባሉት ስፍራዎች ተዘዋውሮአል:: አሁን ደግሞ ወደ ይሁዳ በመመለሱ ይህን ወዳጅነት ሊያድሰው ይችላል::

አልዓዛር ኢየሱስን በዳስ በዓል ላይ አግኝቶ እንደ ነበርና ይህንኑም ለማርያምና ለማርታ እንደ ነገራቸው እናስባለን:: በበነጋው ኢየሱስ ለራት እንዲመጣ ይነግረው ዘንድ አልዓዛርን መልሰው ወደ ኢየሩሳሌም ላኩት:: ሥራ በጣም በዝቶበት ስለ ነበር በበዓሉ ዕለት ለመምጣት አልቻለም:: በዓሉ ካለፈ በኋላ ግን ከውድ ወዳጆቹ ጋር ምግብ ለመብላት ወደ ቢታንያ መጣ:: አልዓዛር እዚህ ላይ ስላልተጠቀሰ፣ ኢየሱስ ከላካቸው ሰባ ሁለት ደቀ መዛሙርት አንዱ ሳይሆን አይቀርም::

ማርያምና ማርታ ለወዳጃቸውና ዝነኛ ለሆነው መምህር፣ ለኢየሱስ በጋራ[2] ግብዣ አዘጋጅተዋል:: ዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ሲታሰቡ ይህ የእነ ማርያም ሥራ ቀላል አይደለም:: ማርያምና ማርታ ግምት ውስጥ የሚገባ ሀብት ያላቸው መሆኑን የሚያመለክት ትልቅ ቤት አላቸው:: ስምዖን (ለምጻሙ፣ ማቴ 26:6) ምን ዓይነት ሥራ እንደ ነበረውና ሕመሙስ በኑሮው ላይ ምን ሳንካ እንዳስከተለበት አናውቅም:: ለኑሮአቸው የሚሆነውን አያሌውን ገንዘብ ለፍቶ የሚያመጣው አልዓዛር ሊሆን ይችላል:: ይህ ከሆነ ደግሞ ከሁለት ወር በኋላ እርሱን ከሞት ማስነሣቱ በቤተ ሰቡ ላይ ታላቅ ውለታ ጥሏል::

[1] ለምጻሙ ስምዖን (ማቴ 26፥6) የቤተ ሰቡ አራተኛ አባል ሳይሆን አይቀርም፤ ይህ ከሆነ ደግሞ የማርያም ወይም የማርታ ባል ሊሆን ይችላል:: ደግሞም ማቴዎስ 26፥6 በዚህ ፍጹም የተለየ በሆነ ቤት ውስጥ የተከናወነ ሳይሆን አይቀርም፤ ወይም ለምጻሙ ስምዖን የተባለው አልዓዛር ሊሆን ይችላል::

[2] ማርታ «ሥራውን ለእኔ ብቻ ጥላ» (ቁ 40) በማለት ስሜታዊ ሐረግን ተጠቅማለች ይህም ማርያም በመጀመሪያ ታግዛት እንደ ነበር ያመለክታል::

ኢየሱስ እስፍራው ከደረሰ በኋላ፣ ማርያም እኅቷ ብቻዋን ሥራውን ሁሉ እንድታከናውን በማድረግ፣ ኢየሱስ እግር ሥር ተቀምጣ የሚያስተምረውን ትሰማ ጀመር። አግባብ ያልሆነው ነገር እኅቷን ብቻዋን መተዋ ብቻ አልነበረም፤ በባህል ረገድም ተገቢ አይደለም። ማርያም የወንድ የሆነውን፣ ማለትም የደቀ መዝሙርነትን ሚና የራሷ አደረገች (ከሉቃ 8፥1-3 ጋር ያነጻጽሩ)። ማርታ በማእድ ቤቱና በምግብ አዳራሹ ስትመላለስ ሳለ በእኅቷ ላይ ይበልጥ ትበሳጭ ጀመር። በመጨረሻም እንዲህ በማለት ቍጣዋን ለኢየሱስ ገለጸች፤ «ጌታ ሆይ፤ እኅቴ ሥራውን በእኔ ላይ ጥላ ስትቀመጥ ዝም ትላለህ? እንድታግዘኝ ንገራት እንጂ፤» በዚህ ንግግሯ የወቀሰችው እኅቷን ብቻ ሳይሆን ኢየሱስንም ነበር።

ኢየሱስ ምን ማድረግ እንዳለበት በመናገሯ ማርታ ባለጌና ስድ ብትሆንም (ስለ ተናደደች) ጥያቄዋ ተገቢ ነበር። ማርያም ታግዛት ዘንድ ፈለገች [ሲናንቲለምባኖ - Synantilambano] ቃሉ «ድርሻዋን ታናውን ዘንድ» ማለት ነው። ሁለት በሬዎች በአንድ ላይ ተጠምደው ሁለቱም የየራሳቸውን ሸክም በመሸከም የሚያከናውኑትን ሥራ ለመግለጽ የሚያገለግል ቃል ነው። ይህ ነበር አይሁድና ክርስቲያን ቀይጥ የቆየ የሥራ ሥነ ምግባር።

> [41]«'ማርታ፣ ማርታ፤ ስለ ብዙ ነገር ትጨነቂያለሽ፤ ትዋከቢያለሽም፤[42] የሚያስፈልገው ግን አንድ ነገር ብቻ ነው፤ˮ ማርያምም የሚሻለውን ድርሻ መርጣለች፤ ይህም ከእርሷ አይወሰድም።'»
>
> **ሉቃ 10፥41-42**

*ˮ42 አንዳንድ የጥንት ቅጆች «የሚያስፈልገው ግን ጥቂት ብቻ ነው» ይላሉ።*

ኢየሱስ የማርታን ንግግር ባረመ ጊዜ በስፍራው የነበረውን የታፈነ ሣቅ ለመስማት እንችላለን፤ «ማርታ፣ ማርታ፣ ስለ ብዙ ነገር ትጨነቂያለሽ፤ ትዋከቢያለሽም፤» ይህ በጧቱ ዜናችን ዕጥር ምጥን



ብሎ የሚቀርበውን አሳብ አይመስልም? እኛ ጭንቀትና ፍርሀት የሞላብን ሰዎች ነን። እንደ ማርታም ብዙ ጊዜ የምንጨነቀው ስለ ምግብ ነው።

ቍጥር 42ን አስመልክቶ፣ «የሚያስፈልጉት ጥቂት ነገሮች ብቻ ናቸው» የሚሉ አንዳንድ ቅጆች አሉ። ይህ ጽሑፍ ትክክል ከሆነ፣ ኢየሱስ የተናገረው ስለ ራት ዝግጅቱ ነው። መደረግ ስላለበት ነገር ማርታ ብዙ በመጨነቅ ላይ መሆኗን ነበር የሚነግራት። ይህን በተመለከተ በእጃችን ያለው ጽሑፍ ትክክል ይመስላል። ኢየሱስ የሚናገረው ስለ ምግብ ሳይሆን፣ ስለ ትምህርቱ ነው፤ «የሚያስፈልገው ነገር የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው።»[3]

መደምደሚያው ግልጽ ነው። ማርታ ኢየሱስ የሚናገረውን እያዳመጠች እግሩ ሥር የመቀመጥ ከፍተኛ መብት ነበራት፤ ነገር ግን ምግብን አዘጋጅታ ለማቅረብ ተጨንቃለች። ኢየሱስን ሳታገኘው ቀረች። አምስት ወር በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ይሄዳል። እኛም ስለ ጥቃቅን ነገሮች እየተጨነቅንና ከመለኮት የሆነውን ዕድል እያጣን በሕይወት ውስጥ እንንዛለን። ማርያም ግን ሰው ከሆነው አምላክ ትልቅ ጥቅም አግኝታለች።[4] ጆሮዎቿ አሁን ክፍት በመሆናቸው ኅርብ ሰለት ኢየሱስ ከመሰቀሉ በፊት ለቀብሩ ይሆን ዘንድ ልትቀባው እንደሚገባት አርቃ ተመልካች ሆናለች (ከቍ 141 ጋር ያነጻጽሩ)።

---

[3] R.W. Wall ይህ ጉዳይ የኢየሱስን ቃል ከዘዳግም 8፡3 ጋር ያያይዘዋል ይላል። የሉቃስ 10፥25-28:29-37 እና 38 ሦስቱ አጉልቶ ማሳያዎች በቅደም ተከተላቸው ከዘዳግም 5-6:7 እና 8 ጋር የተያያዙ ናቸው፤ እነዚህም ሙሴ ለእስራኤል እንደ ነበረው ሁሉ ኢየሱስም ለቤተ ክርስቲያን መሆኑን ያሳያሉ።

[4] እነዚህኑ ሁለት ሴቶች ተመሳሳይ ድርጊት አያከናወኑ የሐንስ ምዕራፍ 11 ውስጥ እናገኛቸዋለን። ማርታ እንደ ሥራ ስታናውን ማርያም ግን ኢየሱስን ስታመልክ እናያታለን።

**§ 105ሀ**
**ናሙና ጸሎት**
**(ሉቃ 11÷1-4)**



ጸሎት በጣም አስፈላጊና ኀይል ያለው ነገር ነው:: ስለ ጸሎት በመጠኑ የምናውቀውና በጥቂቱ የምንጸልየው ለምንድን ነው፧ እኛ ብቻ አይደለንም ችግር ያለብን:: የመጀመሪያዎቹ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርትም ስለ ጸሎት ችግር ነበረባቸው:: ጌታ ሲጸልይ በአድናቆት ተመልክተውታል፤ ሳይቀኑበትም አልቀሩም::

በደንብ እና ዘወትር ይጸልይ ነበር:: በተለይ ሉቃስ ስለ የኢየሱስን የጸሎት ሕይወት በአጽንዖት ገልጿል (3÷21፤ 5÷16፤ 6÷12፤ 9÷18:28፤ 11÷1፤ 22÷32÷41፤ 23÷34):: ኢየሱስ ከአብ ጋር ከነበረው አጭር የቆይታ ጊዜ ሲመለስ ደቀ መዛሙርቱ ጥያቄ ይዘው ወደ እርሱ በመቅረብ፣ «ጸሎት መጸለይን አስተምረን» አሉ:: ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን ቀረቤታ እነርሱም ፈለጉ::

1አንድ ቀን ኢየሱስ በአንድ ስፍራ ይጸልይ
ነበር፤ ጸሎቱንም እንደ ጨረሰ፣ ከደቀ መዛሙርቱ
አንዱ፣ «ጌታ ሆይ፤ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርቱን ጸሎት
እንዳስተማራቸው አንተም መጸለይን አስተምረን»
አለው::

**ሉቃ 11÷1**

አብዛኛው ይህ ክፍል የታወቀና የተለመደ ይመስላል:: እንዲያውም ቍ. 2-4 እና 9-12 ከተራራው ስብከት በቀጥታ የተወሰዱ ናቸው:: ይህ ማለት ግን ሉቃስ የማቴዎስን ጽሑፍ በማስተካከል አርትዖት አድርጎበታል ማለተ አይደለም::[5] 72ቱ ደቀ መዛሙርት

[5] A.J. Banstra, "The Original Form of the Lord's Prayer," *CTJ* 16 (1981): 15-37 የዚህን ጸሎት ሁለት ዓይነት ጽሑፎች አስመልክቶ አምስት ዐይነት ሐሳቦችን ይገመግማል (ይመዝናል):: (1) ኢየሱስ በተለያዩ ሁለት ሁኔታዎች ለሰዎች የሰጠው ጸሎት አንድ ዓይነት ሲሆን፣ ይህም



ጉብኝት ካደረጉ በኋላ ከዚህ ቀደም ያልነበሩ ብዙ ሰዎች ይሰበሰቡ ነበር:: ዐሥራ ሁለቱ ከዓመት በፊት ገሊላ ውስጥ የሰሙትን ነገር እነዚህ የአይሁድ ሰዎች ዛሬ ለመጀመሪያ ጊዜ መስማታቸው ሊሆን ይችላል::

ዮሐንስ ደቀ መዛሙርቱን መጸለይን እንዴት እንዳስተማራቸው ሕዝቡ በደንብ ያስታውሳሉ:: ያኔ አንድ መምህር አንዳንድ መሠረታዊ ጉዳዮችንና የጸሎት ሥርዐቶችን ማስተማሩ እንግዳ ነገር አልነበረም:: ዮሐንስም የግሉ የሆኑትን አንዳንድ የጸሎት አቀራረቦች አስተማረ:: ይህ ደቀ መዝሙር፣ ኢየሱስ የራሱን ልዩ የጸሎት አካሄዶችና አጽንዖቶች ያስተምር ዘንድ የሚጠይቅ ይመስላል:: በመደረግ ላይ የነበሩት ነገሮች ሁሉ ውጤት የሚያስገኙ ይመስላሉ:: የኢየሱስ ጸሎት አንዱ ማራኪ ገጽታ እግዚአብሔርን ምንጊዜም አባት ብሎ መጥራቱ ነው (ከዮሐ 20÷17፤ ከሮሜ 8÷14-17 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ማርቆስ ወንጌል 15:34 ውስጥ ጉልቶ ከሚታየው ልዩነት በቀር ማለት ነው:: የፍልስጥኤም አይሁድ እግዚአብሔርን «አባት» ቢሉትም እንኳ

በማቴዎስና በሉቃስ ታማኝ ጽሑፍ ላይ ሰፍሮአል:: (2) የማቴዎስ ጽሑፍ ላቅ ያለ ወጥነት ያለው ሲሆን፣ ሉቃል አርትዖት አድርጎበታል:: (3) የሉቃስ ጽሑፍ የላቀ ወጥነት ያለው ሲሆን፣ ማቴዎስ ለአምልኮ እንዲመች በማድረግ ጨምሮበታል:: (4) በሁለቱም መልክ የቀረበው ጸሎት በመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን ተፈጠረ እንጂ በኢየሱስ አልተሰጠም:: (5) ማቴዎስና ሉቃስ ለየራሳቸው «እምላኪ ማኅበረሰቦች» እንዲመች አድርገው ከኢየሱስ የተሰጡትን ቃሎች ለውጠዋል:: Banstra የማቴዎስ ጽሑፍ ለአይሁድ ክርስቲያኖች አገባብነት ያለው ነው:: የሉቃስ ደግሞ ለአሕዛብ ክርስቲያኖች አገባብነት አለው በማለት አምስተኛውን መፍትሄ ይቀበላል:: ይሁን እንጂ አንዳንድ ጥንቃቄዎች ሊቀርቡ ይገባል:: በመጀመሪያ ደረጃ የBanstra መደምደሚያ የተመሠረተው በአርትዖት ሐተታና በወንጌሎች መካከል የጽሑፍ ተውሶ በሚለው ላይ ሲሆን፣ ግራ ቀኙም በደንብ የተረጋገጡ አይደሉም:: ሁለተኛ ሁለቱም የጸሎት ጽሑፎች ብርቱ ጥንቃቄ የተደረገበትን የሥነ ግጥማዊ ጽሑፍ ምልክት ያሳያሉ:: ስለዚህ አንዱን፣ «የላቀ ወጥነት አለው» ለማለት የሚቻል አይደለም (አደገኛም ነው):: ሦስተኛ ኢየሱስ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ የሚያስተምር መምህር ነበር:: ተመሳሳይ አቀራረብ በተለያየ ቦታና ጊዜ ቢቀርብ ለየት ባለ መልኩ መቅረቡ የማይቀር ነው::

13 ጋር ያነጻጽሩ)፣ «አባት» ብለው ጸሎት
...ም፡፡ ለዚህ ነው ኢየሱስ በደቀ
...ከል አዲስ ቅርርብን የፈጠረው፡፡
...ዳንድ ትምህርቶች አሉ፤ (1) ድንገት
...ን በጽሑፍ ላይ ያለ ወይም የተጠና ጸሎት
... መቅረብ አለበት፡፡ እነዚህ ጸሎቶች ትኩረት
ያላቸው ...ቸው፤ እያንዳንዱ መሥመር ትርጉም አለው፡፡ ብዙውን ጊዜ ጥልቅ የሆነውን ነገረ መለኮት ከውብ ቋንቋ ጋር ዐዘለው ይገኛሉ፡፡ ብዙ ነገር ስለ አካተቱ ድንገት ለሚቀርብ ጸሎት መነሻ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ማኅበረሰባዊ ማለት የቤተ ክርስቲያንም ናቸው፡፡ ስለዚህ ከሌሎች አማኞች ተለይተን እንዳንጸልይ ማስገንዘቢያ ቀ...ልናል፡፡ (2) «የጸሎት አስተማሪዎችን» ብንሻና የእነርሱን የጸሎት አቀራረብ ብንከተል ውጤታማ እንሆናለን፡፡ የእግዚአብሔርን ፊት ፍለ... በምናደርገው ጉዞ ሊመሩን ይችላሉ፡፡ (3) ጸሎት ትምህርት ሆኖ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ዘወትር እንዲሁ ፍስስ ብሎ አይመጣ ይሆናል፡፡ ልምድ ምናልባትም በተወሰነ መልኩ ልምምድን ሊጠይቅ ይችላል፡፡

2እርሱም እንዲህ አላቸው፤ «ስትጸልዩ እንዲህ በሉ፤
«አባታችን[m] ሆይ፤
ስምህ ይቀደስ፤
መንግሥትህ ትምጣ፤[n]
3የዕለት እንጀራችንን በየዕለቱ ስጠን፤
4በደላችንን ይቅር በለን፤

**ሉቃ 11፥2-4**
**ማቴ 6፥9-13 ጋር**

[6] J. Jeremias. *The Prayers of Jesus* (Naperville: Allenson, 1967) p. 97 ጋር ያነጻጽሩ፡፡ ይሁን እንጂ W.A. VanGemeren «'ABBA'» in the Old Testament? *JETS* 31/4 (1988): 385-398 ጽሑፉ «ከእግዚአብሔር አብ» ጋር ቅርብ ግንኙነት በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን ላይ ይገኛል ይላል፡፡ ስለዚህ በሁለቱ ኪዳኖች መካከል ክፍፍል የለም፡፡ ይሁን እንጂ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ከፍ አድርጎታል፡፡



እኛም የበደሉንን[o] ሁሉ
ይቅር ብለናልና፡፡
ወደ ፈተናም አታግባን፡፡»[p]

[m]2 አንዳንድ ቅጆች በሰማይ የምትኖር አባታችን ይላሉ
[n]2 አንዳንድ ቅጆች ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን ይላሉ
[o]4 አንዳንድ ቅጆች በእኛ ላይ ኀጢአት የሠሩትን ይላሉ
[p]4 አንዳንድ ቅጆች ከክፉው ግን አድነን ይላሉ

[ቍ. 2-4 ማቴ = 6:9-13 በቍ. § 54''' ላይ የቀረበውን ማብራሪያ ይመልከቱ]፡፡

ማቴዎስና ሉቃስ ውስጥ በቀረበው የጌታ ጸሎት መካከል ልዩነቶች አሉ፡- (1) ማቴዎስ ውስጥ የቀረበው፣ ረዘም ያለና ይበልጥ አምልኮአዊ (ቅዳሴያዊ) ሥርዐት ነው (ማቴዎስ ስላደረገው ጭማሪ ከፍ ብሎ የቀረበውን ጽሑፍ ይመልከቱ)፡፡ (2) ማቴዎስ «የዕለት እንጀራችንን» ይላል፤ ሉቃስም እንዲሁ ይላል፡፡ ስለዚህ በማቴዎስ ወንጌል የእንጀራ ልመና አጣዳፊ ልመና ነው፤ (3) ወገኖቻችንን ይቅር የማለት ጉዳይ ማቴዎስ ውስጥ የተጠቀሰው ኅላፊ ግስ ነው፤ ሉቃስ ውስጥ ግን የአሁን ወይም የወደፊት ጊዜ ግስ ነው፤ «ይቅር እንደምንል፤» (4) ማቴዎስ «መተላለፋችንን» ሲል ሉቃስ ግን «በደላችንን» ይላል፡፡ (ይህ ሁሉ ልዩነት ይበልጥ ጉልሕ ሆኖ የሚገኘው ግን በእንግሊዝኛው ትርጉም ነው)፡፡

## § 105ለ ጸሎት ስለማድረግ ምክር (ሉቃ 11፥5-13)

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ እንዴት መጸለይ እንዳለባቸው ነግሮአቸዋል፡፡ አሁን ደግሞ እንዲተገብሩት አደፋፈራቸው፡፡ አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር በእውነት እንደሚሰማን

ለማመን አስቸጋሪ ነው:: የእኔ ደካማ ጸሎት ልዑል እግዚአብሔርን ያንቀሳውሰዋልን? እንል ይሆናል:: በርግጥ ያንቀሳቅሰዋል፤ የዚህ ምሳሌ የሚሆን ትምህርት ይኸው::

**ሉቃ 11÷5-8**



5ደግሞም እንዲህ ኣላቸው፤ «ከእናንተ አንዱ
ወዳጅ ቢኖረውና በእኩለ ሌሊት ወደ እርሱ ሄዶ፤
'ወዳጄ ሆይ፤ ሦስት እንጀራ አበድረኝ፤ 6አንድ
ባለንጀራዬ ከመንገድ መጥቶብኝ የማቀርብለት ምንም
ነገር የለኝምና' ብሎ ለመነው እንበል:: 7«በቤት ውስጥ
ያለውም፣ 'አታስቸግረኝ፤ በሩ ተቆልፎአል፤ ልጆቼም አብረውኝ ተኝተዋል፤
ከእንግዲህ ተነሥቼ ልሰጥህ አልችልም' ይለዋልን? 8እላችኋለሁ ወዳጁ በመሆኑ
ተነሥቶ ባይሰጠው እንኳ፣ ስለ ንዝነዛው ብቻ የሚፈልገውን ሁሉ ይሰጠዋል::»

*8ወይም መወትወት*

ይህ ምሳሌ ከእኛ ይልቅ በፖሊስትንኛ የበለጠ ትርጉም አለው:: ለምሳሌ አንድ ወዳጃችን በእኩለ ሌሊት ወደ ቤታችን ቢመጣ ድርጊቱ ያልተገባ ነገር ሆኖ ይቈጠራል:: ረዥም ጉዞ በእግርህ ከተጓዝህ ግን ይህ የማይቀር አጋጣሚ ነው:: የፖሊስትናን አስጨናቂ ሐሩር ለማምለጥ ከፈለግህ በሌሊት ነው የምትጓዘው:: በእኩለ ሌሊት ጎረቤትን መቀስቀስም ያልተገባ ነገር ይመስላል:: ድርጊቱ ያልተገባ የሚሆንበት ምክንያት ብዙ የፖሊስትና ቤተ ሰቦች አንድ ክፍል ውስጥ አንድ መኝታ ላይ የሚተኙ በመሆናቸው ነው:: ለወዳጁ እንጀራ ለመስጠት አባት ቢነሣ ሚስቱንና ልጆቹን ይቀሰቅሳቸዋል:: አንድ እንግዳ በአንድ ቤተ ሰብ ብቻ ሳይሆን በመላው ማኅበረ ሰብ እንዲስተናገድ መደረጉም የባህላቸው አካል ነበር:: ስለዚህ ይህ ጎረቤት ወዳጁ ባቀረበለት ጥያቄ ቅር በሲኝም እንኳ፣ ለእንግዳው የሚሆነውን ነገር ወዳጁ ያሟላላት ዘንድ የመጠየቅ መብት አለው:: በመለስተኛ ማኅበረ ሰቦች ዘንድም ቤተ ሰባቸው ለሳምንቱ የሚሆነውን እንጀራ የጋገረ መሆኑን ለመደበቅ አይቻልም::



ይህ ምሳሌ አብዝታ ለነዘነዘችው መበልት ጨካኙ ዳኛ እንዲፈርድላት የተገደደ መሆኑን ከሚገልጸውና ሉቃስ 18÷1-8 ውስጥ ካለው ታሪክ ጋር ተመሳሳይ ነው:: ስለዚህ ኢየሱስ የሚለው ምንድን ነው? እግዚአብሔር እኛ የለመንነውን ከመስጠቱ በፊት ጎትጓችና ነዝናዦች መሆን እንዳለብን እያሳሰበን ነውን? በእርግጥ አይደለም:: ይህ የማነጻጸሪያ እንጂ የማወዳደሪያ ምሳሌ አይደለም:: ከአነስተኛው ወደ ላቀው የሚጓዝና ዘመናትን ያሳለፈ የአይሁድ ምክንያታዊ (ተጠየቃዊ) አቀራረብ ነው:- አንድ ንፉግ ጎረቤትህ በድፍረት ላቀረብከው ጥያቄ እሽ የሚልህ ከሆነ፣ እግዚአብሔር መልካም ስጦታ ለልጆቹ በመስጠት የቱን ያህል ይደሰታል! ወደ እግዚአብሔር በሙሉ ልብ ለመቅረብ እንችላለን፤[7] ምክንያቱም እርሱ የጠየቅነውን በመስጠት ደስ የሚለው አፍቃሪ አባታችን ነው:: ይህ ቀጥሎ ቊ 9-13 ላይ ከሰፈረው ሐሳብ ጋር በትክክል ይገጣጠማል::

**ሉቃስ 11÷9-13**

9«ስለዚህ እላችኋለሁ፤ ለምኑ ይሰጣችኋል፤
ፈልጉ ታገኛላችሁ፤ በር አንኳኩ ይከፈትላችኋል፤
10ምክንያቱም የሚለምን ሁሉ ይቀበላል፤ የሚፈልግም
ያገኛል፤ በር ለሚያንኳኳም ይከፈትለታል::

[7] Klyne Snodgrass, "*Anaideia* and the Friend at Midnight (Lk 11:8)" *JBL* 116/3 (Fall 1997): 505-513 በሰብዓ ሊቃናት ትርጉም፣ በግሪክና በጥንት ክርስቲያናዊ ጽሑፎች *Anaideia* ማለት ምንጊዜም «ኀፍረተ ቢስነት» ወይም «ፊቀደኛ» አለመሆን ከሚለው በቀር ማለት ነው):: በተጨማሪም ይህ «ዐይን አውጣነት» ከበር አንኳኪው ይልቅ የተኛው ሰው ጠባይ ሊሆን ይችላል:: ይህም ከመኝታው ሊነሣ ይችላል፤ ሰውዬው ከመኝታው የተነሣው ወዳጁ ማንኳኳቱን በመቀጠሉ ሳይሆን፣ በበነጋው ከማኅበረ ሰበ ዘንድ ሊመጣበት የሚችለውን መዋረድ ከመፍራት ነው (ከNolland pp 625-626 ጋር ያነጻጽሩ):: ይሁን እንጂ የዚህ ምሳሌ ቀዳሚ ትኩረት የማያቋርጥ ጸሎት ሳይሆን ድፍረት ያለበት ጸሎትን ነው:: የA.F Johnson, "Assurance for Man: The Fallacy of Translating *Anaideia* by 'Persistence' in Luke 11:5-8," *JETS* 22/2 (1979):123-131 ይመልከቱ::

11«ከእናንተ መካከል አባት ሆኖ ሳለ ልጁ ዓሣ ቢለምነው እባብ የሚሰጠው ይኖራልን? 12ወይስ ዕንቍላል ቢለምነው ጊንጥ ይሰጠዋልን? 13እናንተ ክፉዎች ሆናችሁ ሳላችሁ፣ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታን መስጠት ካወቃችሁበት፣ የሰማይ አባታችሁ ታዲያ ለሚለምኑት መንፈስ ቅዱስን እንዴት አብልጦ አይሰጥ!»

*11አንዳንድ ቅጆች ዳቦ ቢለምነው ድንጋይ ይሰጠዋልን? ይላሉ::*

[ቍ. 9-13 = ማቴ 7፥7-11 በቍ. §54ሸ የቀረበውን ማብራሪያ ይመልከቱ]

ሉቃስ ከማቴዎስ በመጠኑ የሚለየው፣ በቃላት አገባብ ነው:: ቍጥር 11 ውስጥ ማቴዎስ የተጠቀመው የዳቦ/ድንጋይ ገልጦ ማሳያን ሲሆን፣ ሉቃስ ግን የዕንቍላል/ጊንጥ ገልጦ ማሳያን ይጠቀማል:: Viner የተጠቀለለው ጊንጥ ዕንቍላል ይመስላል ይላል::[8] ሉቃስ ነጠላ ቍጥር የሆነውን፣ «የሰማይ» (ቋሚ የሆነ የግሪክ አገላለጽ ነው) የሚለውን ሲጠቀም ማቴዎስ «ሰማያት» (ቋሚ የዕብራይስጥ አገላለጽ ሆኖ በአንዳንድ ቅጆች ላይ በዚህ መልኩ ይገኛል) የሚለውን ይጠቀማሉ:: ሁለቱም አነስተኛ ልዩነቶች ናቸው:: ቍጥር ውስጥ የሚገባ ሌላ ልዩነት አለ:: በማቴዎስ ላይ እንዳለው፣ «መልካም ስጦታን» በማለት ፈንታ ሉቃስ «መንፈስ ቅዱስን» ይላል:: ይህ ልናገኘው የሚቻለን ከፍተኛ ስጦታ ነው (ከሐሥ 1፥4፤ 2፥33፤ ከሉቃ 24፥49 ጋር ያነጻጽሩ)::

ሐሳቡ ግልጽ ነው:: እኩለ ሌሊት ቢሆንም እንኳን እንግዶችን ለማስተናገድ ከገብጋባ ጎረቤትህ የሚያስፈልግህን ለማግኘት ተስፋ ታደርጋለህ:: ታዲያ አፍቃሪ አባታችን ለእኛ ጥቅም የሚሆነውን ሁሉ፣

[8] T. Viner, "Stories Jesus Told: The Friend at Midnight," *CS* (Feb. 3, 1991): 17.

በተለይ መንፈስ ቅዱስን ለመስጠት እንዴት ፈቃደኛ አይሆንም! ስለዚህ ተነሥና ጠይቅ! የሚያስፈልግህን እንደምታገኝም እርግጠኛ ነህ::

**§ 106**
**ብዔል ዜቡልና የዮናስ ምልክት**
**(ሉቃ 11፥14-36 ከቍ. 61-62፣ ከማቴ 12፥22-45፤ ከማር 3፥20-30 ጋር ያነጻጽሩ**

እነዚህን ቃሎች ቀደም ሲል አንብበናቸዋል (ቍ. 61-62):: ማቴዎስና ሉቃስ ገሊላ ውስጥ የተፈጠረውን አስቀያሚ ፍጥጫ ለመግለጽ ተጠቅመውባቸዋል:: ሉቃስ በይሁዳ የነበረውን ጭቅጭቅ ለመግለጽ ተመሳሳይ ቃላትን ተጠቅሞአል:: በዚህ ብዙ መደነቅ የለብንም:: ሉቃስና ማቴዎስ በይሁዳ (ሉቃ 10) የሰባ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት መላክና በገሊላም የዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት መላክ ለመግለጽ በተመሳሳይ ቃላት ተጠቅመዋል:: ይህን ክሥተትም ሉቃስ «ማእከላዊ ክፍል» ውስጥ ልብ እንላለን:: በመጀመሪያው የኢየሱስ አገልግሎት ላይ በሰሜን በኩል እውን የሆኑት ክሥተቶች፣ በኋላኛው አገልግሎቱ በደቡብ ክፍል የተደገሙ መሆናቸውን ግልጽ አድርጎአል::

በዚህ በይሁዳ ያሉት የሃይማኖት መሪዎች እንኳ ኢየሱስ ታላቅ ታምራት ያደረገ መሆኑን አይክዱም:: ይህን ሰውና እንቅስቃሴውን ችላ ማለት ያዋጣቸዋልን? አንድም የኢየሱስ ኀይል ከእግዚአብሔር መሆኑን አምነው ለጌትነቱ መገዛት አለባቸው፤ ወይም የታምራት ኀይሉን አዋርደው ከሰይጣን ነው በማለት ለሰይጣን መስጠት አለባቸው:: ኢየሱስ ትክክል እንደ ነበር ለማመን የተዘጋጁ አይደሉም:: ያላቸው ብቸኛ ምርጫ እርሱን መተቸት ነው:: ይህን በማድረጋቸው ኢየሱስ የሰጣቸውን ማስጠንቀቂያ ማቴዎስ በጽሑፍ ገልጾልናል:: በትሥጉቱ በክርስቶስ ላይ የስድብ ቃል መሰንዘር ይቅር ሊባል ይችላል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚሰነዘር የስድብ ቃል ግን ይቅር አይባልም:: እንግዲህ እነዚህ ወገኖች በአደገኛ ሁኔታ ከማይመለሱበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል ማለት ነው::

## ኢየሱስና ብዔል ዜቡል

ሉቃ 11÷14-23
ከማቴ 12÷22-25፣
ከማር 3÷22-23
ጋር

14እንድ ቀን ኢየሱስ ድዳ ጋኔን ያወጣ ነበር፤ ጋኔኑም
ከወጣበት በኋላ ድዳው ሰው ተናገረ፤ ሕዝቡም
ተገረሙ:: 15እንዳንዶቹ ግን፣ «በአጋንንት አለቃ፣
በብዔል ዜቡል[ll] አጋንንትን ያወጣል 16እንዳንዶቹ ደግሞ
ሊፈታተኑት ከሰማይ ምልክት እንዲያሳያቸው ከእርሱ
ይፈልጉ ነበር::
17ኢየሱስ ግን ሐሳባቸውን ዐውቆ እንዲህ
አላቸው፤ «እርስ በርሱ የሚከፋፈል መንግሥት ሁሉ
ይጠፋል፤ የሚለያይ ቤትም ይወድቃል:: 18ሰይጣንም
እርስ
በርሱ ከተከፋፈለ መንግሥቱ እንዴት ይጸናል? አጋንንትን በብዔል ዜቡል እንደማወጣ
ትናገራላችሁና:: 19እንግዲህ እኔ አጋንንትን የማወጣው በብዔል ዜቡል ከሆነ፣
ልጆቻችሁ በማን ያወጧቸው ይሆን? ስለዚህ እነርሱ ፈራጆች ይሆኑባችኋል:: እኔ ግን
አጋንንትን የማወጣው በእግዚአብሔር ጣት ከሆነ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ
እናንተ እንደ መጣች ዕወቁ::
21«ብርቱ ሰው በሚገባ ታጥቆ ቤቱን ከጠበቀ፣ ንብረቱ በሰላም
ይቀመጣል:: 22ነገር ግን ይበልጥ ብርቱ የሆነ ሰው መጥቶ ካጠቃውና ካሸነፈው
ታምኖበት የነበረውን ትጥቁን ያስፈታዋል፤ ምርኮውንም ወስዶ ለሌሎች ያካፍላል::
23«ከእኔ ጋር ያልሆነ ይቃወመኛል፤ ከእኔ ጋር የማይሰበስብም ይበትናል::»

*[ll] 15 ገፅ ብዔል ዜቡል ወይም ብዔል ዜብል ይባል፤ እንዲሁም ቍ 18፡19 ይመ::*

[ቍ 14-23 = ማቴ 12÷22-30፤ ማር 3÷22-27፤ በቍ 61 ላይ
የቀረበውን ማብራሪያ ይመልከቱ]



ሉቃስ ያልገለጻቸውን ሁለት ነገሮች ማቴዎስ ገልጿል:: በመጀመሪያ፣ ነቀፋው የተመራው በፈሪሳውያን ነው:: ሁለተኛ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል መሰንዘር በሚለው ሐተታ ነገሩ ይደመደማል:: ይህ አስፈሪና ኀይለኛ አባባል ነው::[2] በተለይ ብርቱ የሆነውን ሰው ቤት መበዝበዝን አስመልክቶ ሉቃስ ያቀረበው ሐተታ እጅግ ሥዕላዊ ነበር::

ፈሪሳውያን ኢየሱስን ሰይጣን ነህ በማለት ወነጀሉት:: ይህ በቀላሉ የሚታለፍ ውንጀላ አይደለም:: እርሱም እንዲሁ ችላ ብሎ ሊያልፈው አይቻለውም:: እንዲያውም ይህን ውንጀላ ለማስተባበል ከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘውን ተጠየቁን አዘጋጀ::

**ክርክር ቍ 1:-** ***«እርስ በርሱ የሚከፋፈል መንግሥት ሁሉ ይጠፋል!»*** የኢየሱስ ኀይል የሰይጣንን መንግሥት ለማፈረስ እየሠራ ነው:: የሰይጣን ወገን ቢሆን ኖሮ እርሱን መቃወም ሳይሆን ለእርሱ ይሠራ ነበር:: ይህ ደግሞ አንድ ሰው ፊት ላይ ለመትፋት አፍንጫን እንደ መቍረጥ ያህል ነው:: ሰይጣን አንድን ጋኔል አያዝም ማለት ሳይሆን አያደርገውም ማለት ነው::

**ክርክር ቍጥር 2:-** ***«ልጆቻችሁ በማን ያወጧቸው ይሆን?»*** ለክርክሩ ያህል ኢየሱስ አጋንንትን በማስወጣቱ ሥራው የሰይጣን ነው እንበል:: ይህ ክርክር ለሌሎች የአይሁድ መተተኞች አይሠራምን (ከሐሥ 19÷13-14 ጋር ያነጻጽሩ):: ግብዝነታቸው ጕልሕ ነው:: በኢየሱስ ላይ ያወረዱት ውግዘት በራሳቸው ላይ ይደርሳል::

**ክርክር ቍጥር 3:-** ***«የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ እንደ መጣች»*** ሰዎቹ የኢየሱስን የነገር አካሄድ ተገንዝበውት ከሆነ እዚህ ላይ ፍርሀት ሊያድርባቸው ይገባል:: ሌላው ቀርቶ ከእነርሱ አኳያ ሲታይ የኢየሱስ ኀይል ከእግዚአብሔር የመሆኑ ሐቅ የሩቅ እውነታ አለው ቢባል እንኳ፣ በእግዚአብሔር ስም ላይ አስከፊ የሆነውን የስድብ ቃል ፈጽመዋል:: «እንደ መጣች» የሚለው ሐረግ

«መጣ» ከሚለው መደበኛ ግስ የተገኘ አይደለም:: ይህ ማለት «ደረሰ፣ እኩል ደረሰ» ወይም በ1ተሰሎንቄ 4÷15 ላይ እንዳለው «እስኪመጣ» እንደ ማለት ነው:: ዐይነተኛው ጉዳይ:- የእግዚአብሔር መንግሥት በራቸው ላይ ያለመሆኑ ነው!

«በእግዚአብሔር ጣት» የሚለውን ዘይቤ ስናስተውል ይህ ይበልጥ አስገራሚ ይሆናል:: ይህ ሐረግ በግልጽ የሚያመለክተው፣ የእግዚአብሔርን ኀይል ነው:: ይሁን እንጂ ዘፀአት 8:19 ውስጥ እንደምንረዳው (የሙሴና የአሮን የተባይ መቅሠፍት) በሰው በኩል የእግዚአብሔርን ኀይል ያሳያል:: ኢየሱስ በዚህ ሐረግ አማካይነት ከእስራኤል የባርነት ነጻነት ጋር[9] ግንኙነት ያለውን ትእምርታዊ ታምራትን ለማድረግ ኀይል ተቀብለው ከነበሩትና ከእግዚአብሔርም ከሆኑት ከእውነተኞቹ መልእክተኞች፣ ከሙሴና ከአሮን ጋር ቢያንስ ቢያንስ ራሱን ማሳለፉን ያሳያል:: ከዚህም በላይ የፈርዖን አስማተኞች ከዚህ ቀደም እንዳከናወኗቸው እንደ ሁለቱ መቅሠፍት አሁን ለማድረግ እንዳልቻሉ ሁሉ፣ ኢየሱስም «ተራ አስማት» ነው በማለት ከተቃወሙት ፈሪሳውያን እጅግ ሉዐላዊ ነው:: አሁን ተቃዋሚዎቹ ተፈርደባቸዋል::

**ክርክር ቁጥር 4:-** ***ይበልጥ ብርቱ የሆነው ሰው መጥቶ ካጠቃውና ካሸነፈው ታምኖበት የነበረውን ትጥቁን ያስፈታዋል፤»*** ይህ ሐሳብ በኢየሱስ ላይ ትችት ላቀረቡት ሰዎች አስፈሪ ነው:: ኢየሱስ ሰይጣንን ትጥቁን አስፈትቶታል:: ይዞታውንም ከፋፍሎአል:: ግዛቱን በእጁ አስገብቶአል፤ አጥቅቶታል፤ ኀይሉን ገፎታል፤ ንብረቱንም ማርኮአል፤ ቀጥሎ ያለው ማነው?!

---

[9] Paul Meier, p. 411.



## አጋንንት በምድረ በዳ

[24]ርኩስ ǁመንፈስ ከሰው ሲወጣ ዕረፍት ፍለጋ ውሃ በሌለበት ስፍራ ይንከራተታል፤ ሳያገኝም ሲቀር፣ ወደ ወጣሁበት ቤቴ እመለሳለሁ ይላል፤[25] ሲመለስም ቤቱ [ባዶ ሆኖ ማቴ] ተጠራርጎና ተስተካክሎ ያገኘዋል::[10] [26]ከዚህም በኋላ ሄዶ ሌሎች ከእርሱ የከፉ ሰባት አጋንንት ይዞ ይመጣል፤ ገብተውበትም በዚያ ይኖራሉ፤ ስለዚያ ሰው ከመጀመሪያው ይልቅ የኋላኛው ሁኔታ የከፋ ይሆንበታል:: [በዚህ ክፉ ትውልድም ላይ እንዲሁ ይሆንበታል::ማቴ]»

***ሉቃ 11÷24-26 ከማቴ 12÷44-45 ጋር***

*ǁ24 ወይም ክፉ*

[ቁ. 24-26 = ማቴ 12÷43-45፤ በቁ. 62 ላይ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ]

ይህ ሁሉ ክርክር የተጀመረው ኢየሱስ ከድዳው ሰውየ ጋኔን ባስወጣ ጊዜ ነበር:: ሰውዬው የትኩረት ማዕከል ሆኖአል:: ኢየሱስ የመላውን ሕዝብ አስከፊ ሁኔታ ለማሳያነት ተጠቅሞበታል:: ለሰውዬውም በጎ ነገር አድርጎለታል:: ጋኔኑን በማስወጣት ንጹሕ አድርጎታል:: ይህ መልካም ነገር ነው:: ነገር ግን ይህ ሰው አካሉን በሌላ ነገር ካልሞላ፣ እርካታን አጥቶ የሚዞረው ጋኔን ከሰራዊቱ ጋር ንጹሕ ወደ ሆነው መኖሪያው መመለሱ አይቀርም:: ከዚያም ይህ ሰው የባሰ ይሆንበታል:: እንደዚሁም የኢየሱስ አገር ሰዎች ከእርሱ መገኘት

---

[10] «ተስተካክሎ» [ኮስሜዎ- *Kosmeo*] የሚለው ቃል «አምሮ» ወይም «ተሟልቶ» የሚል ግንዛቤ ይሰጣል:: ሥዕሉ የቤት ዕቃ ሳይኖርበት ወና የሆነውን ቤት አያመለክትም:: ይልቁንስ ተቃራውን እውነት ነው:: በመኖሪያ ዝግጁ ነው:: የእኛ ልብ ሁኔታም እንደዚሁ ነው:: መንፈሳዊ መኖሪያ ዝግጁ ነው::

(ሀልዎት) የተነሣ ታላቅ በረከትን አግኝተዋል:: ጌታ አድርገው ካልተቀበሉት ግን፣ ለድንገተኛ ሁኔታ ተዘጋጅተዋል፤ መከራቸው እርሱ ከመምጣቱ በፊት ከነበረውም የከፋ ይሆናል::

**ሉቃ 11÷27-28**

[27]ኢየሱስ ይህን እየተናገረ እያለ፣ ከሕዝቡ መካከል
አንዲት ሴት ድምፅዋን ከፍ አድርጋ፣ «የተሸከመችህ
ማሕፀንና የጠባሃቸው ጡቶች ብፁዓን ናቸው»
አለችው::
[28]እርሱ ግን፣ ብፁዓንስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚታዘዙት ናቸው»
አለ::

ይህች ሴት የማርያምን አካል በተለይ ማሕፀኗንና ጡቶቿን ትባርካለች:: ማርያም ኢየሱስን በማርገዝና ልጇ እንደ መሆኑ መጠን በማሳደጉ ተባርካ ነበር (ሉቃ 1÷28-35÷42-55):: እግዚአብሔር እምነቷንና ቅድስናዋን አክብሮአል:: ይሁን እንጂ እርሷም እንደ መጥምቁ ዮሐንስ በእግዚአብሔር መንግሥት ከትንሹ ያነሰች ነበረች:: የኢየሱስ የመግቢያ ቃል ሚናውን - *menoun* እውነት «እውነት ነው፤ ነገር ግን» እንደ ማለት ነው:: ኢየሱስ እርሷ የተናገረችውን ቢያፀናም ምሉእ አለመሆኑን አመልክቶአል:: እውነተኛ መባረክ የሚመጣው የእግዚአብሔርን ቃል በመስማትና በመታዘዝ ነው:: ለቃሉ ከመታዘዝ ውጭ በረከት የለም:: ይህ የኢየሱስ ቤተ ሰዎች ሲፈልጉት እንደ ነበረው እንደ ማቴዎስ 12÷46-50 (ቊ 63) ነው:: ሁለቱም ክፍሎች የኢየሱስ እውነተኛ ቤተ ሰዎች የሚሰሙና የሚታዘዙ ናቸው ይላሉ:: ይህም ከፈሪሳውያን አካሄድ እጅግ ይለያል::



## የዮናስ ምልክት

**ሉቃ 11÷29-32**
**ከማቴ 12÷39**
**ጋር**

[29]ብዙ ሕዝብ እየተሰበሰበ በሄደ ጊዜ ኢየሱስ
እንዲህ ይል ጀመር፤ «ይህ ትውልድ ክፉ [የ
አመንዝራ[ማቴ]] ነው፤ ታምራዊ ምልክት ይፈልጋል፤ ነገር
ግን ከዮናስ ምልክት በስተቀር ሌላ አይሰጠውም::
[30]ምክንያቱም ዮናስ ለነነዌ ሰዎች ምልክት እንደ ሆናቸው የሰው ልጅም ለዚህ
ትውልድ ምልክት ይሆናል:: [31]የደቡብ ንግሥት በፍርድ ጊዜ ከዚህ ትውልድ ጋር
ተነሥታ ትፈርድባቸዋለች፤ እርሷ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከምድር ዳርቻ
መጥታለችና፤ እነሆ፤ ከሰሎሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ:: [32]የነነዌ ሰዎችም በፍርድ
ጊዜ ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥተው ይፈርዱበታል:: እነርሱ የዮናስን ስብከት ሰምተው
ንስሓ ገብተዋልና፤ እነሆ፣ ከዮናስ የሚበልጥ እዚህ አለ::

[ቊ 29-32 = ማቴ 12÷38-42፤ በቊጥር 62 ላይ የሚገኘውን ማብራሪያ ይመልከቱ]

በዚህ ጊዜ ነገሮች በመክረር ላይ ናቸው:: ሕዝቡ ሁካታውን ለማጣራት ተሰብስበዋል:: ኢየሱስ በቊጥር 15 ላይ ለተሰነዘረበት ክስ በዚህ ጊዜ መልስ ሰጠ:: አሁን ደግሞ ከሕዝቡ መካከል አንዳንዶች ወዳቀረቡት ጥያቄ ተመለሰ:: ይህ ጥያቄው ቊጥር 16 ውስጥ ስለሚገኘውና ከሰማይ ስለ ሆነው ምልክት ነው::

ከሰማይ ምልክት ለመጠየቅ እንዴት ደፈሩ! በመጠኑም ቢሆን እንዲብራራላቸው መጠየቃቸው ስሕተት የለበትም:: የታምራት ሙሉ ዓላማም ይኸው ነው (ከዮሐ 20÷31 ጋር ያነጻጽሩ):: ኢየሱስ ድንቅ ታምራትን አድርጎአል:: ታዲያ ሌላ ታምር ለምን ይጠይቃሉ? ምክንያቱ ሌላ ሳይሆን የሚያምን ልብ ስለሌላቸው ነው::

የእግዚአብሔር ሕዝብ ናቸው ተብሎ ስለሚታመን ይህ ድርጊታቸው እንግዳ የሚገርም ነገር ነው:: አረማውያን እንኳ ከዚህ

የተሻለ ያውቃሉ:: ለምሳሌ የነነዌ ሰዎችና ንግሥት ሳባ በሰሙ ጊዜ መልካም የሆነውን ነገር ዐውቀዋል:: ሆኖም እነዚህ ሰዎች በኢየሱስ ላይ የስድብ ቃል በመሰንዘር እዚህ ቆመዋል:: አሳፋሪ ጠባያቸው በፍርድ ቀን በእነዚህ አረማውያን እንኳን ሳይቀር ይፋ ይሆናል:: ምልክት ይሰጣቸዋል:: ግን ከሰማይ አይሆንም:: ኢየሱስ ትንሣኤ ባገኘ ጊዜ ከምድር ሆድ ይሆናል::[11]

**ሉቃ 11፤33-36**

33«መብራት አብርቶ በሰውር ቦታ ወይም
ከእንቅብ በታች የሚያስቀምጥ ማንም የለም፤ ይልቁን
የሚገቡ ሰዎች ብርሃኑን እንዲያዩ በመቅረዝ ላይ
ያስቀምጠዋል:: 34የሰውነትህ ብርሃን ዐይንህ ናት፤ ዐይንህ ጤናማ ስትሆን መላ
ሰውነትህ ብሩህ ይሆናል፤ ዐይንህ ታማሚ ከሆነች ግን መላ ሰውነትህ የጨለመ
ይሆናል:: 35ስለዚህ በውስጥህ ያለው ብርሃን ጨለማ እንዳይሆን ተጠንቀቅ::
36እንግዲህ ሰውነትህ ሁሉ ብሩህ ከሆነና የጨለመ የሰውነት ክፍል ከሌለበት፣
የሰውነትህ ሁለንተና መብራት በወገግታው ያበራልህ ያህል ይደምቃል::»

[ቍ 33 = ማቴ 5÷15 በቍጥር 54 ላይ የሚገኘውን ማብራሪያ ይመልከቱ]

[ቍ 34-36 = ማቴ 6÷22-23 በቍጥር 54 ላይ የሚገኘውን ማብራሪያ ይመልከቱ]

የአካል መብራት ዐይን መሆኑን ኢየሱስ አስተማረ ይሁን እንጂ ዐይን ብርሃንን አያመነጭም::[12] ብርሃን ወደ አካል የሚገባበት ነው:: ኢየሱስ ብርሃን ነው:: እርሱም ፊት ለፊታቸው ይገኛል:: ብዙ

[11] E.H. Merrill, "The Sign of Jonah," *JETS* 23/1 (1980): 23-30.

[12] የጥንቱ የግሪክና የዕብራይስጥ ግንዛቤ ዐይን ብርሃንን እንደሚያመነጭ ነው (cf. Plato, *Timaeus,* 45b-46a). ስለ ጥንቱ አመለካከት የቀረበውን ዕጥርታ D.C. Allison, "The Eye is the Lamp of the Body," *NTS* 33 (1987): 61-83 ይመልከቱ::



ሰዎች ብርሃን ይወዳሉ:: እንዲያውም በቤቱ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ብርሃን ይሰጡ ዘንድ ፋናዎችን በመቅረዝ ላይ ያስቀምጧቸዋል:: እነዚህ ሰዎች «እርሱን ለማጥፋት» ጥረት ያደርጋሉ፤ ዐይኖቻቸው የዓለምን ብርሃን ቢያዩም መጥፎዎች ስለ ሆኑ፣ አካሎቻቸው ብርሃን አላገኙም:: መጋረጃ ተጋርዶባቸዋል:: ብርሃን እንዳይገባ ጥላቸው ተዘርግቶአል:: አሁንም ሌላ ምልክት በመፈለግ ላይ በመሆናቸውና የተሰጣቸውን ብርሃን በመናቃቸው[13] ዕውርነታቸውን አጕልተው ያሳያሉ:: ዕጥር ምጥን ባለ መልኩ ኢየሱስ፣ «ዐይኖቻችሁን ግለጡ፤ በሐቅ እኔን ተመልከቱ! እንድገባ ብትፈቅዱ በውስጣችሁ አበራለሁ» አላቸው (ከኤፌ 5÷13÷14 ጋር ያነጻጽሩ):: ዐይኖቻችንን ከፍተን ብርሃን ልናገኝ እንችላለን (ቍ 36)፤ ወይም ዐይኖቻችንን ከድነን ዕውርና ጨለማ ለመሆን እንችላለን (ቍ 34):: «የማያዩ ሰዎች ዕውር የሆኑትን ያህል ዕውር የሆነ ሰው የለም::»

ኢየሱስ ክርክሩን በዚህ ደመደመ:: ሉቃስ ስለ ብርሃን በመናገር ደመደመ:: የማቴዎስ አቀራረብ የሚደመደመው ስለ ፍሬ በመናገር ነው (ማቴ 12÷33-37):: ኢየሱስ በሁለቱም ማለት በሚሰሙትና በማይሰሙት መካከል ያለውን አነሣሽ ምክንያት ልዩነቶቹን አጕልቶ በማሳየት ይደመድማል::

**§ 107**
**ስለ ፈሪሳውያንና ስለ ሕግ መምህራን የቀረበ ወዮታ**
**(ሉቃ 11÷37-54፤ ከ77 እና ከ137ሀ ጋር ያነጻጽሩ)**

ይህ ከገሊላ አገልግሎቱ ጋር የሚመሳሰል (ከቍ 102 ሀና 106 ጋር ያነጻጽሩ) በኢየሱስ ኋለኛ የይሁዳ አገልግሎቱ ሦስተኛ ሁነት ነው:: ኢየሱስ በገሊላ የፈጸመውን በዚህ ጊዜ ደግሞ በደቡቡ አገር የሚፈጽም ይመስላል:: ጊዜው እየተገባደደ በመሆኑ ፈጠን ባለ መልኩ መንቀሳቀስ አለበት::

[13] S.R. Garrett, "Lest the Light in You be Darkness". Luke 11:33-36 and the Question of Commitment," *JBL* 110/1 (1991):93-105.

ክፍል 77 ውስጥ በገሊላ ምድር በሥርዐታቸው መሠረት ስለ መንጻት ጉዳይ ከፈሪሳውያን ጋር ሲጋጭ እንመለከታለን። ማቴዎስ 15:1 እና ማርቆስ 7፥1 የኢየሩሳሌም ፈሪሳውያን በማለት ለይቶ ያመለክቷቸዋል። ስለዚህ እነዚህ ሰዎች ከዚህ ቀደም የዛቱበት ሊሆኑ ይችላሉ። ያገኙት ጥቅም ቢኖር በዚህ ጊዜ በራሳቸው የፍርድ ሸንጎ ላይ መቅረባቸው ነው።[14]

ፈሪሳውያን የቀኝ ክንፍ የሃይማኖት ሰዎች ነበሩ። በማንኛውም የሕይወታቸው ፈርጅ የብሉይ ኪዳንን መርሖች ተግባራዊ በማድረግ ከኅብረተ ሰባቸው ብልሹነት ራሳቸውን ለመለየት ጥረት የሚያደርጉ ሰዎች ነበሩ። በመጀመሪያ አነሣሽ ምክንያቶቻቸው መልካም ነበሩ። ነገር ግን ለንጽሕና ካላቸው ቅናት የተነሣ በጥቃቅን ትውፊቶች ረገድ በሕግ ላይ ሕግ ለወጡ። አለመታደል ሆነና እየራቁ በሄዱ ቍጥር ሰዎችን ዘንግተው በሥርዐት ላይ ዝንባሌ ያሳድሩ ጀመር። ይህ ድርጊት ኢየሱስ ወደሚነቅፈው ብልሹነት አመራ።

በሰንበት ደንቦች፣ በሥርዐታዊ መንጻትና በጾም ረገድ ኢየሱስ ደንባቸውን (ትውፊቶችን) ባለመከተሉ የነቀፌታቸውና የሤራቸው የዘወትር ዒላማ ሆነ፦

1. ኢየሱስ ኀጢአትን ይቅር እላለሁ ባለ ጊዜ እግዚአብሔርን የመሳደብ ያህል ነው ሲሉ ከሰሱት፤ ከማቴ 9:33 ጋር ያነጻጽሩ፤ ከማር 6:22 ጋር ያነጻጽሩ፤ ሉቃ 5፥21)።

[14] ኢየሱስ ከፈሪሳውያን ጋር የተጋፈጠ መሆኑን የሚያመለክቱ ዐሥራ ዘጠኝ ያህል ምንባቦች አሉ (ማቴ 9፥32-34፤ 12፥22-24፤ 21፥33-46፤ 22፥31-40፤ 22፥41-46፤ 23፥1-36፤ ማር 2፥15-17፤ 2፥23-26፤ 3፥1-6፤ 7፥1-8፤ 8፥11-13፤ 10፥2-9፤ 12፥13-17፤ ሉቃ 5፥17-26፤ 7፥36-50፤ 14፥1-6፤ 15፥1-7፤ 10፥14-15፤ 17፥20-21፤ 19፥37-40)። እነዚህ ክርክሮችም ከኢየሩሳሌም በ70 ዓ.ም. መውደቅ በኋላ በክርስቲያኖችና በፈሪሳውያን መካከል የቀጠለውን እሰጥ አገባ ሊያንጸባርቁ ይችላሉ (cf R.A. Wild, "The Encounter between Pharisaic and Chirstian Judaism: Some Early Gospel Evidence," *NovT* 27/2 [1985]: 105-124).



2. አዘውትሮ የኀጢአተኞች ወዳጅ በመሆኑ ናቁት (ማቴ 9፥11፤ ማር 2፥16፤ ሉቃ 5፥30፤ 15፥1)።
3. ጾምን አልፈጸመም (ሉቃ 5፥33)፣ የሰንበትን ደንቦች ሳያከብር በመቅረቱ (ማቴ 12፥2:10፤ ማር 2፥23፤ 3፥2፤ ሉቃ 6፥5-7፤ ከ13፥14 ጋር ያነጻጽሩ፤ ዮሐ 5፥10-18፤ 9፥13)፤ እጁን አልታጠበም (ማቴ 15፥1-20፤ ማር 7፥1-23፤ ሉቃ 11፥37-41) ትውፊታችንን አላከበረም በማለት ከሰሱት።
4. ለሰይጣን/በሰይጣን ኀይል (ብዔል ዜቡል) ሠርቷል በማለት ኢየሱስን ከሰሱት (ማቴ 9፥34፤ 11፥19፤ ከ12፥24 ጋር ያነጻጽሩ፤ ማር 3፥22፤ ሉቃ 11፥14)።
5. አታሏል (ከማቴ 27፥62 ጋር ያነጻጽሩ፤ ዮሐ 7፥12) በሮም መንግሥት ላይ ዐመፅ አነሣሥቶአል (ማቴ 27፥18፤ ሉቃ 23፥1-2)፤ ቤተ መቅደሱን ለማፍረስ ዝቷል በማለት (ማቴ 26፥59-61፤ 27፥39-40፤ ዮሐ 2፥19) ከሰሱት።
6. ሳምራዊና ጋኔን ያደረግህ ነህ (ዮሐ 8:48) በማለት አላገጡበት (ዮሐ 8፥48)።
7. ኢየሱስን ለማጥመድ (ሉቃ 11፥53-54)፣ ለመያዝ (ዮሐ 7፥30-32:44-45፤ 8፥20) እና ለመግደል (ማቴ 27፥62፤ ዮሐ 8፥59፤ 18፥3 የሄሮድስ ወገን ከሚባለው ክፍልና (ማር 3፥6) ከሰዱቃውያን ጋር ተባበሩ።

37ኢየሱስ ንግግሩን እንደ ጨረሰ፣ አንድ ፈሪሳዊ ከእርሱ ጋር ምግብ እንዲበላ ጋበዘው፤ እርሱም ሰብሮት ገብቶ በማእድ ተቀመጠ። ሉቃ 11፥37

ኢየሱስ ረፋዱ ላይ ምግብ ይበላ ዘንድ ተጋበዘ::[15] በኢየሱስና በፈሪሳውያን መካከል ካለው ጥላቻ አኳያ ሲታይ ይህ እንግዳ ነገር ነው:: ፈሪሳዊው ምናልባት ኢየሱስን በድብቅ ለማጥመድ ፈልጎ ይሆናል:: ፍላጎቱን በግብዣው ደበቀ:: እንዲያውም የፈሪሳውያኑ ቡድን ከጥቂት ጊዜ በኋላ በይፋ ኢየሱስን ለማጥመድ ጥረት ያደርጋል (ቍ. 53-54):: በሌላ በኩል ግን የዳስ በዓል በአይሁድ መሪዎች መካከል መለያየትን ፈጥሮአል:: ብዙዎቹ በኢየሱስ ያምናሉ፤ የቀሩት ደግሞ በእርሱ ላይ ቅን አመለካከት አላቸው (ዮሐ 7÷45-52፤ 10÷19-21፤ ከ12:42 ጋር ያነጻጽሩ):: ይህ ፈሪሳዊ ከየትኛው ወገን እንደ ሆነ ለማወቅ አንችልም:: ራሱም እንኳን አያውቅ ይሆናል::

ተጋብዞ ግብዣን መበታተን ነውር ይመስላል:: ከዚህ ቀደም የነበራቸውን ግንኙነት መሠረት በማድረግ፣ ኢየሱስ በእነዚህ ፈሪሳውያን ላይ ብርቱና ቀጥተኛ ንግግር ማድረጉ በእጅጉ ትክክል ያደርገዋል:: ከአራት ወር በኋላ፣ ከመስቀሉ በፊት በነበረው ማክሰኞ ዕለት (ማቴ. 23) ቤተ መቅደስ ውስጥ ይህንኑ ተግሣጽ በተመሳሳይ ቃላት ይደግመዋል::

ሉቃ 11÷38-41

[38]ፈሪሳዊውም ኢየሱስ ከምግብ በፊት እጁን እንዳልታጠበ ባየ ጊዜ ተደነቀ::

[39]ጌታም እንዲህ አለው፤ «አሁን እናንተ ፈሪሳውያን የጽዋውንና የወጭቱን ውጫዊ ክፍል ታጸዳላችሁ፤ ውስጣችሁ ግን በስስትና በክፋ የተሞላ ነው:: [40]እናንት ሞኞች፤ የውጪውን የፈጠረ የውስጡንም አልፈጠረምን? [41]ነገር ግን በውስጥ ያለውን ምጽዋት[a] አድርጋችሁ ስጡ፤ በዚህ ጊዜ ሁሉም ንጹሕ ይሆንላችኋል [ከማቴ 23:25-26 ጋር ያነጻጽሩ]

[a]41 *ወይም ያላችሁን*

ኢየሱስ ከመመገቡ በፊት አልታጠበም:: ይህ መታጠብ ተራ መታጠብ ሳይሆን በሥርዐታቸው መሠረት የሚደረግ ነበር:: ከዚህም በላይ የቅዱሳት መጻሕፍት ሕግ ሳይሆን የአለቆች (የሽማግሌዎች) ትውፊት ነበር:: አይሁድ ሁሉ የእጃቸውን ኀጢአት ለማስወገድ እጃቸውን ወደ ልብሳቸው እጅጌ ቀና አድርገው ከመታጠብ ይልቅ ጣቶቻቸውን ወደ ታች አድርገው እስከ ግማሹ ውሃ ካለበት ዕቃ እየተጨመረላቸው መታጠብ ነበረባቸው (ከቡትለር፣ ገጽ 239 ጋር ያነጻጽሩ):: ኢየሱስ በሥርዐታቸው መሠረት ንጹሕ ባለመሆኑ ወነጀሉት:: ጌታም በበኩሉ መንፈሳዊ ንጽሕና ስላልነበራቸው ወነጀላቸው:: በውጭ ንጹሕ ናቸው፤ በውስጥ ግን ቆሽሸዋል:: የኢየሱስ ትምህርት ግልጽና ቀላል ነው:- የውስጡን ንጹሕ አድርጉት፣ ከዚያም የውጭው ንጹሕ ይሆናል::[16]

እንዴት ነው የውስጡን ንጹሕ የምናደርገው? ሀብታችንን ለድኾች በመስጠት:: ኢየሱስ በዚህ ታላቅ ግብዣ ላይ በመገኘት፣ የፈሪሳዊው ጊዜና ገንዘብ እንዲህ ላለው የታይታ ግብዣ ከሚውል ይልቅ ለድኾች ቸርነት ተደርጎ ቢጠፋ ይሻል ነበር በማለት አስተያየቱን ሰጠ:: ይህ ብልግና ነው ብለህ የምታስብ ከሆነ፣ ኢየሱስ ቀጥሎ የተናገረውን እስከምትሰማ ድረስ ታገሥ!

ሉቃ 11÷42-44

[42]«እናንተ ፈሪሳውያን ግን ወዮላችሁ፤ ከአዝሙድና ከጤና አዳም እንዲሁም ከአትክልት ሁሉ ዐሥራት ታወጣላችሁ፤ ሆኖም ፍትሕንና እግዚአብሔርን መውደድ ቸል ትላላችሁ፤ ነገር ግን ያንን ሳትተው ይኸኛውን ማድረግ በተገባችሁ ነበር::

[43]«እናንት ፈሪሳውያን ወዮላችሁ በምኵራብ የክብር መቀመጫ፣ በገበያ መካከልም እጅ መንሣትን ትወዳላችሁና::

[15] ይህ መቆያ ምግብ የሚቀርበው ከማለዳ ጸሎት በኋላ በ4 ሰዓትና በ5 ሰዓት መካከል ነው (ሉቃ 14:12 ጋር ያነጻጽሩ)::

[16] J. Neusner, "'First Cleanse the Inside,'" *NTS* 22 (1975-76): 486-495 በሚለው ጽሑፍ ላይ ውስብስብ የሆነውን የዚህን ደንብ ሃላክ ሂካዊ ዳራ ያብራራል::

44«ሰዎች ሳያውቁ በላዩ የሚሄዱበትን የተሰወረ መቃብር ስለምትመስሉ፣ ወዮላችሁ።» [ከማቴ 23፡27 ጋር ያነጻጽሩ]

**ወዮታ ቍጥር 1፡- በጥቃቅኑ ነገር ልቆ መገኘት ዋና በሆነው ነገር ደግሞ አንሶ መገኘት፤** ፈሪሳውያን ከጓሮ አትክልታቸው እንኳን ሳይቀር ዐሥራት ለመክፈል ጠንቃቆች ነበሩ። ሥዕሉ አሳፋሪ ነገር ነው፤ አንድ ካህን ረጅም ቀሚስ ለብሶ በማጎደሩ (በመጽሐፍ መያዣው) የጸሎት መጽሐፉን እንደ ያዘ በጓሮ የሚገኘውን አዝሙድ ወይም ጤና አዳም[17] እየቈጠረ ሲታይ ምን ያህል ያሳፍራል! ማቴዎስ 23፥24 በሚገባ ገልጾታል፤ «እናንት የታወራችሁ መሪዎች፣ ትንኟን አጥርታችሁ ትጥላላችሁ፤ ግመልን ግን ትውጣላችሁ።» ዋና ዋና ጉዳዮችን ትተን ለጥቃቅን ነገሮች በመጨነቅ ብዙ ጊዜ ብቃታችንን የምናሳየው። እግዚአብሔር ከጽድቁና ከፍቅሩ የሚልቁ ሌሎች ባሕርያት የሉትም። ለዝርዝር ጉዳዮች በመጨነቅ እነዚህን ስንት ጊዜ ነው የምንዘነጋቸው? የሩቁን አቅርቦ የሚያሳየውን ቴሌስኮፕ በመዘንጋት ረቂቁን በሚያሳየው ማይክሮስኮፕ በመጠቀሙ ረገድ ፍጹም ነን።

**ወዮታ ቍጥር 2፡- ራስን ከፍ ከፍ ማድረግ፤** እነዚህ ሰዎች ስለ ሹመት በጣም ይጨነቃሉ። በሕዝቡ ዘንድ ከበሬታን ስለሚያስገኝላቸው ሹመቱን ይወዱታል። ወደፊት ያልፉ ዘንድ በሮች እንዲከፈቱላቸውና ዕቃዎች ከመንገዳቸው እንዲወገዱላቸው ይፈልጋሉ። ለክብር ቦታቸው ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፣ ካሰቡበት ለመድረስም ታጥቀው ይነሣሉ።

**ወዮታ ቍጥር 3፡- የተሰወረ መቃብር፤** አይሁዳዊ በቀላሉ ከሚረክስባቸው መንገዶች አንዱ ሬሳ መንካት ነው። ይህ መቃብርን

[17] «ጤና አዳም ሁለት ጫማ ያህል ቁመት ያለው ቁጥቋጦ ሲሆን፣ የወይን ጠጅ ለማጣፈጥ ከመጥቀሙም በላይ ለመድኀኒትነትም ያገለግል ነበር» (McGarvey, ገጽ 313)።



መርገጥንም ያካትታል (ከዘኍ 19፥16 ጋር ያነጻጽሩ)። እነዚህ ፈሪሳውያን እንደ ስውር መቃብር ሰዎችን ያረክሳሉ፤ ሕዝቡም የሃይማኖት መሪዎቻቸው የሚያረክሱ ሰዎች መሆናቸውን ሳያውቁ ከእነርሱ ጋር ድንገት ይገናኛሉ። እምነት የለሽ ካህናት ያለማመን በሽታቸውን ሳያውቁት ያሠራጫሉ። ተራዎቹ ምእመናንም በአመራራቸው ይታመናሉ፤ የመሪዎቹ ድርጊት ግን ወደ ጥፋት እንጂ ወደ ድኅነት አይመራቸውም።

45ከሕግ ዐዋቂዎች አንዱ መልሶ «መምህር ሆይ፤ እንዲህ ስትናገር እኮ እኛንም መስደብህ ነው» ሲል መለሰለት። **ሉቃ 11፥45-46**

46ኢየሱስም እንዲህ አለ፤ «እናንት ሕግ ዐዋቂዎችም ደግሞ ወዮላችሁ፤ ሰዎች ሊሸከሙ የማይችሉትን ከባድ ሸክም ታሸክማላችሁ፤ እናንተ ራሳችሁ ግን በጣታችሁ እንኳ አትነኩትም።» [ከማቴ 23፡4 ጋር ያነጻጽሩ]።

ጸሐፍት ወይም ሕግ ዐዋቂዎቹ ብዙ ጊዜ ፈሪሳውያንም ነበሩ። የልብ ሐኪሞች ስፔሽያሊስት ዶክተሮች እንደ ሆኑ ሁሉ ጸሐፍትም ልዩ ሙያ የነበራቸው ፈሪሳውያን ነበሩ። የከበሬታ ስፍራ ነበራቸው። የበላይነት የሚሰማቸው በተራው ሕዝብ ላይ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ፈሪሳውያንም ላይ ነበር። የሙሴን ሕግ መቅዳት (መገልበጥ) መተርጐምና የሚነሡ ጥያቄዎችን መመለስ የእነርሱ የሥራ ድርሻ ነው። በብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ላይ ጊዜያቸውን ያጠፉ ስለ ነበር ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚነሡ ጥያቄዎችን የሚመልሱ ሊቃውንት ነበሩ። ብዙ ጊዜ እንደሚሆነውም ይህ ዕውቀትና ሊቅነት ወደ ትዕቢት መራቸው። ኢየሱስ በእነርሱና በጸሐፍት መካከል ልዩነት ሳያደርግ ገሠጻቸው። ይህም ወደ እውነት በጣም የቀረበ ነው። ይህ ጸሐፊ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ልዩነት እንዲያሳይ ነው ኢየሱስን የጠየቀው። ኢየሱስ ጥያቄን እንዲሁ አያልፍም ተጠንቀቅ።

**ወዮታ ቍጥር 4:- ለሸክም የሚያስቸግሩ ሸክሞችን መጫን፤** ሕጉን በደንብ ስለሚያውቁት በተራው ሕዝብ ላይ የሚጭኑና ሕጉን የሚያስከብሩ እነርሱ ናቸው:: የሕጉ ልዩ ባለሞያ በመሆናቸው ለራሳቸው የማምለጫ መንገድ ለመፈለግ ይችላሉ:: የሌሎችን ሸክም ለማቃለል ግን መጠነኛ ጥረት እንኳ አያደርጉም:: ሉቃስ «ጣት አያነሡም» በማለት ሕክምናዊ አገላለጽን ተጠቀመ:: የታመመ አካልን በቀስታ መዳሰስ ወይም የልብ ትርታን ለማወቅ መንካት ማለት ነው:: እነዚህ ጸሐፍት በሕዝቡ ላይ ያለርኅራኄ የሚጭኑትን ጭነት በዳሰሳ እንኳን አይነኩም::

**ሉቃ 11፥47-51**

47«አባቶቻችሁ የገደሏቸውን የነቢያትን መቃብር ስለምታበጁ፣ ወዮላችሁ፤ እንግዲህ የአባቶቻችሁን ሥራ የምታጸኑ ምስክሮች ናችሁ፤ እነርሱ ነቢያትን ገደሉ፤ እናንተም መቃብራቸውን ታበጃላችሁ:: 49ስለዚህም የእግዚአብሔር ጥበብ እንዲህ አለች፤ 'ነቢያትንና ሐዋርያትን እልከባቸኋለሁ፤ እነርሱ አንዳንዶቹን ይገድላሉ፤ ሌሎችንም ያሳድዳሉ::' 50ስለዚህ ይህ ትውልድ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ስለ ፈሰሰው፣ ስለነቢያት ሁሉ ደም ተጠያቂ ነው፤ 51ከአቤል ደም ጀምሮ፣ በመሠዊያውና በቤተ መቅደሱ መካከል እስከ ፈሰሰው እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ ይፈለግበታል፤ አዎን እላችኋለሁ፤ ይህ ትውልድ ስለዚህ ተጠያቂ ነው» ከማቴ 23፥29-36 ጋር ያነጻጽሩ::

**ወዮታ ቍጥር 5:- ነቢያትን መግደል፤** ልጅ መሆን የአባትህን ባሕ‹› ሥራና ፍልስፍና መውረስን ያመለክታል:: አባቶቻቸው ብዙዎትን ነቢያት እንደ ደበደቡና እንደ ገደሉ እነዚህ ጸሐፍትም ተመሳሳይ ድርጊት ይፈጽሙ ነበር (ከ1ነገ 19፥14፤ ከኤር 7፥25-26፤ ከሚል 3፥10 ጋር ያነጻጽሩ):: በኢየሱስም ላይ ያንኑ አባቶቻቸው ያስተማሯቸውን እውነትን መጥላትና ልበ ደንደናነትን ያሳያሉ::

«የነቢያት ገዳዮች አይደለንም:: እንዲያውም ለስማቸው ማስታወሻ ብለን የሚያማምሩ መቃብሮችን በመሥራት እያከበርናቸው ነው» ይላሉ:: ኢየሱስ ግን እነዚህ የሚያማምሩ መቃብሮች የአባቶቻቸው ሥራ ቀጣይ ድርጊት እንጂ የዚያ ተቃራኒ አይደለም ይላል::

«እግዚአብሔር በጥበቡ እንዲህ አለ» የሚሉት ቃላት ብሉይ ኪዳን ውስጥ አይገኙም:: ኢየሱስ ከቅዱስ መጽሐፍ መቅጠሱ ሳይሆን፣ ከራሱ የሆነውን መግለጡ ነው:: አብ በግሉ ከነገረው ጋር በማዛመድ ላይ ነበር:: ይህ ትውልድ የነቢያት ሁሉ ፍጻሜ የሆነውን ኢየሱስን በመግደሉ በእርሱና በሌሎቹም ደም ተጠያቂ ነው::[18] ኢየሱስን በመግደል አባቶቻቸው ያካሄዱትን ገድያና ድብደባ ያጠቃልላሉ:: ጭካኔ የተሞላበት ድርጊታቸው በእግዚአብሔር ላይ ያደረጉት የነበረ ዐመፅ ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሱን ያመለክታል::

**ሉቃ 11፥52-54**

52«እናንተ ሕግ ዐዋቂዎች ወዮላችሁ፤ የዕውቀትን መክፈቻ ነጥቃችሁ ወስዳችኋልና፤ እናንተ ራሳችሁ አልገባችሁበትም፤ የሚገቡትንም ከልክላችኋል::»

53ኢየሱስ ከዚያ ከወጣ በኋላ፣ ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ክፉኛ ይቃወሙትና በጥያቄም ያጥከቡት ጀመር፤ 54ከአፉ በሚወጣውም ቃል ሊያጠምዱት ያደቡ ነበር::

**ወዮታ ቍጥር 6:- የተደበቁ ቍልፎች፤** ጸሐፍት ሰዎች ወደ መንግሥተ ሰማይ እንዲገቡ የሚያበቃ የዕውቀት ቍልፍ አላቸው:: በሌላ አባባል የቅዱሳት መጻሕፍትን ትክክለኛ ትርጓሜ ያውቃሉ

---

[18] ቀኖና በሆኑት በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ቅደም ተከተል መሠረት (በማቴ 23፥33-36፤ በ137ሀ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ):: አቤል የመጀመሪያውን ሰማዕት ይወክላል:: ዘካርያስም የመጨረሻውን የብሉይ ኪዳን ሰማዕት ይወክላል:: ወይም እኛ «ከዘፍጥረት እስከ ዮሐንስ ራእይ» እንደምንለው ዐይነት ነው:: ወይም ለእኛ ነገሩን ግልጽ ለማደረግ፣ «ሁሉንም ነቢያት ከሀ-ፐ» እንደምንለው ዓይነት::

(ወይም ማወቅ ነበረባቸው):: ነገር ግን ሌሎች እንዳይገቡበት አደረጉ፤ ወይም ራሳቸው ሳይገቡበት ደብቀው አስቀሩት::

ኢየሱስ የፈሪሳውያንን ዐበይት ችግሮች ለይቶ አመልክቷል:: እነዚህ ስድስት መሰናክሎች ከዛሬዎቹ ካህናት ጋር ካሉት የተለዩ አይደሉም:: አንድ ሰው «የሥራ ተግዳሮቶች»[19] ብሎ ይጠራቸው ይሆናል::

ኢየሱስ ከነበሩበት ቤት ወጥቶ ሲሄድ ፈሪሳውያንና ጸሐፍት ተከተሉት:: እርሱን በማዋረድም የራሳቸውን አስተዋይነትና ተቀባይነት ለመከላከል ጥረት አደረጉ:: «ደምበኛ ትምህርትኮ የለውም:: በቀላሉ የሚረታ መሆን አለበት» ተባባሉ:: ኢየሱስ ግን ማስተዋላቸውንና ቅድመ ግንዛቤያቸውን ከንቱ እያደረገ በየትኛውም ደረጃ አሸነፋቸው::

**§ 108 ሀ**
**ለደቀ መዛሙርቱ ማስጠንቀቂያዎችና ተስፋዎች**
**(ሉቃ 12፥1-2)**

እንደገና በገሊላ አገልግሎቱ ውስጥ የሉቃስ ቃሎች በማቴዎስ (እና በማርቆስ) ውስጥ እንደሚገኙ ልብ እንላለን:: ማቴዎስና ሉቃስ የየግላቸውን የታሪክ መስመር ግልጽ ለማድረግ አንዳንድ ታሪኮችን አብረው አቃንተዋቸዋል ማለት ነው:: ነገር ግን የሚያስኬደው አገላለጽ ኢየሱስ ብዙ ተመሳሳይ ነገሮችን ቢያንስ ሁለት ጊዜ ተናግሯል የሚለው ነው:: ስለዚህ አንድ ዐይነት የሆኑት ቃላት በገሊላና በይሁዳ የተነገረውን ዋና ሐሳብ ሊገልጹ ይችላሉ::

**ሉቃ 12፡**

በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች አንዱ ሌላውን እስኪረግጥ ድረስ እየተጋፉ በተሰበሰቡ ጊዜ በመጀመሪያ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ሲል ይናገር ጀመር «ከፈሪሳውያን እርሾ ተጠንቀቁ፤ እርሱም ግብዝነት ነው»::

[19] Liefeld (p 956) እንደሚከተለው ለይቶ ያመለክታቸዋል:- ግብዝነት (ቁ. 39-41)፣ ኢሚዛናዊነት (ቁ. 42)፣ ታይታ (ቁ. 43) የማይቻሉ ጥያቄዎች (ቁ. 46) አለመቻቻል (ቁ. 47-51)፣ ግለኝነት (ቁ. 52)::

ኢየሱስ ፈሪሳዊው ቤት ውስጥ ድምፁን ከፍ አድርጎ የመናገሩ ዜና ተሠራጭቶአል (§ 107):: ብዙ ጊዜ ማኅበረ ሰቡ ተቀምጦ እነዚህን ግብግቦች እንዲከታተል ይፈቀድለት ነበር:: ሕዝቡ የዚህን ታላቅ የክርክር ፍልሚያ ዜና በሰሙ ጊዜ መሰብሰባቸው አያስደንቅም:: ይህን ሕዝብ ለመግለጽ ሉቃስ የተጠቀመበት ሐረግ ሐዋርያት ሥራ 21፡20 ውስጥ ይገኛል:: (እዚያ ላይ ክርስቶስን ስለ ተቀበሉ ብዙ ሺህ አይሁዳውያን ይጠቅሳል) ይህ የሕዝብ ቊጥር በወንጌላት ውስጥ ትልቁ ሳይሆን አይቀርም:: እነዚህ ሰዎች በመጀመሪያው ረድፍ ባለው ሥፍራ ለመቀመጥ ይሽቀዳደሙ ነበር::

ኢየሱስ ከፈሪሳውያን እርሾ እንዲጠነቀቁ በመጀመሪያ ለቅርብ ደቀ መዛሙርቱ ተናገረ:: ከዚህ ቀደም በገሊላ ባጋጠመው ተመሳሳይ ተቃውሞ ጊዜ የተጠቀመባቸውን ተመሳሳይ ቃሎች አሁንም ተጠመቀ (ማቴ 16፥5-6፤ ማር 8፥14-15፤ ቊ 81ሀ):: ይህ ተጽዕኖው ሰፊ የሆነ እርሾ የፈሪሳውያን ግብዝነት[20] ነው:: Mc Garvey (ገጽ 316) ግብዝነት «መጥፎ ሰው መልካሙን ሰው ከመፍራቱ የተነሣ መጥፎነቱን እንዲደብቅ ያደርገዋል፤ መልካሙ ሰው ደግሞ መጥፎውን ሰው ከመፍራቱ የተነሣ መልካምነቱን እንዲደብቅ ያደርገዋል» ይላል::

[20] C.L. Mitton ሁለት ዐይነት እርሾዎች አሉ ይላል:: ሁለቱም በሊጥ ውስጥ ይገኛሉ:: ከፊሉ ለሚቀጥለው ጋገራ እንዲያገለግል ተለይቶ በመቀመጥ እንዳይበላሽ ይደረግ ነበር:: በሚብላላበትና ከአዲሱ ሊጥ ጋር በሚደባለቅበት ጊዜ ሊጡ ኩፍ እንዲል ያደርገዋል:: ያለ እርሾ የተጋገረ የቂጣ በዓል በየዓመቱ በሚከበርበት ጊዜ ሕዝቡ እርሾአቸውን ያስወግዳሉ:: ይህ የእርሾ «መታደስ» በሽታ እንዳይሠራጭ ይከለክላል:: ይህን ልምድ መሠረት በማድረግም እርሾ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ዘይቤአዊ በሆነ ስልት በአራት መንገድ ተወክሎአል:- (ሀ) የፈሪሳውያን፣ የሰዱቃውያንና የሄሮድስ እርሾ (ማቴ 8፥15፤ 16፥6፤ ሉቃ 12፥1):: (2) የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ እርሾ ታድጋለች (ማቴ 13፥33፤ ሉቃ 13፥21):: (3) «ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ ያቦካል (ገላ 5፥9፤ 1ቆሮ 5፥5):: (4) የክርስቲያን ሕይወት መታደስ (1ቆሮ 5፥6-7):: C.L. Mitton. "Leaven." *ExpT* (1972-73): 339-343 ይመልከቱ::

2«የማይገለጥ የተሸፈነ፣ የማይታወቅ የተሰወረ
ምንም የለም። 3ስለዚህ በጨለማ ያወራችሁት ሁሉ
በብርሃን ይሰማል፤ በእልፍኝም ውስጥ በጆሮ
ያንሾካሾካችሁት በሰገነት ይነገራል።

ሉቃ 12፥2-9

4«ወዳጆች ሆይ፤ እላችኋለሁ ሥጋን የሚገድሉትን፣ ከዚያ ወዲያ ግን
ምንም ማድረግ የማይችሉትን አትፍሩ። 5ነገር ግን መፍራት የሚገባችሁን
አሳያችኋለሁ፤ ከገደለ በኋላ ወደ ገሃነም ለመጣል ሥልጣን ያለውን እርሱን ፍሩት፤
አዎን፤ እርሱን ፍሩት እላችኋለሁ። 6አምስት ድንቢጦች በሁለት ሳንቲም[ሐ] ይሸጡ
የለምን? ይሁን እንጂ ከእነርሱ አንዷ እንኳ በእግዚአብሔር ዘንድ አትዘነጋም።
7የእናንተ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳ የተቈጠረ ነው፤ እንግዲህ አትፍሩ፤ ከብዙ
ድንቢጦች የበለጠ ዋጋ አላችሁ።

8«እላችኋለሁ፤ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ የሰው ልጅ ደግሞ
በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ይመሰክርለታል። 9በሰው ፊት የሚክደኝም
በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ይካዳል።»

*ሐ6 ግሪኩ ሁለት ሲሳሪያ ይባል*

[ቍ. 2-9 = ማቴ 10፥26-33፤ በቍጥር 70ለ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ]

ቍጥር 2-3 ማቴዎስ 10፥26-27 ውስጥ ካለው ክፍል ጋር ተመሳሳይ ነው። ዳራው ግን ይለያል። በማቴዎስ ውስጥ ኢየሱስ የሚለው «ተቃውሞና ስደት በመጣ ጊዜ ስለ እኔ ለመናገር አትፍሩ» ነው። ሐዋርያት ኢየሱስ በግል የነገራቸውን አሁን በአደባባይ መስበክ ቢኖርባቸው ነው። በዚህ በሉቃስ ውስጥ የዐረፍተ ነገሩ ባለቤት «ድብቅ ዐደራዎቻችን» የሚለው ነው። በሉቃስ 11 ውስጥ ኢየሱስን ራት የጋበዘው ፈሪሳዊ ወዳጅ ይመስላል። ሆኖም ድብቅ ዓላማዎች በቍ. 53-54 ውስጥ ጉልሕ ሆነው ታዩ። በአራት ወር ጊዜ ውስጥ ፈሪሳውያን



ኢየሱስን ለመግደል ከሰዱቃውያንና ከሄሮድሳውያን ጋር ግንባር ይፈጥራሉ። ነገር ግን ሕዝቡ ኢየሱስን ስለሚወዱት በአደባባይ ማክበር አለባቸው። የግል ጥላቻቸውና ነቀፌታቸው ግን ለረጅም ጊዜ አይደበቅም።

ኢየሱስ እርሱን ለመግደል ስለማሤራቸው ያውቃል። ያ ግን የሚያስፈራ አይደለም። ፈሪሳውያን ማድረግ የሚችሉት ነገር አካልን መግደል ነው። ዘላለማዊነት ያለው አሁንም በአብ ሥልጣን ሥር ነው። ጥያቄው ግን «የምትፈራው ሕይወትህን የሚያጠፋውን ጥይት ነውን፣ ወይስ ወደ በገሃነም የሚጥልህን እግዚአብሔር?»[21] የሚለው ነው። ደቀ መዛሙርት ያን ጥያቄ ለራሳቸው ሲሉ በፍጥነት መመለስ ነበረባቸው። ውሳኔ ላይ ይደርሱ ዘንድ ለመርዳት እግዚአብሔር አብዝቶ እንደሚወዳቸው ኢየሱስ አስታወሰው። እግዚአብሔር የራሳቸውን ጠጉር እንኳን ቈጥሮአል። እግዚአብሔር ድንቢጦችን የሚጠብቅ ከሆነ፣ ውድ ልጆቹን ምን ያህል ይንከባከባቸው ይሆን? የተሰጠው ተስፋ ይህ ነው። በግልባጩ ግን ማስጠንቀቂያ አለ:- ሕይወትን ለሞት በሚያደርስ ተቃውሞ የተነሣ እንኳ በምድር ላይ ኢየሱስን ብትክዳ፣ በመንግሥተ ሰማይ ይክድሃል። ማጠቃለያውም:- የሚጠሉህን ሰዎች አትፍራ፤ ይልቅስ የሚወድህን አብን ፍራ።

10«በሰው ልጅ ላይ የማቃለል ቃል የሚሰነዝር
ሁሉ ይሰረይለታል፤ መንፈስ ቅዱስን የሚሳደብ ግን
አይሰረይለትም።

ሉቃ 12፥10-12

---

[21] H.K. Moulton, "Luke 12:5," *BT* 25 (1974): 246-247) በሚለው ላይ ድንቅ ሐሳብ ያቀርባል። «እርሱን» (እግዚአብሔርን ያመለክታል፤ RSV - Revised Standerd Version) በግሪኩ ቅጅ ላይ አይገኝም። ስለዚህ ይህ ጥቅስ እንደሚከተለው ሊጻፍ ይችላል፤ «እነርሱ ከገደሉ በኋላ ወደ ገሃነም እሳት የሚጥላችሁን ፍሩ» በሌላ አባባል ለግድያው ኀላፊ የሚሆነው እግዚአብሔር ሳይሆን ክፉ ሰዎች ናቸው። *«አፖክቴኖ - apokteino -* እገላለሁ የሚለው ግስ 74 ጊዜ የተጠቀሰ ሲሆን፣ ዮሐንስ ራእይ 2፥23 እና 19፥21» (ገጽ 247) ቀጥተኛ ባልሆነ መልኩ ካልሆነ በቀር እግዚአብሔር የዐረፍተ ነገሩ ባለቤት ሆኖ በእነዚህ ሁሉ ክንውኖች አንድ ጊዜ እንኳን አልቀረበም።

[11]«ሰዎች ይዘው ወደ ምኵራብ ወደ ገዥዎችና ወደ ባለ ሥልጣናት ባቀረቧችሁ ጊዜ እንዴት ወይም ምን እንደምትመልሱ አትጨነቁ፤ [12]በዚያ ሰዓት መንፈስ ቅዱስ መናገር የሚገባችሁን ያስተምራችኋልና::»

[ቍ. 10 = ማቴ 12÷31-32፤ ማር 3÷28-30፤ ቍ. 61 ውስጥ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ]
[ቍ. 11-12 = ማቴ 10÷18-20 (ከማር 13÷11 እና ከሉቃ 21÷14-15 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ቍ. 70ለ ውስጥ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ]

አሁንም የምንናገረው ሚናን ስለ መምረጥ ነው:: ኢየሱስ ሌላ ማስጠንቀቂያና ሌላ ተስፋ ይሰጣል:: ማስጠንቀቂያው:- ኢየሱስን በመቃወም የምትናገር ከሆንክ በእግዚአብሔር ላይ የስድብ ቃል ማሰማትህ ነው:: ደግነቱ ይህ ይቅር የሚባል ኀጢአት ነው:: አንድ ሰው ትምህርትን በተሳሳተ መንገድ የሚረዳ መሆኑ ግንዛቤ ውስጥ ይገባል:: ይህ ሰዎች ሊገነዘቡት የሚቻላቸው ፅንሰ ሐሳብ አይደለምና:: ችግሩ ግን ኢየሱስን መቃወማቸው ሳይሆን፣ በምልክቶችና ድንቅ ነገሮች የኢየሱስን ሥራ ያከበረውን መንፈስ ቅዱስን መቃወማቸው ነው:: አሁን 11÷14-15 ውስጥ ወደ ተገለጠው እርኩስ መንፈስ እንመለስላን:: አንዳንዶች እንዴት ኢየሱስ ታምር የሠራው በብዔዕል ዜቡል ነው እንዳሉ አስታውሱ:: የኢየሱስ ሥራ በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ተከናውኖ ሳለ፣ በክፉ መንፈስ ኀይል ነው የተከናወነው አሉ:: መንፈስ ቅዱስ ስሜቱ ስለ ተጐዳ የሰደበውን ሰው ይቅር ለማለት አልፈቀደም ማለት አይደለም:: ይልቁን እነዚህ ሰዎች ኢየሱስንና ስለ እርሱ የሚናገሩትን ቅዱሳት መጻሕፍት አንቀበልም ብለዋል:: በተስፋ ሰንሰለታቸው ላይ የመጨረሻው ቀለበት መንፈስ ቅዱስ ነው:: እርሱን አንቀበልም ካሉ እጅግ እርቀዋል::



ስለዚህ ፈሪሳውያን የኢየሱስና የመንፈስ ቅዱስ ተቃዋሚዎች ሆነው ተሰልፈዋል:: በሌላ አንፃር ግን ኢየሱስን ለመከተል ዝግጁ የሆኑ ደቀ መዛሙርት ነበሩ:: ይህን ካደረጉ የተርብ ቀፎ ወደአለበት ሥፍራ በመግባት ላይ ናቸው ማለት ነው:: በኢየሱስ ላይ የደረሰው ብርቱ ተቃውሞ በእነርሱም ላይ ይደርሳል:: ታሥረው ወደ ሃይማኖት መሪዎችና ገገሮች ፊት ለፍርድ ይቀርባሉ:: እንዲያ ያለውን ፍጥጫ ለመቋቋም ገና አልተዘጋጁም:: ለዚህ ነው እንዲህ የሚለው ተስፋ የተሰጣቸው:- «አትጨነቁ፤ መንፈስ ቅዱስ ጣልቃ ይገባል፤ በትክክለኛ ውም ወቅት ተገቢውን ቃል ይሰጣችኋል::»

### § 108ለ
### በሀብትና በጭንቀት ላይ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ
### (ሉቃ 12÷13-34)

[13]ከሕዝቡም መካከል አንድ ሰው «መምህር ሆይ፤ ወንድሜ ውርስ እንዲያካፍለኝ ንገረው» አለው:: [14]ኢየሱስም «አንተ ሰው፤ ከእናንተ በላይ ፈራጅ ወይም ዳኛ ያደረገኝ ማነው» አለው:: [15]ደግሞም፣ «የሰው ሕይወቱ በሀብቱ ብዛት የተመሠረተ ስላልሆነ፣ ተጠንቀቁ፤ ከስግብግብነትም ሁሉ ራሳችሁንም ጠብቁ»::

የተከበሩ መምህሩን ስለ ማኅበራዊ ጉዳይ ምክር መጠየቃቸው የተለመደ ነበር:: እንዲያውም አይሁድ ማኅበራዊውንና ሃይማኖታዊውን ጉዳይ አልለዩም:: ኢየሱስ መደበኛ በሆነ መልኩ ሃይማኖታዊ ወይም ፖለቲካዊ የሆነው መዋቅር አካል ባለመሆኑ፣ ሰውየው ለወንድሙ የሚገባውን ውርስ ይሰጥ ዘንድ ለማዘዝ ሕጋዊ ሥልጣን አልነበረውም:: ይሁን እንጂ ኢየሱስ ሁለቱም ሥልጣን ከእግዚአብሔር ተሰጥቶታል፤ በሕዝቡ ዘንድም ተቀባይነት አለው:: የሰውዬው ወንድም ይከፍል ዘንድ ሊያስገድደው ይችል ነበር:: ያ ግን ያገልግሎቱን አቅጣጫ ያስት ነበር::

ኢየሱስ ስለ ገንዘብ ወይም ስለ ማኅበራዊ ፍትሕ ግድ የሌለው ሰው አልነበረም:: እነዚህ ነገሮች በመሲሐዊው አገልግሎቱ ላይ ቀዳሚ ስፍራ እንዲኖቸው ግን ፈቃደኛ አይደለም:: የጥያቄ ናዳ

የሚያስከትልበትንና ባለፈው እንደ ታየውም የፖለቲካ መሲሕ ተደርጎ[22] በአጉል መልኩ እንዲታይ የሚያደርገውን «ጉዳዩ» ለማየት ፈቃደኛ አይደለም።

ክፉ ሐሳብ ዐዝሎ በነበረው የሰውየው ዓላማ ላይ ነው የተናገረው። ውርስን በተመለከተ ቍልጭ ያሉ ሕጎች ነበሩ። ሰውየው ፍርድ ፊት የሚቀርብ ጉዳይ ቢኖረው ኖሮ፣ በተገቢው መንገድ ፍትሕ ያገኝበት ነበር። በዚህ ፈንታ የዐመፅ መንፈስ ያለበት ጥያቄ በማቅረብ የራሱ ያልሆነን ገንዘብ ለመውሰድ የፈለገ ይመስላል። ለታላቅ ወንድም እግዚአብሔር የሰጠውን ዕጥፍ የበኵር ድርሻ የሚቃወም ታናሽ ወንድም ሳይሆን አይቀርም።

ስስት ወይም ስግብግብነት ቃል በቃል ሲታዩ፣ «ብዙ ለማጋበስ መመኘት» ነው። ብዙ ለማጋበስ ሲባል በቃኝን የማያውቅ ፍላጎት። ሊኖሩን ይገባል ከሚል ሐሳብ በመነሣት በብልጭልጭና ጥቃቅን ቍሳቁሶች ቤታችንን ያጠባበብን ሰዎች ምን ያህል ልባችን ሊነካ ይገባል? ኢየሱስ እንደሚለው የሕይወት ትርጕም የኛ ያደረግነውን ንብረት ሁሉ ያካተተ ወይም ባለን ነገር የተመሠረተ አይደለም፤ ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት ላይ እንጂ።

**ሉቃ 12፥16-21**

16ቀጥሎም እንዲህ ሲል ምሳሌ ነገራቸው፤ «ዕርሻው እጅግ ፍሬያማ የሆነችለት አንድ ሀብታም ነበረ፤ 17ይህም ሰው፣ ምርቴን የማከማችበት ስፍራ ስለሌለኝ ምን ላድርግ፤ ብሎ በልቡ አሰበ። 18«እንዲህም አለ፤ እንደዚህ አደርጋለሁ፤ ያሉኝን ጐተራዎች አፈርስና ሌሎች ሰፋ ያሉ ጐተራዎች እሠራለሁ፤ በዚያም ምርቴንና ንብረቴንም ሁሉ አከማቻለሁ፤ 19ነፍሴንም «ነፍሴ ሆይ፤ ለብዙ ዘመን የሚበቃሽ ሀብት አከማችቼልሻለሁ፤ እንግዲህ ዕረፊ፤ ብዪ፤ ጠጪ፤ ደስም ይበልሽ» እላታለሁ።

[22] ከT. Gorringe, "A Zealot Option Rejected? Luke 12:13-14," *ExpT* 98 (1986-87): 267-270 ጋር ያነጻጽሩ።



20እግዚአብሔር ግን፣ አንተ ሞኝ፤ ነፍስህን በዚህች ሌሊት ከአንተ ሊወስዱ ይፈልጓታል፤ እንግዲህ፣ ለራስህ ያከማቸኸው ለማን ይሆናል? አለው።

21«ስለዚህ ለራሱ ሀብት የሚያከማች፣ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ሀብታም ያልሆነ ሰው መጨረሻው ይኸው ነው።»

በጥንቃቄ የሚያቅዱ፣ በጥበብ የሚሠሩ፣ በብልኀትም የሚያከማቹ፣ መንፈሳዊ ነገሮችን ግን የማያከማቹ ሰዎች እንዲህ ያሉት ናቸው። በወቅቱ ባለው ሀብት ራሱን በምቾት ሊያኖር ይችላል (ቍ. 19)፤ እግዚአብሔርም ነፍሱን ይፈልጋታል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ያለውን ሰው ሞኝ ይለዋል። ማሰብ የማይችል ሰው ነው ለማለት ሳይሆን፣ የሕይወት ቅደም ተከተሉ ተዘበራርቆበታል ማለት ነው። ብገንዘብ ዋስትና ላይ ከማዋል ይልቅ በዘላለም ላይ ማዋል ይኖርብናል።

ሰውየው ሲሞት በጐተራዎቹ ያከማቸው ምርት ሁሉ የወራሾቹ ይሆናል። ሀብቱ በአገባቡ ስለ መያዙ ወይም ስለ መባከኑ ማን ያውቃል? ብዙ ሀብት በወራሹ ግድየለሽ አያያዝ ምክንያት እንዳልነበረ ሆኖአል። መጽሐፈ መክብብ 2፥18-19 ውስጥ እንዲህ ይላል፤ «ከፀሐይ በታች የደከምሁበትን ነገር ሁሉ ጠላሁት፤ ከኋላዬ ለሚመጣው የግድ እተውለታለሁና። 19እርሱ ጠቢብ ወይም ሞኝ ይሆን እንደ ሆነ ማን ያውቃል? ሆኖም ከፀሐይ በታች ድካሜንና ችሎታዬን ባፈሰስሁበት ሥራ ሁሉ ላይ ባለቤት ይሆንበታል፤ ይህም ደግሞ ከንቱ ነው።»[23] የምድራዊው ልፋታችን ጥራት ፊት ለፊቱ ባለው የመቃብር ድንጋይ ላይ በግልጽ ይታያል።

[23] ይህ ዐይነቱ ተመሳሳይ ሐሳብ የቤን ሲራና የሰኔካ ጥበብ በተሰኘው በመጽሐፈ ሄኖክ ላይ ይገኛል። ይህ ደግሞ ከዚህ ቀደም ያልታየ አዲስ ሐሳብህ አይደለም፤ ከStacey, "Lk 12:13-31: The Parable of the Rich Fool," *RevExp* 94/2 (1997): 285-292 ጋር ያነጻጽሩ።

ሉቃ 12፥22-32

22ከዚያም ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ
አለ፤ «ስለዚህ እላችኋለሁ፣ ስለ ሕይወታችሁ ምን
እንደምትበሉ፣ ወይም ስለ ሰውነታችሁ ምን
እንደምትለብሱ አትጨነቁ፤
23ሕይወት ከምግብ፣ ሰውነትም ከልብስ ይበልጣልና:: 24ቁራዎችን ተመልከቱ፤
አይዘሩም፤ አያጭዱም፤ ማከማቻ ወይም ጐተራ የላቸውም፤ እግዚአብሔር ግን
ይመግባቸዋል:: እናንተማ ከወፎች እጅግ ትበልጡ የለምን? 25ስለመሆኑ ከእናንተ
ተጨንቆ በዕድሜው ላይ አንዲት ደቂቃ መጨመር የሚችል ማነው?[ሠ] 26እንግዲህ
ቀላሉን ነገር እንኳ ማድረግ የማትችሉ ከሆነ፣ ስለ ሌላው ነገር ለምን ትጨነቃላችሁ?
27«አበቦች እንዴት እንደሚያድጉ ተመልከቱ፤ አይለፉም፤
አይፈትሉም፤ ነገር ግን እላችኋለሁ፤ ሰሎሞን እንኳ በዚያ ሁሉ ክብሩ ከእነርሱ እንደ
አንዱ እንኳ አልለበሰም:: 28እንግዲህ እግዚአብሔር ዛሬ ታይቶ ነገ ወደ እሳት
የሚጣለውን የሜዳ ሣር እንዲህ የሚያለብስ ከሆነ፣ እናንተ እምነት የጐደላችሁ፣
እናንተንማ እንዴት አብልጦ አያለብሳችሁም:: 29ስለዚህ ምን እንደምትበሉና ምን
እንደምትጠጡ በመሻት ልባችሁ አይጨነቅ፤ 30ይህንማ በዓለም ያለ ሕዝብ ሁሉ
ይፈልጋል፤ አባታችሁ እኮ ይህ ሁሉ እንደሚያስፈልጋችሁ ያውቃል:: 31ይልቁንስ
የእግዚአብሔርን መንግሥት ፈልጉ፤ ይህም ሁሉ በተጨማሪ ይሰጣችኋል::
32«እናንተ አነስተኛ መንጋ የሆናችሁ መንግሥትን ሊሰጣችሁ የአባታችሁ
መልካም ፈቃድ ነውና አትፍሩ፤»

*[ሠ]25 ወይም በቁመት ላይ አንድ ክንድ*

[ቍ. 22-32 = ማቴ 6፥25-34 በቍ. 54ሰ ውስጥ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ]::

ሕዝቡ ዳር ሆኖ እንዲያዳምጥ ተፈቅዶለታል፤ የኢየሱስ ቃል የታለመው ግን ለደቀ መዛሙርቱ ነበር:: ለጥቂት ጊዜ ከእርሱ ጋር የነበሩት ይህን ስብከት[24] ቀደም ሲል ሰምተውታል:: ከጥቂት ልዩነቶች

[24] የማቴዎስ 6፥25-34 እና የሉቃስ 12፥22-34 ክፍል በቃላት ረገድ ተመሳስሎ መገኘት፣ ቃላቱን በመለዋወጥ ብቻ አንዳቸው የሌላቸውን ገልብጠዋል



በቀር ቃሎቹና መልእክቱ ከተራራው ስብከት፣ ማለት ከማቴዎስ 6፡25-34 ጋር ተመሳሳይ ናቸው::[25] በቀላሉ ሲገለጽ፣ መጨነቅ ያለብን ስለ ሀብት ሳይሆን ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ነው::

ለውርስ ክርክሩ መትፍትሄ እንዲያስገኝለት ኢየሱስን የጠየቀው ወጣት መኖር ለሌለብን (መጨነቅ ለሌለብን) ጉዳይ ጥሩ ምሳሌ ነው:: የሁለቱም ሐሳብ የተጠመደው በእግዚአብሔር መንግሥት ላይ ሳይሆን በሀብት ላይ ነበር:: ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ «ስለ ሀብት

ማለት አይደለም:: (በማቴዎስ አቀነባበር መሠረት የሉቃስ 12፡22-31፤ የሉቃስ 12፥32-34ን ይከተላሉ):: የኢየሱስ ቃሎች በቃል ተጠንተው መጠነኛ ለውጥ ወይም ምንም ለውጥ ሳይደረግባቸው በቃል ከአንዱ ወደ ሌላው ሳይተላለፉ አልቀረም:: ከዚያም ማቴዎስና ሉቃስ እነዚህን ቃሎች በጽሑፍ ላይ አሰፈሯቸው:: ግን በሁለት የተለያዩ ስብከቶች ውስጥ ይገኛሉ:: ይህ የሚያስደንቅ አይደለም:: በመጀመሪያ ደረጃ ኢየሱስ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ የሚያስተምር ሰባኪ ሲሆን ገንዘብ ደግሞ በተደጋጋሚ መነገር ያለበት ርእሰ ጉዳይ ነበር:: ስለዚህ ኢየሱስ እነዚህን ጉዳዮች በተለያዩ ወቅቶች ተናግሮአቸዋል:: ሁለተኛ፤ ሁለቱም ስብከቶች በጣም አጫጭር ስለሆኑ የኢየሱስ ሙሉ ስብከት ቃል በቃል በጽሑፍ ላይ ሰፍሮአል ለማለት አይቻልም:: ስለዚህ ኢየሱስ በሁለት የተለያዩ ጊዜያት ከተናገራቸው ውስጥ ትክክለኛ የሆነውን ዕጥርታ (በዐጭሩ የቀረበ) ለማቅረብ ሁለቱም ምንባቦች ተመሳሳይ ቃላትን ተጠቅመዋል::

[25] ቀጥሎ ያሉት በማቴዎስና በሉቃስ መካከል የተመለከቱት መለስተኛ ለውጦች ናቸው:-

1. በእንግሊዝኛው ትርጉም ግልጽ ሆኖ እንደሚታየው ሉቃስ «ተመልከቱ» በሚለው ቃል ከመጠቀም ይልቅ «አስተውሉ» Consider (ቍ. 24) ብሏል:: ለሉቃስ ይህ ከዐይን ገረፍታ በላይ ነው:: እግዚአብሔር ሰዎችን ከወፎች ይበልጥ እንደሚንከባከባቸው ለማስተዋል ጥሞናዊ አስተንትኖን ይጠይቃል::
2. ሉቃስ «ወፎች» ከሚለው ቃል ይልቅ «ቁራዎች» በማለት ተጠቅሟል (24):: በብሉይ ኪዳን ቁራ ርኩስ እንስሳ ነው (ዘሌ 11፡15):: ኢየሱስ ቁራ የሚለውን ቃል መጠቀሙ እግዚአብሔር የዓለም ርኩሳን (ለሰዎችም) እንኳን እንደሚያስብ ረቂቅ በሆነ መንገድ ያመለክታል:: ሉቃስ እንደ አሕዛብነቱ በዚህ ጉዳይ ላይ ፍላጎቱ ከፍተኛ ሳይሆን አይቀርም!
3. ለነገ ስለ አለማሰብ ከተነገረው ይልቅ ሉቃስ እንዲህ ይላል፣ «እናንተ አነስተኛ መንጋ የሆናችሁ መንግሥትን ሊሰጣችሁ የአባታችሁ መልካም ፈቃድ ነውና አትፍሩ፤» ይህ ይበልጥ ፍቅርን ገላጭ አገላለጥ ሲሆን፣ ሉቃስ ለታናሾቹና ለጠፉት የቱን ያህል እንደሚጨነቅ ማለትም የግል መለያ ጠባዩን ያመለክታል::

አትጨነቁ፤ እግዚአብሔር ያስብበታል::» ይህ እንዴት እንደ ሆነ ለማሳየት በሁለት ጉልሕ ማስረጃዎች ይጠቀማል:: ስለ ምግብ ብዙ እንጨነቃለን:: ሆኖም ቁራዎችን ለምሳሌ ተመልከቱ:: እግዚአብሔር እነዚህን ንጹሕ ያልሆኑ ወፎች እንኳን ይመግባል! ታዲያ በእጅጉ የሚወዳቸውን ሰዎች ምን ያህል ይመግባቸው ይሆን? ስለ ልብሳችንም እንጨነቃለን:: ይሁን እንጂ የሜዳ አበቦችን ተመልከቱ:: ያማሩ ናቸው! እግዚአብሔር እነዚህን ዐላፊ ጠፊ የሆኑ አበቦች እንዲህ የሚያለብስ ከሆነ፣ ለአንተ ምን ያህል ይጨነቅልሃል?

መጨነቅ የለብንም:: ለምንድነው የማንጨነቀው? በመጀመሪያ ይህ አምላክ የለሽነት ነው:: በእግዚአብሔር ቸርነት ላይ ጥርጣሬ ማሳደራችንን በጉልሕ ያሳያል:: እርሱ ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ ለእኛ እንደሚያስብልን ተናግሯል:: ጭንቀታችን ግን ዋሾ ነህ ይለዋል:: ይህ ድርጊታችን እግዚአብሔርን ከማያውቁት አረማውያን ጋር ያመሳስለናል (ቍ 30):: ሁለተኛ መጨነቅ የሚያተርፈው ነገር የለም:: አንድ ነገር እንድንሠራ እንደሚያደርገን ግን የትም እንደማያደርሰን አሮጌ ተወዛዋዥ ወንበር ነው:: በሕይወትህ ላይ አንድ ሰዓት እንኳ አይጨምርልህም ብሎአል ኢየሱስ:: ምሳሌያዊው አነጋገር ቃል በቃል ሲገለጽም፣ «በሕይወት ዘመንህ ላይ ቅንጣት ታህል አይጨምርልህም» እንደ ማለት ነው:: የጊዜንና የርቀትን ዘይቤ በማጣመር በሕይወት ጎዳና የሚጓዝን ሰው እናያለን:: መጨረሻው ሥፍራ ደርሶአል:: ጭንቀቱ ሕይወቱን በአጭሩ ሳያስቀረው አልቀረም! ሦስተኛም በአንድ ጊዜ ልናከናውነው የምንችለው አንድ ነገር ብቻ ነው:: ሀብትን በማሳደድ ላይ እያለን እግዚአብሔርን ልንፈልግ አንችልም (ቍ 31፤ ከማቴ 6÷24 ጋር ያነጻጽሩ)::

ሉቃ 12÷33-34

«[33]ያላችሁን ሽጡና ለድኾች ስጡ፤ ሌባ በማይሰርቅበት፣ ብል በማይበላበት፣ በማያረጅ ከረጢት የማያልቅ ንብረት በሰማይ አከማቹ፤ [34]ልባችሁ፣ ንብረታችሁ ባለበት ቦታ ይሆናልና::»



[ቍ 33-34 = ማቴ 6፡19-21 በቍ 54ሰ ውስጥ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ]

ሉቃስ 12፡33፣ ማቴዎስ 6፡19ን ያሟላል:: ለራሳችን ሀብት ከምናከማች ይልቅ (ማቴ 6፡19) ያለንን ሀብት ሁሉ እንድንሸጥና ሽያጩንም ለድኾች እንድንሰጥ (ሉቃ 12፡33) ተጠይቀናል:: በመንግሥተ ሰማይ በራሳችን የሒሳብ መዝገብ ላይ የምናስቀምጥበት መንገድ ይህ ነው::

የማንፈልገውን ዕቃ ስንሸጥ ነገሩ እንዲህ አይደለም:: ዕቃዎቻችንን ስንሸጥ ለመደገፍ ድርጅቶችና ለተጫራቾች የምንሸጠው በዝቅተኛ ዋጋ ይሆናል:: ዋስትና የሚኖረን በባንኮችና መሰል ተቋሞች ውስጥ ነው:: በኢየሱስ ዘመን የንብረት ዋስትና የነበረው በዕንቁ፣ በልብስ፣ በከበሩ ብረታ ብረቶች፣ በመንጋዎችና በምግብ እህል ክምችት ላይ ነበር:: እነዚህን ንብረቶች የሚሸጧቸው ከመጀመሪያው ዋጋ 10 በመቶ (10%) ተቀንሰው ሳይሆን በወቅቱ በነበረው የልውውጥ መጠን ነበር::

የኢየሱስን ንግግር ወደ ሃያ አንደኛው ምእት ዓመት ስናመጣው ዛሬ የእኛን እርዳታ የሚፈልጉ ብዙ ሰዎች መኖራቸውን እያወቅን፣ ይህ ገንዘብ ለሚመጣው ጊዜ ያገለግለናል በማለት ማከማቸት የሌለብን መሆኑ ያስገነዝበናል:: በተጨማሪም ቃሉ፡ ተምሳሌታዊ አይደለም:: አሁን ቸርነት ብናደርግ ለዘላለሙ የሚሆነን ሀብት በሰማያት እንደምናከማች ኢየሱስ የነገረን ግልጽ በሆነ መልኩ ነው:: ሀብታችን ይዘነው እንደማንሄድ እርግጥ ነው፤ ነገር ግን አስቀድመን ልንልከው እንችላለን (ቍ 16-21)!

ንብረታችንን የምንሸጠው በቀናነት ለድኾች ጥቅም ነውን? አይመስለንም:: በንፉግነት የምናደርገው አስተዋፅኦ ድኽነትን

አያስወግድም። ድኽነት ምንጊዜም መኖሩ አይቀርም (ዘዳ 15፥11፤ ማቴ 26፥11)። ኢየሱስ በዋናነት የሚናገረው ለራሳቸው ለደቀ መዛሙርቱ ጥቅም ነው። ከቁሳዊ ነገሮች ሽክም መላቀቅ አለባቸው። ሀብት ለክርስቲያን ትልቅ አደጋ ነው። አእምሮን ግራ ያጋባል፤ ልብን ያሳውራል፤ ተገቢ ቅደም ተከተሎችንም ያመሰቃቅላል።

እንግዲህ ኢየሱስ ንብረታችሁን ሁሉ ሽጡ አላላም፤ ወይም ማለቱ አይደለም። በመጠኑ እየኖርን የተረፈውን ለድኾች መስጠት አለብን ነው ያለው። መተዳደሪያችንን ሠርተን እናገኝ ዘንድ ይጠበቅብናል፤ ዐቅሙ ካለን መሥራት አለብን (ምሳሌ 6፥6-8፤ 2ቆሮ 12፥14፤ 1ጢሞ 5፥8፤ 2ተሰ 3፥6-15፤ 1ተሰ 4፥10-12፤ ቈላ 3፥22-25፤ ኤፌ 6፥5-9)። ይህም ለኑሮአችን የሚያስፈልገንን ማቅረብን ማለት ለመኖሪያ፣ ለልብስ፣ ለመጓጓዣና ለቤተ ሰባችን የሚሆነውን ወጭ አመች አድርጎ መገኘት ማለት ነው (1ጢሞ 5፥8)። ሚዛናዊነት ያስፈልገናል። መጽሐፈ ምሳሌ 30፥8-9 እንዲህ ይላል፣ «ሐሰትንና ሐሰት መናገርን ከእኔ አርቅልኝ፤ ድኽነትንም ሆነ ብልጽግናን አትስጠኝ፤ ብቻ የዕለት እንጀራዬን ስጠኝ። ያለዚያ ግን ያለልክ እጠግብና እክድሃለሁ፤ 'እግዚአብሔር ማን ነው?' እላለሁ፤ ወይም ድኻ እሆንና እሰርቃለሁ፤ የአምላኬንም ስም አሰድባለሁ»።

በማጠቃለያም የገዳም ኑሮ እንድኖር ወይም ሁሉን እንድንተው አልተጠራንም። ኢየሱስ የሚናገረው ግልጽ ነው፦

1. እውነተኛ ሕይወት ያለው በምናከማቸው ሀብት ውስጥ አይደለም (ቍ 22-23)።
2. ስለ መሠረታዊ ፍላጎታችሁ አትጨነቁ፤ እግዚአብሔር ይሰጣል። እነዚህ ነገሮች እንደሚያስፈልጓችሁ እርሱ ያውቃል (ቍ 24-30)።



3. መንፈሳዊ ጉዳዮችን በመሻት ጊዜያችሁን አሳልፉ (ቍ 31-32)።
4. ዘላለማዊ ሀብት ታከማቹ ዘንድ ትርፍ የሆነውን ስጡ (ቍ 33-34)።

**§ 108ሐ ማስጠንቀቂያ፦ ለክርስቶስ ምጽአት ተዘጋጁ (ሉቃ 12፥35-48)**

ትኩረታችንን ወደ ብዙ ነገሮች ልናደርግ እንችላለን። ቀደም ባለው ምንባብ ልባችን በምድራዊ ሀብት ላይ እንዳይሆን ኢየሱስ አስጠነቀቀ። እዚህ ላይ ደግሞ አወንታዊ አማራጭ ይሰጣል፤ ይኸውም ትኩረታችሁን ለኢየሱስ ምጽአት ስጡ የሚል ነው። ይህኛው ስለ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት በግልጽ ከሚናገረው የደብረ ዘይት ተራራ ላይ ንግግር ጋር ይመሳሰላል (ማቴ 24፥45-51)። ወዲያውኑ የሚያመለክተው ግን በቅርቡ እውን የሚሆነውን የክርስቶስ መስቀል ሊሆን ይችላል።

*ሉቃ 12፥35-38*

[35]«በእጥር ታጥቃችሁ ተዘጋጁ፤ መብራታችሁም የበራ ይሁን፤ [36]ጌታቸው ከሰርግ ግብዣ እስኪመለስ እንደሚጠባበቁና መጥቶም በር ሲያንኳኳ ወዲያው ለመክፈት ዝግጁ የሆኑ ሰዎችም ምሰሉ። [37]ጌታቸው በሚመጣበት ጊዜ ነቅተው የሚያገኛቸው አገልጋዮች ብፁዓን ናቸው፤ እውነት እላችኋለሁ፤ ጌታቸውም በእጥር ይታጠቃል፤ በማእድ ያስቀምጣቸዋል፤ ቀርቦም ያስተናግዳቸዋል። [38]ከሌሊቱ በሁለተኛው ሆነ በሦስተኛው ክፍል መጥቶ እንደዚያው ነቅተው ቢያገኛቸው፣ እነዚያ አገልጋዮች ብፁዓን ናቸው።»

«በአጭር ታጥቃችሁ ተዘጋጁ» ማለት መቀነት ከመታጠቅ በላይ ነው:: «ታጥቃችሁ» የሚለው ቃል «ወገባችሁን ታጠቁ» ማለት ነው:: የፓሊስትና ወንዶች በሚሠሩበት ጊዜ ቀልጥማቸው ላይ የሚሰበሰብ ረጅምና ለቀቅ ያለ ቀሚስ ይለብሳሉ:: አለባበሱ ለሥራ ያስቸግራል:: ለዚህ መፍትሔው ወደ ተረከዝ ዝቅ ብሎ የልብሱን ታችኛ ግማሽ ክፍል በመሰብሰብ ፊት ለፊት ባለው መቀነት (መታጠቂያ) ማሰር ነው:: ሁኔታው ሲታይ በጣም ትልቅ የሕፃናት የሽንት ጨርቅ ይመስላል:: ቢሆንም ሌላው ቢቀር ለመሥራት፣ ለመሮጥ ወይም ለመመከት ዝግጁ ናችሁ ማለት ነው (ከ1ነገ 18÷46፤ እንዲሁም ከኤፌ 6÷14 እና ከ1ጴጥ 1÷13 ጋር ያነጻጽሩ):: ከዚህም በላይ «ተዘጋጁ» የሚለው ግስ ቀጣይ ክንዋኔን የሚያሳይ የአሁን ጊዜ ትእዛዛዊ አንቀጽ ነው:: ጌታን ለማገልገል ዘወትር መልበስ ዘወትር መዘጋጀት አለብን::

«ወገባችንን መታጠቅ» ብቻ ሳይሆን መብራታችን ሳይቋረጥ እንዲበራ ማድረግ አለብን (ማቴ 25÷1-13):: እነዚህ «መብራቶች» (ፋኑሶች) በቀላሉ የሚያዙ ናቸው:: ሆኖም ጧፉ መኩስተሩን ዘይት መያዣውም ዘይት ያለበት መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል::

በአጭር መታጠቅና የመብራትን ጧፍ መኰስተር ቀላል ክንዋኔዎች ናቸው:: ሆኖም ጌታው ከሰርጉ ግብዣ ሲመለስ ዝግጁ ሆኖ ለመገኘት ትጋትን ይጠይቃል::[26] «እስኪመለስ» (ቍ 26) ማለት «እስከሚለይ» ማለት ነው:: ድንኳን የማፍረስ እንድምታ አለው:: በሌላ

[26] P.E. Deterding, "Eschatological and Eucharistic Motifs in Luke 12:35-40" *CJ* (1979): 85-93 በሚለው ስሜት ቀስቃሽ (ተንኳሽ) መጣጥፉ የፋሲካን የመሲሓዊ ግብዣንና የጌታ እራትን ጭብጥ ይዳስሳል:: ሁሉም በዚህ ጽሑፍ ውስጥ እንደሚገኙ ያምናል:: ስለዚህ (ሀ) ሉቃስ 12÷35-40 የጌታን እራትና ዳግም ምጽአት አስቀድሞ ያመለክታል፤ እናም (ለ) ፋሲካ፣ የጌታ እራትና ዳግም ምጽአት ተመሳሳይ ጭብጥና ተመሳሳይ ዘይቤዎችን ስለሚጋሩ፣ አንዱ በሌላው አንጻር መታየት አለባቸው::



አገላለጽ የሰርጉ ግብገር ተካሂአል፤ ከሙሽሪት ጋር ወደ ቤቱ እየመጣ ነው:: ሰውየው ወደ ቤቱ የሚመጣው በዚህ ቀን ነው ብሎ የሚነገርበት መንገድ አልነበረም:: ግብገሮው ጥቂት ሰዓታት ወይም ጥቂት ቀናት ሊወስድ ይችላል:: ስለዚህ የጌታው መመለሻ በሁለተኛው ወይም በሦስተኛው ክፍል፣ (ከምሽቱ ሦስት ሰዓት እስከ ሌሊት ዘጠኝ ሰዓት) ከእኩለ ሌሊት በኋላ ሊሆን ይችላል:: ሁኔታው አስቸጋሪ አልነበረም:: ግን ትጋትን ይጠይቃል:: እንደዚሁም ባልተጠበቀና በማይመች ጊዜ ቢሆንም እንኳን ክርስቶስን በትጋት የሚጠባበቁ ሁሉ እርሱ በሚመጣበት ጊዜ ልዩ በረከትን ይቀበላሉ::

በዚህ ምሳሌ የተጠቀሰው ባለቤት በመጣ ጊዜ ያልተለመደ የሚናዎች ሞለዋወጥ ይኖራል:: ጌታው አገልጋዮቹን ማገልገል አልነበረበትም:: ይህ ተሰምቶ የማይታወቅ ነገር ነው:: ሆኖም ለትጋታቸው ሽልማት እንዲሆን እነርሱን አገለገለ:: ኢየሱስ ለእኛ ያደረገው በትክክል ይህንኑ ነው:: ወልድ አገልጋይ ሆነ (ከሉቃ 27÷27፤ ከዮሐ 13÷1-17 ጋር ያነጻጽሩ)::[27] ይህ ሊሆን የሚችለው በእግዚአብሔር መንግሥት ብቻ ነው::

> [39]ይህን ግን ዕወቁ፤ ሌባ በምን ሰዓት እንደሚመጣ የቤቱ ባለቤት ቢያውቅ ኖሮ፣ ቤቱ ሲቈፈር ዝም ብሎ ባላየ ነበር:: [40]እናንተም ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ፤ የሰው ልጅ ባላሰባችሁት ሰዓት ይመጣልና::
>
> **ሉቃ 12÷39-40**

«ሲቈፈር» ማለት «የሸክላው ዐፊር ሲነሣ» ማለት ነው:: የፍልስጥኤማውያን ቤቶች የሚሠሩት በፀሐይ ከደረቀ ጡብ ነበር:: በመሆኑም በሩን ሰብሮ ከመግባት የጣራውን ወለል ሰብሮ መግባት ይቀል ነበር:: እንግዲህ ሌባው መቼ እንደሚመጣ ብናውቅ እንዳይገባ ማድረጉ ቀላል ይሆን ነበር (ከማቴ 24:42-44 ጋር ያነጻጽሩ)::

[27] ይህ ልዩ ሐሳብ ከቀረበበት (Liefeld, p. 966) ከሉቃ 17:7-10 ንጽጽሮሽ አኳያ ነው::

እንደዚሁም ኢየሱስ መቼ እንደሚመጣ ብናውቅ፣ እርሱን ለመቀበል መዘጋጀቱ ቀላል ይሆንልን ነበር:: ለኢየሱስ ያለን ፍቅር የሚገለጸው ለእርሱ መምጣት ዝግጁዎች በመሆናችን ሳይሆን፣ ለእርሱ መምጣት ዝጅጉዎች ሆነን በመጠባበቃችን ነው:: በድንገትና ሳይታሰብ ይመጣል (ከማቴ 24፥36-25፥30፤ ከ1ተሰ 5፥1-2፤ ከ2ጴጥ 3፥10፤ ከራእ 3፥3 ጋር ያነጻጽሩ):: ተዘጋጅተን ብንጠብቅ ይሻላል::

**ሉቃ 12፥41-46**

41ጴጥሮስም፣ «ጌታ ሆይ፤ ይህን ምሳሌ የምትናገረው
ለእኛ ብቻ ነው ወይስ ለሁሉም ጭምር ነው?» አለው::
42ጌታም እንዲህ ሲል መለሰ፤ «እንግዲህ፣ ምግባቸውን በተገቢው ጊዜ
እንዲሰጣቸው ጌታው በቤተ ሰዎቹ ላይ የሚሾመው ታማኝና ብልህ መጋቢ ማነው?
43ጌታው ሲመለስ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው አገልጋይ እርሱ ብፁዕ ነው:: 44እውነት
እላችኋለሁ፤ ባለው ንብረት ሁሉ ይሾመዋል:: 45ዳሩ ግን ያ አገልጋይ፣ ጌታዬ ቶሎ
አይመጣም፤ ይዘገያል፤ ብሎ ቢያስብና ወንድና ሴት አገልጋዮችን ቢሰድብ፣ ደግሞም
እንዳሻው መብላት፣ መጠጣትና መስከር ቢጀምር፣ 46የዚያ አገልጋይ ጌታ ባላሰበው
ቀንና ባልጠረጠረው ሰዓት ይመጣበታል፤ ስለዚህ ይቈራርጠዋል፤ ዕድል ፈንታውንም
ከማያምኑ ጋር ያደርጋል::

ጴጥሮስ እንደ ተለመደው የቡድኑ አፈ ጉባኤ ሆኖ ይሠራል:: ኢየሱስም በተለመደው የምትህርት አቀራረቡ ጥያቄውን በጥያቄ ይመልሳል (ከማቴ 24፥45-51 ጋር ያነጻጽሩ):: ጴጥሮስ በእርግጥ ይጠይቅ የነበረው ስለ ሹመት ነው:: ይኸውም «የአንተ ልዩ አገልጋዮች እኛ ብቻ ነን?» የሚል ነው:: ኢየሱስ የመለሰው ግን ስለ ኀላፊነት በመናገር ነው:: ይኸውም «ለአንድ ሰው ኀላፊነት ከሰጠሁት፣ ሥራው መ ሙን ማረጋገጥ አለበት» የሚል ነው:: አገልጋዩ ጴጥሮስ ብቻ፣ ወይም ሐዋርያት ብቻ ወይም በዚያ የቆሙት ሁሉ ሆኑም አልሆኑ ምንም አይደለም:: ዋናው ነገር ኢየሱስ አንድ ሥራ ከሰጠህ፣ ሌሎች ምን እንደሚሠሩ ከመጨነቅ ወይም ይሠሩ ዘንድ ምን እንደ



ተሰጣቸው ከመጨነቅ ይልቅ ለተሰጠህ ሥራ ታማኝ ስለ መሆንህ መጨነቅ ነው:: ሌላ ስፍራ ግን ተግቶ የመጠባበቁ ትእዛዝ ለእያንዳንዱ ሰው የተሰጠ መሆኑን ኢየሱስ ግለጽ አድርጎአል (ማር 13፥37)::

በስኬታማ ድርጅቶች እንደሚሆነው ሁሉ በእግዚአብሔር መንግሥትም ኀላፊነትን በሚገባ የሚወጡ በየጊዜው የላቀ ኀላፊነት ይሰጣቸዋል:: ጴጥሮስ ስለ ሹመት ያቀረበውን ጥያቄ ኢየሱስ በመሠረቱ በመመለስ ላይ ነው:: «ሥራህን በሚገባ አከናውን» ይላል ኢየሱስ፤ «ከዚያም ተጨማሪ ሥራ ይሰጥሃል» ሌላ ስፍራ እንደ ተናገረው፣ «በትንሽ ነገር ታማኝ የሆነ በትልቁም ይታመናል» (ሉቃ 16፥10)::

አለቃው በሚቈጣጠርበት ጊዜና እርሱ ከሄደ ከጥቂት ጊዜ በኋላም ኀላፊነትን መወጣት ቀላል ነው:: ነገር ግን አለቃው ሳምንቱን ሙሉ ወይም ወሩን ሙሉ የማይኖር ከሆነ፣ ኀላፊነትን ወዳለመወጣት ሁኔታ መዝቀጡ ቀላል ይሆናል:: እንደዚሁም በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ብዙዎች፣ «ኢየሱስ ከሄደ ብዙ ጊዜ ነው፤ ጌታ ዳግም ከመምጣቱ በፊት ሕይወቴን ለማስተካከል ጊዜ አለኝ» ይላሉ:: በጥንቃቄ አንብቡና አስተውሉ! ለክርስቶስ ያለን ፍቅር በዋናነት የሚታየው፣ ለምጽአቱ ዝግጁዎች በመሆናችን ሳይሆን፣ ለምጽአቱ ዝግጁዎች ሆነን በመኖራችን ነው::

በጥንታውያን ሕዝቦች ዘንድ ተለምዶ የነበረ ቢሆንም (ከ1ሳሙ 4፥12፤ ከዳን 2፥5፤ ከዕብ 11፥37 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ይህ ሰውን ስለ መቈራረጥ የተደረገ ገለጣ አግንኖ የማሳያ ስልት ነው::[28] ሆኖም ታሪኩ

[28] P. Ellingworth, "Lk 12:46 - Is There an Anti-Climax Here?" *BT* 31/2 (1980): 242-243 በሚለው ጽሑፉ *'ዳይኮቶሜሲ - dichotomesei'* «ከእግዚአብሔር ሕዝብ ተወገደ» ብለን በመተርጐም እንዲህ ያለውን ብርቱ ቋንቋ አለሳልሰን እናቀርበዋለን ይላል:: ይህ ዘሌ 17፥10ን የሚያንጸባርቅ ሲሆን «ዕድል ፈንታውንም ከማያምኑ ጋር ያደርጋል» ከሚለው ከሉቃ 12፥46 ሁለተኛ አጋማሽ ጋር በጣም ይገጣጠማል ይላል:: ነገር ግን M.A. Beavis, "Ancient

ውስጥ የሚገኙት ገጸ ባሕርያት የዘላለም ፍርድ የሚቀበሉትን (ከሐሥ 20÷29-30፤ ከማቴ 7÷15-23 ጋር ያነጻጽሩ)፣ የሐሰት መምህራንና ግብዝ ሃይማኖተኞችን እንደሚወክሉ ማስተዋል አለብን::

ሉቃ 12÷47-48

47«የጌታውን ፍላጎት እያወቀ የማይዘጋጅና
ፈቃዱን የማያደርግ አገልጋይ እርሱ ከፍኛ ይገረፋል፤
48ነገር ግን ይህን ሳያውቅ ቀርቶ መገረፍ የሚገባውን
ያህል ያደረገ አገልጋይ በጥቂቱ ይገረፋል:: ብዙ
ከተሰጠው ሁሉ ብዙ ይፈለግበታል፤ ብዙ ዐደራ
ከተቀበለም ብዙ ይጠበቅበታል::»

የድፍረት ኀጢአት (ከዘኍ 15÷30-31 ጋር ያነጻጽሩ) አይቀጡ ቅጣት ያስቀጣል:: ብዙ የሚያውቁ፣ ግን አሁንም በደልን የሚፈጽሙ ወይም ትክክሉን ዐውቀው ሳለ የማይደፈጽሙት የከፋ ፍርድ ይጠብቃቸዋል:: ሉቃስ «መምታት» ለሚለው ግስ የተጠቀመው የጭካኔ ቃል ሲሆን፣ «መግፈፍ» ወይም «መላጥ» ተብሎ ሊተረጎም ይችላል::

ካለማወቅ የሚፈጸም ኀጢአት (ዘኍ 15÷27-29፤ መዝ 19÷12) በመጠኑ ይቀጣል፤ መቀጣቱ አይቀርም::[29] ለምን? ምክንያቱም

---

Slavery as an Interpretive Context for the N.T. Servant Parables with Special Reference to the Unjust Steward (Lk 16:1-8)" *JBL* 111/1 (1992): 37-54 እንዲህ ያለው አረመኔያዊ ቋንቋ በሮም ሙሉ ግዛት ውስጥ ብዙዎቹ ባሪያዎች የተቀበሉትን ሥቃይ በትክክል ይገልጻል ይላል::

[29] ይህ ማለት ግን ቅጣቱ ቀላል ወይም የሚቻል ዐይነት ይሆናል ማለት አይደለም:: ያው ገሃነመ እሳት ነው:: የቅጣት ደረጃ ያለ መሆኑን የሚያስተምር ይመስላል:: አንዳንድ የነገረ መለኮት ሊቃውንት ይህ ፍጽመተ ውድመት የሚባለውን ያመለክታል ይላሉ (ለምሳሌ Clark Pinnock, John Stott, Edward Fudge, Michael Green, Russel Boatman):: በመሠረቱ ይህ አቋም እግዚአብሔር አማናዊ በሆነ ገሀነመ እሳት ውስጥ ተገቢ ለሆነ ወቅት ክፉ የሚሠሩትን የሚቀጣ መሆኑን፣ ከዚያም ነብሳቸው ለዘላለም የምትጠፋ መሆኑን ያረጋግጣል:: ለዚህ አቋም ክርክሮቹ የሚከተሉትን ያካትታሉ:- (1)



አገልጋይ የጌታውን ፈቃድ ማወቅ ነበረበት:: ሰዎች ሁሉ ስለ እግዚአብሔር የተወሰነ ነገር ያውቃሉ (ሮሜ 1:20)፤ በተረዱት መጠንም ፍርድ ይቀበላሉ (ሮሜ 2:12-13):: አለማወቅ ምክንያት ሊሆን አይችልም::

**§ 108መ**
**ማስጠንቀቂያ:-**
**ችግር እየመጣ ነው**
**(ሉቃ 12÷49-53)**

49«እኔ የመጣሁት በምድር ላይ እሳት
ለመለኰስ ነው፤ አሁኑኑ ቢቀጣጠል ምንኛ ደስ ባለኝ!
እስኪፈጸምም ድረስ እንዴት ተጨንቄአለሁ? 50ነገር ግን
የምጠመቀው ጥምቀት አለኝ፤ እስኪፈጸምም ድረስ
እንዴት ተጨንቄአለሁ? 51በምድር ላይ ሰላምን
ለማምጣት የመጣሁ ይመስላችኋል? አይደለም፤
እላችኋለሁ፤ እኔ የመጣሁት ለመለያየት ነው:: 52ከአሁን
ጀምሮ እርስ በርስ
የተለያዩ በአንድ ቤተ ሰብ ውስጥ አምስት ሰዎች ይኖራሉ፤ ሁለቱ በሦስቱ ላይ፣
ሦስቱም በሁለቱ ላይ፣ ወንድ ልጅም በአባቱ ላይ፣ እናት በሴት ልጇ ላይ፣ ሴት

---

በ1ጢሞ 6:15-16 በመመሥረት፣ የሰው ኢመዋቲነት እውን የሚሆነው ከአምላክ መለኮታዊ መንፈስና ከትንሣኤ አካል ጋር ባለው ግንኙነት ብቻ ነው (1ቆሮ 15÷50-54):: ስለዚህ ሰዎች ገሀነመ እሳት ውስጥ ዘላለማዊ ከሆኑ፣ በምድር ላይ በእግዚአብሔር ተደግፈው እንደኖሩ ሁሉ በገሀነም ውስጥም እግዚአብሔር ደግፎ ማኖር አለበት:: ይህ ደግሞ እግዚአብሔር ፍጥረተ ዓለምን ሙሉ በሙሉ ከቶ የማይቤዥበትን ዘላለማዊና የማይመች ውስጣዊ እንዲሁም መንታ ዓለም ይፈጥራል:: (2) መጽሐፍ ቅዱስ ኀጢአተኞች ይጠፋሉ ብሎ ያስተምራል (መዝ 37÷2:9-10:20:38፤ ሚል 4:1-2፤ ማቴ 3:10-12፤ 10:28፤ ገላ 6÷8፤ 1ቆሮ 3÷17፤ ሮሜ 1:32፤ ፊል 1:28፤ 3:19፤ 2ጴጥ 2:1:3:6፤ 3÷6-7፤ ወዘተ):: እነዚህ ምንባቦች ተምሳሌታዊ በሆነ መልኩ ስለ ዘላለማዊ ገሀነመ እሳት የሚናገሩ ሆነው ከተገኙ፣ ሌሎች ምንባቦች ውስጥ «ዘላለማዊ» የሚለው ቃል ግነታዊ በሆነ መልኩ ዘላለማዊ ስለ ሆነው ፍጽመተ ውድመት ሊናገር ይችላል (ለምሳሌ ማቴ 25:46፤ ማር 9:48፤ ራእ 14:11):: (3) ፍጽመተ ውድመት እግዚአብሔርን እስከዚህ ነው በማይባል ዘመን ውስጥ የጠፉትን ጥበባዊ፣ ግን ርኅራኄ ቢስ በሆነ መልኩ የሚቀጣ አድርጎ ከማሳየት ይልቅ ጻድቅ አድርጎ ይገልጸዋል:: ስለዚህ እግዚአብሔርን የዘላለማዊ አውስኪዊትዝ - Auschwitz ቅጣት ምንጭ አድርገው የሚያቀርቡትን ለመከራከር ፍጽመተ ውደመት ውጤታማ ዐቃቤ እምነት ነው::

ልጅም በእናቷ ላይ፣ አማት በምራቷ ላይ፣ ምራትም በአማቷ ላይ ተነሥተው ይለያያሉ።»

[ቍ. 51-53 = ማቴ 10÷34-36፤ በቍ. 70ለ ላይ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ]

ኢየሱስ በጎ ነገሮችን ሁሉ ወደ ምድር አመጣ። ሁሉም ቀላል ነበር ማለት ግን አይደለም። ኢየሱስ በዚህ ምንባብ ውስጥ ለዓለምና ለራሱ የሚከፈለውን ዋጋ ዐሰበ።

የሚከፍለው ዋጋ የቀራንዮ መስቀልና መስቀሉን ተከትሎ የሚመጣው ማለት ከአብ መለየት፣ በራሱ ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነትን ማጣት፣ መደብደብ፣ በአደባባይ መሰደብ፣ ወዘተ ናቸው ይህን ሁሉ ኢየሱስ ጥምቀት ብሎታል (ከማር 10÷38-39 ጋር ያነጻጽሩ)፤ የሥቃይ መዐት ማለት ነው።

ዓለም የሚከፍለው ዋጋ እሳትና መከፋፈል ይሆናል። ይህ እሳት ያለጥርጥር የሚያመለክተው ፍርድን ነው። ኢየሱስ እንዲሠቃይ በመደረጉ፣ ኢየሩሳሌም በእግዚአብሔር ርግማን ሥር ሆናለች (ማቴ 27÷25፤ ሉቃ 23÷28-31)። ከተማዋ በወደመችበት 70 ዓ.ም. ይህ በሚገባ ግልጽ ይሆን ነበር። ከዚህም በላይ ኢየሱስ ዳኛ፣ (ዮሐ 5÷22:27)፤ ቃሉም ሰዎች ፍርድ የሚቀበሉበት ሚዛን ነው። ይህ እሳት ፍርድን የሚያመለክት መሆኑ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ማንጻትንም ያካትታል። በእሳት ያልተቃጠለ ሁሉ በዚያው እሳት ንጹሕ ይሆናል።

ለዓለም ሁለተኛው ዕዳ ኢየሱስ መከፋፈልን እውን የሚያደርግ መሆኑ ነው። በኢየሱስ ዘንድ «ከፍርድ ነጻ የሚሆን አካል» ባለመኖሩ በጣም ጥብቅ የሆነውን የቤተ ሰብ ግንኙነት እንኳ ሳይቀር ይከፋፍላል። አንድ ሰው ሙሉ በሙሉ የእርሱ መሆን፣ ወይም ሙሉ በሙሉ እርሱን የሚቃወም መሆን አለበት። ካለብን ውጤቱ አሳዛኝና አይቀሬ ነው።



ኢየሱስ ሰላምን ወደ ዓለም አምጥቶአል (ሉቃ 2:14፤ 7:50፤ 10:5)፤ የእርሱ ሰላም ተስፋ ሆኖ የተሰጠው ግን ለክርስቲያኖች ነው። ኢአማንያን ይህ ሰላም ሊኖራቸው አይችልም። ከዚህም በላይ በዚህ አስጨናቂ ዓለም ውስጥ ክርስቲያኖች መከራ የሚበዛባቸው በመሆኑ ይህ ሰላም የውስጥ ሕይወት ሰላም ነው። በዚህ ምንባብ መሠረትም ይህ አስጨናቂ ክፍፍል እውን የሚሆነው ከቤተ ሰብ ሊሆን ይችላል (ከሚክያስ 7:6 ጋር ያነጻጽሩ)።

**§ 108ሠ**
**የጊዜያቱን ምልክቶች መተርጐምን አስመልክቶ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ**
**(ሉቃ 12÷54-59)**

54ደግሞም ለሕዝቡ እንዲህ አለ፤ «ደመና
በምዕራብ በኩል ሲወጣ ሲታዩ ወዲያው፣ ዝናብ ሊመጣ
ነው ትላላችሁ፤ እንደዚያም የሆናል፤ 55የደቡብ ነፋስም
ከደቡብ በኩል ሲነፍስ፣ ቀኑ ሞቃት ይሆናል ትላላችሁ፤
እንደዚያም ይሆናል። 56እናንት ግብዞች የምድሪንና
የሰማዩን መልክ መመርመር ታቀበታላሁ፤ ታዲያ ይህን
የአሁኑን ዘመን መመርመር እንዴት ተሳናችሁ?»

[ቍ. 54-56 = ማቴ 16:2-3፤ በቍ. 80 ላይ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ]

በይሁዳ ምድር ከምዕራብ በኩል ደመና የሚነሣ ከሆነ፣ ዝናብ ከሜዲትራንያን ባሕር ይመጣል ማለት ነው። በኔጌቭ ምድረ በዳ በኩል የሚመጣ ደቡባዊ ነፋስ ሞቃት አየርን ይዞ ይመጣል። የአየርን ሁኔታ የሚያስተውል ማንም የፓሊስቲና ሰው ይህን ያውቃል። ሰዎች የአየርን ሁኔታ በሚገባ የሚያውቁ ሆነው ሳለ፣ የወቅቱን መንፈሳዊ ሁኔታ በመገንዘብ ረገድ ለምን የማያስተውሉ ሆኑ? መጠነኛ ማስተዋል ያለው ሰው፣ በተለይ በታምራቱና በነቢያት በኩል የኢየሱስን ማንነት ለመገንዘብ ይችላል። ምልክቶቹ የታወቁ ናቸው።

እነዚህ መልክቶች ከዳግም ምፅአቱ ይልቅ ከኢየሱስ መጀመሪያ መምጣት ጋር ቀጥታ ግንኙነት አላቸው:: በኢየሱስ ዳግም ምጽአት ላይ የተደረገው አጽንዖት የወቅቱን ምልክቶች በመተርጎም ላይ ሳይሆን፣ ተስፋ ለተደረገው ለጌታ ዳግም ምጽአት ተዘጋጅቶ በመኖር ላይ ነው::

ሉቃ 12፥57-59

[57]«ታዲያ ራሳችሁ ትክክለኛ የሆነውን ነገር ለምን
ለትፈርዱም? [58]ከባላጋራህ ጋር ወደ ዳኛ ፊት ለመቅረብ
ስትሄድ ገና በመንገድ ሳይ ሳለህ ለመታረቅ ጥረት
አድርግ፤ አለበለዚያ ጐትቶ ወደ ዳኛው ይወስድሃል፤ ዳኛ
ውም ለመኰንኑ አሳልፎ ይሰጥሃል፤ መኰንኑም ወደ ወህኒ
ይጥልሃል፤ [59]እልሃለሁ፤ የመጨረሻዋን ሳንቲም[ፊ]
እስክትከፍል ድረስ ከዚያ አትወጣም::

[ፊ]59 ግሪኩ ሌፕቶን ይላል

[ቍ 57-59 = ማቴ 5፥25-26፤ በቍ 54[ሠ] ላይ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ]

ማቴዎስ እነዚህን ሰዋዊ ስለ ሆኑ ግንኙነቶች ለመግለጽ ሲጠቀምባቸው፣ ሉቃስ ግን ከመለኮት ጋር ስላለው ግንኙነት ይጠቀምባቸዋል:: ማቴዎስ በተናገረው መሠረት አብ ፊት ከሚያቀርበን ክርስቶስ ጋር መወዳጀት አለብን:: እርሱ ለልጅነት ወይም ለፍርድ አብ ፊት ያቀርበናል (ከመዝ 2፥12 ጋር ያነጻጽሩ):: ጊዜው በመፍጠን ነው:: ቶሎ ብንታረቅና ከፍርድ ብናመልጥ ይሻለናል![30]

[30] B. Kinman ይህ ምሳሌ የተነገረው ስለ ግለሰብ ዘላለማዊ ቅጣት ሳይሆን፣ እስራኤላውያን ኢየሱስን አንቀበልም በማለታቸው በእነርሱ ላይ ስለሚመጣው ጊዜያዊ ፍርድ ነው በማለት ክርክሩን ያቀርባል፤ "Debtor's Prison and the Future of Israel (Lk 12:57-59" *JETS* 42/3 (1999): 411-425.



**§ 109**
**ንስሓ ግቡ ወይም ጥፉ**
**(ሉቃ 13፥1-9)**

**ንስሓ ግቡ ወይም ጥፉ፣ ተመለሱ ወይም ተቃጠሉ!** እነዚህ መፈክሮች ጭክና የተሞላባቸው፣ ጠባብና እንደውም ዘግናኝ ናቸው:: ይሁን እንጂ ከኢየሱስ አንደበት የወጡ እውነትና ቀጥተኛ (ወላዋይነት የሌለባቸው) ቃሎች ናቸው:: የሰጠው ማስጠንቀቂያ ግልጽና ምሕረት ያለበት ነው:: አንድ ሰው መኪናውን ወደ ገደል ቢነዳ፣ «ንስሓ ግባ፤ ወይም ጥፋ» ብሎ የማይጮኽ ማን ነው! ቅዱት መጻሕፍት እውነት ከሆኑ ዘንድ፣ ሰዎችን ስለ ሲኦል ማስጠንቀቅ አለብን::

ሉቃ 13፥1-5

[1]በዚህ ጊዜ መጥተው፣ ጲላጦስ ደማቸውን
ከመሥዋዕታቸው ጋር ስለ ደባለቀው ስለ ገሊላ ሰዎች
ያወሩለት ሰዎች በዚያ ነበሩ:: [2]እርሱም እንዲህ
መለሰላቸው፤ «ታዲያ እነዚህ የገሊላ ሰዎች ከሁሉ ይልቅ ኀጢአተኞች ስለ ነበሩ
ይመስላችኋል? [3]አይደለም እላችኋለሁ፤ ንስሓ ካልገባችሁ ሁላችሁ እንደዚሁ
ትጠፋላችሁ:: [4]ወይም ደግሞ በሰሊሆን ግንብ ተንደባቸው የሞቱት ዐሥራ ስምንት
ሰዎች በኢየሩሳሌም ከሚኖሩት ሰዎች ሁሉ ይልቅ በደለኞች ስለ ነበሩ ይመስላችኋል?
[5]አይደለም እላችኋለሁ፤ ንስሓ ካልገባችሁ ሁላችሁ እንደዚሁ ትጠፋላችሁ::»

እነዚህ የገሊላ ሰዎች በጲላጦስ ስለ መጨፍጨፋቸው የሚነግረን፣ በሉቃስ ወንጌል ከተጠቀሰው በቀር ሌላ ማስረጃ የለንም:: ጲላጦስ ከ26-36 ዓ.ም. ድረስ የዐመፅ ምድር የነበረችውን የይሁዳ ግዛት ማስተዳደሩን እናውቃለን:: ከአይሁድ ጋር በየጊዜው ይጋጭ ነበር:: የጴንጤናዊው ዘመንተኞች የነበሩት ፋይሎ (*Embassy to Gaius* 38) እና ኢዮሳፍስ (*Antiquities* 18.55-62; *War* 2.169-174) ጲላጦስን ጨካኝና ዐመፀኛ ሰው በማለት ገልጸውታል:: ከአይሁድ ጋር በየወቅቱ መጋጨቱ ለእርሱ እንግዳ ነገር አልነበረም::

በዚህ ምንባብ መሠረት አንዳንድ የገሊላ ዐመፀኞች ኢየሩሳሌም ውስጥ መሥዋዕት በሚያቀርቡበት ጊዜ[31] ጲላጦስ ገድሏቸዋል:: ይህ የተፈጸመውም በቀላሉ ነበር:: የሮም መንግሥት ጦር ከቤተ መቅደሱ ሰሜን ምዕራብ በአንጦንያ ምሽግ ሠፍሯል:: ወታደሮቹ አመቺ በነበረው ቦታቸው ላይ ሆነው ቤተ መቅደሱ ውስጥ የሚከናወነውን ነገር ለመቃኘት ይችሉ ነበር:: እነዚህ የገሊላ ሰዎች ከተወሰነላቸው ክልል ወጥተው ስለ ነበር ቤተ መቅደሱ ውስጥ መሥዋዕታቸውን በማቅረብ ላይ ሳሉ ወታደሮቹ እንዲገድሏቸው ታዘዙ:: ይህ ለአይሁዳውያን የሚዘገንን ድርጊት ነበር:: እነዚህ «ወሬ አናፋሾች» በዚህ ጉዳይ ላይ ኢየሱስ አንድ ነገር እንዲያደርግ የፈለጉ ይመስላሉ:: ያም ሆነ ይህ እውነተኛ መሲሕ ጲላጦስን መበቀሉ አይቀርም::

አንድ ሰው ከኀጢአቱ የተነሣ ሥቃይ ይቀበላል ብለው ለሚያምኑት አይሁድ እንዲህ ያለው ሁኔታ ግራ የሚያጋባ ነበር:: እንዲህ ያለ ነገር ደጋግ በነበሩ ሰዎች ላይ ለምን እንደ ደረሰ ኢየሱስ እንዲያብራራላቸው ሳይፈልጉ አልቀሩም:: ወይም ወገኖቹ የሆኑትን ገሊላውያንን ክፉዎች ናቸው በማለት እንዲያወግዛቸው አስበው ይሆናል:: ኢየሱስ ግን በዚህ ሐሳባቸው አልተጠመደም (ከዮሐ 9÷1-3 ጋር ያነጻጽሩ):: ይልቁን ፍርድ በዓለም ውስጥ ያለና ከአጥናፍ እስከ አጥናፍም ጭካኔ ያለበት ድርጊት መሆኑን አስተማረ:: ኢየሱስ ይህን ሐሳብ ዳግመኛ የተናገረው በሰሊሆም ኩሬ የደረሰውን የግንብ መፍረስ ምሳሌ በማቅረብ ነው (የዚህን ዝርዝር ጉዳይ እኛ አናውቅም):: በግራ ቀኙ ወገኖች ላይ ይህ ሁኔታ የደረሰው እግዚአብሔር በኀጢአታቸው ስለ ቀጣቸው አይደለም:: በትክክለኛ ጊዜ አጉል ቦታ የተገኙ ሰዎች ነበሩ እንጂ:: ንስሐ ካልገባን ሁላችንም የእግዚአብሔር ፍርድ

[31] የገሊላ ሰዎች በተለይ ለዐመፅ ያደሩ እንደ ነበሩ ኢዮሳፍስ ይገልጻል (Josephus, *Life* 92.17).



ይደርስብናል:: ይህ በሰይፍ ከመገደል ወይም በግንብ ናዳ ከመሞት የከፋ ቅጣት ነው::

**ሉቃ 13÷6-9**

[6]ደግሞም እንዲህ ሲል ይህን ምሳሌ ተናገረ፤ «አንድ ሰው በወይኑ ዕርሻ ቦታ የተተከለች አንዲት የበለስ ተክል ነበረችው፤ እርሱም ፍሬ ሊፈልግበት መጥቶ ምንም አላገኘም:: [7]የወይን አትክልት ሠራተኛውንም፣ «እነሆ፤ ፍሬ ለማግኘት ስፈልግበት ሦስት ዓመት ወደዚህች በለስ መጥቼ ምንም አላገኘሁም፤ ስለዚህ ቍረጣት፤ ለምን ዐፈሩን በከንቱ ታሟጥጣለች?» አለው::

[8]«እርሱ ግን እንዲህ ሲል መለሰለት፤ ጌታ ሆይ፤ ዙሪያዋን እስኰተኵትለትና ፍግ እስከማደርግለት ድረስ ለዘንድሮ ብቻ ተዋት፤ [9]ከአርሟ ካፈራች መልካም ነው፤ አለበለዚያ ትቈርጣታለህ::»

ኢየሱስ ባለፈው ያስተማረውን ትምህርት በምሳሌ ጕልሕ አድርጎ አቀረበ:- በአንድ ወቅት የወይን እርሻ የነበረው አንድ ገበሬ ነበር:: በወይኖቹ መካከል የፍሬ ዛፎችን በመትከል የወይን መኸሩን አሳደገ:: እስከዚህ ድረስ መልካም ነበር:: ይህ የበለስ ዛፍ እስኪያድግ ድረስ በትዕግሥት ጠበቀ:: አደገ:: እስከሚያፈራ ድረስ ጠበቀ:: አላፈራም:: በሁለተኛው ዓመት፣ በሦስተኛውም ጠበቀ:: ምንም አላገኘ ም! በለሱን አስወግዶ ፍሬ በሚያፈራ ሌላ ተክል የመተካቱ ጊዜ አሁን ነበር:: ዛፎችን ይንከባከብ ዘንድ የተቀጠረው ገበሬ ግን የለፋበት ሥራ ከንቱ ሆኖ ሲቀር ለማየት አይፈልግም:: ስለዚህ ይህ ፍሬ ቢስ የሆነው የበለስ ዛፍ ከመቈረጡ በፊት ለአንድ ተጨማሪ ዓመት እንዲታይ ልመና አቀረበ፤ ተፈቀደለትም:: ይህ የበለሱ የመጨረሻ ዕድል ይሆናል::

ኢየሱስ የሚያነጋግሩትን እምነተ ቢስ ተከታዮች ለመቋቋም ፍሬ በሌለበት የበለስ ዛፍ ታሪክ ተጠቀመ። እነዚህ ሰዎች ጲላጦስ የሕዝባቸውን ደም እንደ ጎርፍ በማፍሰሱ ኢየሱስ ይበቀልላቸው ዘንድ ፈልገዋል። ኢየሱስ ግን የራሳቸው ጊዜ ከማለፉ በፊት ንስሐ እንዲገቡ አሳሰባቸው። እነዚህ ቀናተኛ «ደቀ መዛሙርት» ንጉሣችን ይሆናል ያሉት ሰው ሕይወታቸው ያለፈ ወገኖቻቸውን ሞት ለመበቀል ባልፈቀደ ጊዜ ተደነቁ። ለንስሓ ያቀረበላቸውን ጥሪ ካልተቀበሉት ደግሞ ያልጠበቁት ክፉ ነገር ይገጥማቸዋል።

በታሪኩ ላይ እንደተጠቀሰችው ዛፍ ለምለም ምድር ላይ እንድንኖር ተደርገን ነበር። እግዚአብሔርም ማዳበሪያ እንዳገኘች ዛፍ መግቦናል። ከዚያም ፍሬ እስከምናፈራ ድረስ ለረጅም ጊዜ በትዕግሥት ጠበቀን። ትዕግሥቱ ታላቅ ነው፤ የማያልቅ ግን አይደለም። «ክርስቲያን» ፍሬ አልባ ሆኖ እንዲቀር አይፈቀድም። እንዲህ ነው ዙሪያ ክብ ተጉዘን ነገራችን፡- «ንስሓ ግባ፤ ወይም ጥፋ» የሚሆነው። የሰሊሆም ግንብ ሲፈርስ በሞቱት ላይ፣ ቤተ መቅደስ ውስጥ መሥዋዕታቸውን ያቀርቡ በነበሩት ዐመፀኛ ገሊላውያን ላይና ፍሬ በማያፈራው በማንኛውም ሰው ላይ ፍርድ እየመጣ ነው።

## § 110
## የሠራ አካላቷን ታስራ የነበረች ሴት በሰንበት መፈወሷ
## (ሉቃ 13፥10-21)

ሌላ የሰንበት ክርክር ያጋጥመናል (ከቍ. 49-51 ጋር ያነጻጽሩ)። ኢየሱስ በሰንበት ዕለት ቤተ መቅደስ ውስጥ በማስተማር ላይ ነው። አካላዊ ችግር ያለባትን ሴት አይቶ ችግሯን ለማቃለል ወደ እርሷ ሄደ። ይሁን እንጂ ከዚህ ቀደም እንዳየነው በሰንበት ዕለት መፈወስ በአይሁድ ትውፊት መሠረት የተከለከለ ነው። ስለዚህ ሌላ ክርክር የሚያስነሣ ጉዳይ በመምጣት ላይ ነበር።



**ሉቃ 13፥10-13**

10 ኢየሱስ በሰንበት ቀን በአንድ ምኵራብ
ያስተምር ነበር። 11 በዚያም የድካም መንፈስ ዐሥራ
ስምንት ዓመት ሙሉ አካለ ስንኩል ያደረጋት አንዲት
ሴት ነበረች፤ እርሷም ከመጉበጧ የተነሣ ፈጽሞ ቀና
ማለት አትችልም ነበር።
12 ኢየሱስም ባያት ጊዜ ጠራትና፣ «አንቺ ሴት፤ ከሕመምሽ ነጻ ወጥተሻል» አላት።
13 እጁንም በላይዋ ጫነ፤ እርሷም ወዲያው ቀጥ ብላ ቆመች፤ እግዚአብሔርንም
አመሰገነች።

ኢየሱስ ያን ዕለት ምኵራብ ውስጥ እንዲያስተምር የተጋበዘ ይመስላል። የምኵራብ አለቃ እንደ ኢየሱስ ያለን ታዋቂ ሰው መልእክት ያቀርብ ዘንድ መጠየቁ፣ የተለመደ ተግባር ነበር።

ኢየሱስ በማስተማር ላይ ሳለ አድማጮቹ መካከል አንዲት «አካለ ስንኩል» ሴት ድንገት ተመለከተ።[32] ቃሉ ለአከርካሪ[33] መጉበጥ ሕክምና የሚያገለግል ነው። ሐኪሙ ሉቃስ ይህች ሴት ለዐሥራ ስምንት ዓመት መሠቃየቷን ያመለክታል። ይህ ሁሉ የተለመደ ይመስላል። እንግዳው ነገር ይህ ሕመም የደረሰው በጋኔን አማካይነት መሆኑ ነው። አከርካሪን ማጉበጥ የግል ተግባሩ እንደ ሆነ አድርገን በመቍጠር፣ ይህ «የማጉበጥ» ጋኔን ነው ማለታችን አይደለም። ይህ የጥንቈላ እንጂ የፈውስ ጉዳይ አይደለም ማለታችንም አይደለም። በመግለጥ ላይ ያለነው የአካል ጉዳት ከተፈጥሮአዊ ሰበብ የክፉ

[32] የዚህ ዐረፍተ ነገር የመጀመሪያ ቃል 'ኢዱ' - *idou* «እነሆ» ማለት ነው፤ በNIV (The New International Bible) ሳይተረጐም ቀርቶአል። ዐረፍተ ነገሩ ኢየሱስ በመስበክ ላይ ሳለ ድንገት ይህችን ሴት ያያት መሆኑን የሚያመለክት ይመስላል። ይህች ሴት ከወንዶች ተለይታ ከሌሎች ሴቶች ጋር የተቀመጠች ሳትሆን አትቀርም።

[33] J. Wilkinson, "The Case of the Bent Woman in Luke 13:10-17," *EvQ* 49 (1977): 195-205.

የመናፍስት ሥራ ሊሆን መቻሉን ነው። ለማንኛውም ጥቃቅን ጉዳት አጋንንትን መውቀሳችን አይደለም። ጽሑፉ ግን በጣም ግልጽ ነው። ይህ ችግር የተፈጠረው በክፉ መንፈስ ነው። መናፍስት የሰውን መንፈስ የሚቈጣጠሩ መሆናቸውን የሚያመለክቱ (የከባድ እንቅልፍ መንፈስ ኢሳ 29፥10፣ የአመንዝራት መንፈስ ሆሴ 4፥12:19) አንዳንድ ምሳሌዎች ብሉይ ኪዳን ውስጥም ይገኛሉ። ይህ እውነት ከሆነ፣ ማንኛውም የሕመም መፈወስ፣ በዲያብሎስ ሥራ ላይ (ከሐሥ 10፥38 ጋር ያነጻጽሩ)[34] የእግዚአብሔር መንግሥት የሚያካሂደው የግንባር ጥቃት ነው።

ሉቃ 13፥14-16

[14]የምኵራቡ አለቃ ግን፣ ኢየሱስ በሰንበት ቀን ስለ ፈወሰ ተቈጥቶ ሕዝቡን፣ «ሥራ ሊሠራባቸው የሚገባ ስድስት ቀኖች አሉ፤ ስለዚህ በእነዚያ ቀኖች እየመጣችሁ ተፈወሱ እንጂ በሰንበት ቀን አይደለም» አላቸው።

[15]ጌታም መልሶ እንዲህ አለው፤ «እናንተ ግብዞች፤ ከእናንተ መካከል አንድ ሰው በሬውን ወይም አህያውን በሰንበት ቀን ከማደሪያው ፈትቶ ውሃ ሊያጠጣ ይወስደው የለምን? [16]ታዲያ፣ ይህች ሴት የአብርሃም ልጅ ሆና ሳለች ዐሥራ ስምንት ዓመት ሙሉ በሰይጣን ታስራ ስትኖር፣ ከዚህ እስራት በሰንበት ቀን መፈታት አይገባትምን?»

የምኵራቡ አለቃ ኢየሱስን በቀጥታ ለመናገር ድፍረት (ወኔ) ስለአልነበረው፤ በሕዝቡ ላይ ጮኸ። ሴትዮዋ መጥታ ፈውስ በማግኘቷ የሚወቅሳት ይመስላል። ይህ አለቃ ከመሥመር ወጥቷል። ሴትዮዋ ፈውስን ለማግኘት አልመጣችም። ኢየሱስ የጠራት ከሕዝቡ መካከል ነው። መወቀስ ያለበት ሰው ቢኖር፣ ይህች ምስኪን ሴት ሳትሆን ኢየሱስ ነው። በሁለተኛ ደረጃ የደስታውን በዓል ወደ ጠብ ለወጠው።

[34] J. B. Green, "Jesus and a Daughter of Abraham (Lk 13:10-17): Test Case for a Lucan Perspective of Jesus' Miracles," *CBQ* 51 (1989): 643-654.



ሦስተኛ ከእግዚአብሔር ውድ ልጅ ጤንነትና ነጻነት ይልቅ የተጨነቀው ለጥቃቅን ደንቦች ነው።

የምኵራቡ አለቃ የተቈጣው ዘፀአት 20፥9-10 ውስጥ፣ በሰንበት ቀን ምንም ሥራ እንዳይሠራ የሚያዘው ሕግ በመጣሱ ነው። የፈሪሳውያን ልማድ የአንድን ሰው ሕይወት ለማዳን ከሚደረገው ጥረት ያለፈ በሰንበት ቀን ምንም ሥራ እንዳይሠራ በግልጽ ያመለክታል። በዚህም መሠረት ለምሳሌ አንድ ሰው ከደረጃ ላይ ቢወድቅ በሰንበት ቀን ደሙን ለማቆም ጥረት ለማድረግ ይቻላል፤ ፀሐይ ካልጠለቀች በቀር ግን የተሰበረውን ዐጥንት መጠገን አይቻልም። እንግዲህ የሰው ሕይወት አደጋ ላይ በሚሆንበት ጊዜ የሕጉ ጠባይ ይህን ይመስላል።

ሰንበትን በተመለከተ አንዳንድ አስፈላጊ ማስተካከያ ደንቦች አሉ፡- (ሀ) አትሥራ፤ ዘፀአት 20፥9-10። (ለ) አትረስ ወይም መኸር አትሰብስብ፤ ዘፀአት 34፥21። (ሐ) እሳት አታንድድ፤ ዘፀአት 35፥3፤ ዘኍልቁ 15፥32-36። (መ) ምግብ አታዘጋጅ፤ ዘፀአት 16፥23። (ሠ) ወይን አትጥመቅ፤ ነህምያ 13፥15። (ረ) ሸክም አትሸከም፤ ነህምያ 13፥15። (ሰ) አትገበያይ ወይም አትሸጥ፤ ነህምያ 8፥5። ይሁን እንጂ እነዚህ አሉታዊ ሳይሆን አወንታዊ እንዲሆኑ የታሰቡ ነበሩ። ሰንበት ለሰው ልጅ የቀረበው ስጦታ ሆኖ እንጂ ቅጣት ሆኖ አልነበረም። ዕጥፍ ዓላማ አለው። የመጀመሪያው ሰዎች ያርፉ ዘንድ ዕድል ሰጣቸው። ይህ ደግሞ በተለይ ለሴቶችና ለባሪያዎች መልካም ነበር። ሁለተኛው ሰዎች እንዲያመልኩ ዕድል ሰጣቸው። የእግዚአብሔርን መጋቢያዊ እንክብካቤ በማሰብ ለእርሱ የተለየ ቀን መመደብ ነበረባቸው።[35]

[35] ክርስቲያኖች እንደ መሆናችን መጠን ከሕግ ኪዳን ሥር አይደለንም (ቈላ 2፥14፤ ገላ 5፥2-6፤ ኤፌ 2፥14-16፤ ሮሜ 14፥5-9)። ስለዚህ የድኅነት ዋስትና በማድረግ ሰንበትን የማክበር ግዴታ የለብንም። ዘላቂ የሆነው የሰላም ዕረፍት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሀልዎት ውስጥ ለእኛ የተሰጠ

አሁን ደግሞ ኢየሱስ ከዝቅተኛው ወደ ላቀው አመራ:: ፈሪሳውያን አንድን እንስሳ ለማዳን ጥረት ማድረግ የሚችሉ ከሆነ ኢየሱስ፣ «የአብርሃምን ሴት ልጅ» አዲስ ሰው ለማድረግ ለመሥራት በርግጥ ይችላል:: በአንድ በኩል ኢየሱስ አፕልን ከብርቱካን ጋር በማወዳደር ላይ ነበር:: ፈሪሳውያን የእንስሶቻቸውን ሕይወት ለማዳን የሚያስችላቸውን ነገር ብቻ ነበር የሚያከናውኑት:: በነሱ አስተሳሰብ ኢየሱስ ለዚህች ሴት ያደረገው ነገር ይህን ያህል አጣዳፊ አልነበረም:: እስከሚቀጥለው ቀን ለመቆየት ይችል ነበር:: ስለዚህ በፈሪሳውያን የነገር አካሄድ (ተጠየቅ) መሠረት ኢየሱስ ሕግን ተላልፎአል:: ዋናው ጉዳይ ግን ኢየሱስ ሰው ለቀመረው ተጠይቅና ትውፊት አልገዛም አለ:: ዐላማን የሳተንና ግብዝ ትውፊትን ለማክበር ሲል አንድን ሰው ለመታደግ ያገኘውን ዕድል በዝምታ አያሳልፍም:: ግብዝነት በልብሰ ተክህኖአችን ውስጥ ነፍስ ዘርቶ መንቀሳቀሱ ሲታሰብ ያስገርማል::

ኢየሱስ የሴትዮዋ ሕመም የተፈጠረው ወይም እንዲኖር የተደረገው በሰይጣን መሆኑን ግልጽ አደረገ:: ይኸውም ከአጋንንቶቹ አንዱ ሴትዮዋ በዚህ ዐይነት ሁኔታ ለዐሥራ ስምንት ዓመት እንድትኖር አድርጓታል:: ኢየሱስ እርሷን መፈወሱ ሰይጣን ሥልጣኑን የተገፈፈ መሆኑንና የእግዚአብሔር መንግሥት መምጣቱን ያመለክታል::[36]

ስጦታ ነው (ዕብ 4፥9-11):: ከዚህም በላይ የሰንበት መርሕ አሁንም እኛን ይ… ታል:: በሕይወት ዘመናችን ዘወትራዊ የሆነ ዕረፍት ካላረፍን፣ በመ…ሻ ባንዴ ከእኛ ይወሰድብናል::

[36] በእግዚአብሔር መንግሥት መምጣት ዳግም እውን የምትሆነው እስራኤል ምሳሌ መሆኑን ለማሳየት ሉቃስ ይህን ክፍል በጥንቃቄ ጽፎታል:: ፍሬ አልባ በሆነው የበለስ ዛፍ በተመሰለው የእስራኤል ሃይማኖታዊ ሥርዐት በተነጻጻሪ (ሉቃ 13፥6-9)፣ ይህች ሴት እንደ ሰናፍጭ ቅንጣት በሚስፋፋው የእግዚአብሔር መንግሥት (ሉቃ 13፥18-21)፣ የምትገኘውን እውነተኛዋን እስራኤል ትወክላለች:: ሉቃስ 12፥49-13፥35 ውስጥ የተመለከተውና በጥንቃቄ የተዘጋጀው ነገር፣ ማለት እንደ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት፣ ቤተ መቅደስ፣ አጋንንት፣ ... የተከፋፈለ መልስ ወዘተ ያሉትን የሉቃስን




*ሉቃ 13፥17*

[17]ይህን በተናገረ ጊዜ ተቃዋሚዎቹ ሁሉ አፈሩ፤ ሕዝቡ ሁሉ ግን እርሱ ባደረገው ድንቅ ሥራ ሁሉ ደስ አላቸው::

ተቃዋሚዎቹ ወዲያውኑ መዋረዳቸው ለኢየሱስ ትልቅ ድል ነው:: ኀፍረታቸውን ተሸክመው ገሸሽ አሉ:: አልተነገረንም እንጂ ይህን ችግር ፈጣሪ (ኢየሱስን) ለማስወገድ ጥረታቸውን ከመቼውም ይበልጥ አጠናክረዋል:: ለመጨረሻ ጊዜ በሰንበት ዕለት አንድ ሰው በፈወሰ ጊዜ ያደረጉት ይህን ነበር (ማቴ 12፥14፤ ማር 3፥6፤ ሉቃ 6፥11):: ሕዝቡ ግን እነዚህን «ድንቅ ነገሮች»፣ (ቃል በቃል «ውብ ነገሮች»ን) ወደዋል:: ሴትዮዋ በመፈወስዋ፣ ግብዝነት በመጋለጡና የእግዚአብሔርም መንግሥት በመምጣቱ ሐሤት አደረጉ:: በአጠቃላይ ሲታይ ውብ ቀን ነበር::

*ሉቃ 13፥18-11*
*ከማቴ 13፥31*
*ከማር 4፥31-33*
*ጋር*



[18]ከዚያም ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ «የእግዚአብሔር መንግሥት ምን ትመስላለች? ከምንስ ጋር ላመሳስላት? [19]አንድ ሰው ወስዶ በእርሻው ውስጥ የዘራትን የሰናፍጭ ቅንጣት ትመስላለች፤ አድጋ ዛፍ ሆነች፤ የሰማይ ወፎችም በቅርንጫፎቿ ላይ አረፉ::»

[20]ደግሞም እንዲህ አለ፤ «የእግዚአብሔርን መንግሥት ከምን ጋር ላመሳስላት [21]አንዲት ሴት ወስዳ በሙሉ እስኪቦካ ድረስ በዛ ኪሎ[a] ዱቄት ጋር የደባለቀችውን እርሾ ትመስላለች::»

*[a]21 ግሪክኛው ሦስት መስፈሪያ (22 ሊትር የሚያህል) ይላል::*

ተወዳጅና አይተነኛ ጭብጦች በጉልሕ ያሳያል:: ተጨማሪ ዝርዝርን ለማወቅ ከፈለጉ፣ D. Hamm, "The Freeing of the Bent Woman and the Restoration of Israel: Luke 13:10-17 as Narrative Theology," "Some Exegetical Reflections on Luke 13:10-17" *Biblica* 73 (1992): 84-107 ይመልከቱ::

እዚህ ላይ ኢየሱስ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ሁለት ተመሳሳይ አጉልቶ ማሳያዎችን ሰጠ፡፡ ሁለቱም ትንሹ ነገር ትልቅ ሆኖ ስለማደጉና ታላቅ ለውጥ ስለማምጣቱ ይናራሉ፡፡ የክርስቶስ መንግሥትም እንደዚሁ ነው፡፡ እስከ በረት (ግርግም) ድረስ በመውረድ ዝቅ ያለ ጅማሬ ነበረው፡፡ ዛሬ ግን ከእግዚአብሔር መንግሥት የላቀ ተቋም፣ ኀይልና ሰራዊት የለም፡፡

[ቍ. 18-19 = ማቴ 13÷31-32 እና ማር 4÷30-32፤ በ64ሠ ላይ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ]

**ሰናፍጭ** - ይህ የታወቀ ተክል ሲሆን፣ በጣም ትንሽ ፍሬ አለው፤ ለም መሬት ካገኘ ተክሉ እስከ ዐሥር ጫማ ድረስ (በአማካዩ እስከ አራት ጫማ ድረስ ሊያድግ ይችላል)፡፡ ትናንሽ ወፎች ቅርንጫፎቹ ላይ ያርፋሉ፡፡ ይህ በመሲሓዊው መንግሥት የሚኖረውን ጥበቃ የሚያሳይ ነቢያዊ ሥዕል ሊሆን ይችላል (ሕዝ 17÷23፤ 31÷6:12፤ ዳን 4÷12፤ 14÷21-22)፡፡ ስለዚህ የመንግሥቱ ሁለት ባሕርያት ተብራርተዋል፡፡ እነሱም አስገራሚ የሆነው እድገቱና የጥበቃ ችሮታው ናቸው፡፡

[ቍ. 18-19 = ማቴ 13÷31-32 እና ማር 4÷30-32፤ በ64ሠ ላይ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ]

**እርሾ** - ወንዶች ዘርን ሲዘሩ ሴቶች በበኩላቸው እንጀራ ይጋግራሉ፡፡ የኢየሱስ አጉልቶ ማሳያ ምሳሌዎች የተገኙት ከሠራተኛው መደብ የዕለት ተዕለት ተመክሮዎች ነው፡፡ አድማጮቹ (ተደራሲዎቹ) ስለ ምን እንደሚናገር በትክክል ያውቃሉ፡፡ «በዛ ካለ ዶቄት» የሚለው ለአንድ ሰፊ ቤተ ሰብ ከአንድ ሳምንት በላይ የሚበቃ ሊሁል ማለት ነው፡፡ እርሾ ይህን ያህል ዱቄት የሚያቦካ ከሆነ፣ በዚህ የማትደነቅ ሴት ማን ናት? የእግዚአብሔር መንግሥትም እንደዚሁ



ናት፤ ጸጥ ብላና ቀስ ብላ ትሠራጫለች፤ ትሰፋለች፤ ሁሉን ከፍ ታደርጋለች፡፡ አይሁድ የመሲሑ መንግሥት በክበሮ ድምፅና በአስገራሚ ኀይል ትመጣ ዘንድ ፈለጉ፤ እግዚአብሔር ግን ጸጥ ያለውንና ረቂቅ የሆነውን መስፋፋት መረጠ፡፡

**§ 111**
**የቤተ መቅደስ መታደስ በዓል**
**(ዮሐ 10÷22-39)**

ኢየሱስ ለቤተ መቅደሰ መታደስ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ፡፡ ከሁለት ወር በፊት ለዳስ በዓል እዚሁ ነበር፡፡ በዚሁ መሠረት ስለ መልካሙ እረኛና ስለ በጎቹ በመናገር (ከዮሐ 10÷1-21 ጋር ያነጻጽሩ) ትምህርቱን (ውይይቱን) ካቆመበት ቀጠለ፡፡

**ዮሐ 10÷22-24**

22በኢየሩሳሌምም የቤተ መቅደስ መታደስ
በዓል[ሀ] ሆነ፤ ጊዜውም ክረምት ነበረ፤ 23ኢየሱስም በቤተ
መቅደስ ገቢ፣ በሰሎሞን መመላለሻ ያልፍ ነበር፤
24አይሁድም
ከበቡት፣ «እስከ መቼ ልባችንን አንጠልጥለህ ታቈየናለህ?[37] አንተ ክርስቶስ[ለ] ከሆንህ
በግልጽ ንገረን» አሉት፡፡

*[ሀ]22 «ሀኑካ» ማለት ነው፡፡ [ለ]24 ወይም መሲሑ*

የቤተ መቅደስ መታደስ በዓል የሚውለው በ25ኛው ኬስሌቭ ሲሆን፣ ከፈረንጆቹ ታኅሣሥ ወር ጋር አንድ ነው፡፡ ይህ የቤተ መቅደስ መታደስ በዓል ስምንት ቀን ሙሉ የሚከበር ሲሆን፣ መከበር የጀመረው በ165 ዓ.ቅ.ክ. ነው፡፡ ይኸውም አንጥያኮስ ኢጲፋነስ ቤተ መቅደሱን ባረከሰ በሦስተኛው ዓመት ማለት ነው (ከ1መቃብያን 4÷36-59፤ ከ2መቃብያን 10÷1-8 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡ ሰዎች ሁሉ ከየቦታው

[37] ቃል በቃል፣ «ነፍሳችንን እስከ መቼ ታሣሣለህ» ይህም «አንጠልጥለህ ታቆየናለህ» ወይም «ታጓጓናለህ» ከሚለው ጋር አንድ ነው፡፡

ተጉዘው መጥተው የሚያከብሩት ዕውቅ በዓል ባይሆንም እንኳ በበዓሉ ላይ ብዙ ሕዝብ ይገኝ ነበር:: የበዓሉ መለያ ገጽታ ቤተ መቅደሱና በኢየሩሳሌም ባሉ የግል ቤቶች ልዩ በሆነ ሁኔታ ብርሃን እንዲበራላቸው መደረጉ ነበር:: አንዳንድ ጊዜ «የብርሃን በዓል» ተብሎ የሚጠራው ከዚህ የተነሣ ነው::

ኢየሱስ ከቤተ መቅደሱ ምሥራቅ በሚገኘው የሰሎሞን መመላለሻ ይጓዝ ነበር (ከሐሥ 3፥11፤ 5፥12 ጋር ያነጻጽሩ):: ስፍራው ከቀዝቃዛው ነፋስና ዝናብ ለማስጠለልና ብዙ ሕዝብን በአንድ ላይ ለመሰብሰብ ይመች ነበር:: ኢየሱስ በአይሁድ መሪዎች ተከቧል:: ጥያቄያቸው ተገቢ ቢመስልም፣ እሱን ለማጥመድ የታቀደ ነበር:: ኢየሱስ መሲሕ ነኝ ካለ፣ ይህንኑ በግልጽ እንዲያመለክት ፈለጉ:: ያን ቢያደርግ እግዚአብሔርን ተሳድቦአል ብለው ሊከሱት ይችላሉ (ከማር 14፥60-64 ጋር ያነጻጽሩ)::

**ዮሐ 10፥25-30**

25ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ «እኔ
ነግሬአችሁ ነበር፤ እናንተ ግን አታምኑም፤ በአባቴ ስም
የማደርጋቸው ተምራትም ስለ እኔ ይናገራሉ፤ 26እናንተ
ግን በጎቼ ስላልሆናችሁ አታምኑም፤ 27በጎቼ ድምፄን
ይሰማሉ፤ እኔ ዐውቃቸዋለሁ፤ እነርሱም ይከተሉኛል፤
28እኔ የዘላለም ሕይወት እሰጣቸዋለሁ፤ ከቶ አይጠፉም፤
ከእጄም ሊነጥቃቸው የሚችል ማንም የለም:: 29እነርሱን የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ
ይበልጣል†፤ ከአባቴም እጅ ማንም ሊነጥቃቸው አይችልም:: 30እኔና አብ አንድ
ነን::»

*†29 ብዙ የጥንት ቅጆች አባቴ የሰጠኝ ከሁሉ ይበልጣል ይላሉ::*

ኢየሱስ ቀደም ሲል ማንነቱን ገልጿል:: እንዲያውም የዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የተናገራቸው ያለፉት ሦስት ስብከቶች ዐላማ ይኸው



ነበር (ዮሐ 5፡16-47፤ 6፡32-59፤ 7፡14-30):: ያከናወናቸው ተግባሮችም ያለ ጥርጥር መለኮት መሆኑን ይገልጹ ነበር:: ሆኖም የእነዚህ ልበ ደንዳና መሪዎች ዐይኖቻቸውን ከድነዋል፤ ጆሮዎቻቸውንም ደፍነዋል:: ለዚህ ነው ማንነቱን[38] በግልፅ ያሳውቃቸው ዘንድ የሚጠይቁት:: ሲገልጽላቸው ደግሞ አይሰሙም ወይም አያስተውሉም:: ኢየሱስ መሲሕ ነው፤ ሆኖም ቃሉ በወቅቱ በአይሁድ አእምሮ ላይ ካሳደረው ሐሳብ እጅግ ርቋል:: ስለዚህ ከቃሉ ይልቅ ሥራዎቹ ማንነቱን ይገልጹ ዘንድ መረጠ::

ኢየሱስ በበግ ተምሳሊት መለሰላቸው (በዮሐ 6፥37-40 እና በ76ሀ ላይ ከተሰጠው ማብራሪያ ጋር ያነጻጽሩ):: መልሱ ያኔ ለነበሩት አድማጮች በጥፊ የመምታት ያህል ነበር:: የእግዚአብሔር ሕዝብ እውነተኛ እረኛ እኔ ነኝ ብሎአል:: እነዚህ ሰዎች ሐሰተኛ እረኞች ናቸው:: ከዚያ በከፋ ሁኔታም ሌቦች ናቸው:: ከዚያ የከፋው ጉዳይ ከበጎች ጋር ግንኙነት ይኖራቸው ዘንድ የማይፈቀድላቸው መሆኑ ነው:: ይህ ተምሳሌት በዋናነት ለእነዚህ እምነት የለሽ ካህናት ተግሣጽ ነው:: ለመንጋውም ቢሆን ቃሎቹ የሚያበረታቱ አልነበሩም:: በክርስቶስ ኢየሱስ የዘላለም ዋስትና አለን ምንም ኃይል ከእሱ ፍቅር አይለየንም (ከሮሜ 8፥38-39 ጋር ያነጻጽሩ):: በጎቹ እንደ መሆናችን ድምፁን እየሰማን እንከተለዋለን:: እረኛችል ስለሆነ በግል ያውቀናል፤ ወደ ዘላለም ሕይወትም ይመራናል:: እርሱ ስለሚጠብቀን ከቶ አንጠፋም::[39]

[38] «በግልጽ» (ግክ ፖ'ሬ ስያ - *Parresia*) ተብሎ የተተረጐመው ቃል በድፍረት የሚለውንም ያመለክታል:: ኢየሱስ በግልጽ መሲሕ መሆኑን የማይናገር ከሆነ፣ ፈሪ ነህ መባሉ ኢየሱስን በለዘብታ የሚገልጥ አነጋገር ሳይሆን አይቀርም::

[39] ስለ ቍጥር 29 አዲሱ መደበኛ ትርጉም (አመት) በኅዳግ ላይ ማስታወሻ አለው:: አንዳንድ የጥንት ጽሑፎች፣ «አባቴ የሰጠኝ ከሁሉ ይበልጣል» ይላሉ:: ጥያቄው ግን «ከሁሉ የሚበልጠው ምንድን ነው?» የሚል ነው:: አብ ከሆነ (አመት) በጎቹን ለምን ለመጠበቅ እንደ ቻለ ግልጽ ነው:: መንጋ

የዘላለም ዋስትናን አስመልክቶ የሚከተሉትን አስተውሎቶች እናቀርባለን:-

1. ስለ ዘላለም ዋስትና ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ይህ ግልጽ የሆነ አዋጅ ነው:: የምንባቡ ዋና ሐሳብ አማኙ «ለመውደቅ» የመቻሉ ጉዳይ ሳይሆን «ሊነጠቅ» የመቻሉ ጉዳይ ነው:: አንድ ክርስቲያን በፍጥረተ ዓለም ውስጥ ከክርስቶስ ሊለየው ስለሚችል ማንም ኀይል መፍራት የለበትም (ሮሜ 8÷35-39):: ከዚሁ በማያያዝ አማኞች ወደ አለማመን እንዳይመለሱ የሚያስጠነቅቁትን ምንባቦች ችላ ማለት የለብንም (ማቴ 10÷22፤ 24÷13፤ ዮሐ 15÷1-6፤ ሮሜ 11÷20-22፤ 1ቆሮ 9÷24-27፤ 10÷1-13፤ ገላ 5÷1-4፤ 1ጢሞ 1÷18-19፤ ዕብ 6÷4-8፤ 10÷26-31፤ 2ጴጥ 2÷20-22፤ ይሁ 6)::
2. ይህ በተሟሟቀ ክርክር ውስጥ የቀረበ ተምሳሊት ነው:: ሐቁ ጽሑፉን እንዴት መተርጐም እንዳለብን መወሰን አለበት:: በሌላ አነጋገር ከጽሑፉ ቅንጣት ሐሳብ ውስጥ ተነሥተን የራሳችንን ብዙ ነገር እንዳንዘበዝብ መጠንቀቅ አለብን:: ከዚህ ይልቅ በማወዳደሪያው ዐቢይ (ዐበይት) ሐሳብ (ሐሳቦች) ላይ ማተኰር ይገባናል::
3. እንደ እውነቱ ከሆነ በጎች ሁሉ እረኞቻቸውን ይሰማሉ ማለት አይደለም:: እያንዳንዱ የፓሊስቲና እረኛ አንዲት በግ ባዝና ባዝና እንደ ወጣች መቅረቷ የሚያደርሰውን የልብ ስብራት ያውቃል (ዮሐ 17÷12፤ 18÷19)::

ከሆነ (የጎዳግ ማስታወሻ) ደግሞ ስለ ጥበቃቸው ኢየሱስ ለምን ጽኑ እንደ ሆነ ግልጽ ነው::




4. መዝሙር 95÷7-10 የዚህ ጽሑፍ ጉድኝት የሆነ ሐሳብን ይጣል:: እስራኤላውያን የእግዚአብሔር መንጋ ተብለው ነበር፤ እርሱን ይሰሙ ዘንድ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአቸዋል፤ አለዚያ ወደ ዕረፍቱ እንዳይገቡ ይከለከላሉ::
5. ይህ የተነገረው ለአማንያን ሳይሆን ለኢአማንያን ነው:: ተግባሩም ለማጽናናት ሳይሆን በግ ነጣቂዎችን ለመገሠጽ ነው::
6. በክርስቶስ የመጽናታችን ነገር ሙሉ በሙሉ ወይም በዋናነት በእኛ ጥረት ላይ የተደገፈ አይደለም:: እርሱ እረኛችን ነው:: የራሱን መንጋ ለመንከባከብና ለመጠበቅም ኀላፊነቱን በሚገባ ይወጣል:: ወደ መንጋው እኛን ለማምጣት (ዮሐ 6÷44) መንጋም ውስጥ እስከ ዘለቄታው ሊያኖረን (ዮሐ 10÷27-30) ኀላፊነቱ የእርሱ ነው:: ክርስቶስ እኛን ለመጠበቅ እጅግ ከፍተኛ ችሎታ አለው:: ከዚህም በላይ ይህ ጽሑፍ የእሰጥ አገባ መድረክ እንዳይሆንና አማችን የማጽናና ዐቅሙን እንዳያጣ መጠንቀቅ አለብን::
7. ድምዳሜያችን በአጀማመራችን ላይ ሊደገፍ ይችላል፤ «የዘላለም ዋስትና»ን ጽሑፎች[40] በማንበብ የምንጀምር ከሆነ፣ ድምዳሜያችን ይኸው ሊሆን ይችላል:: በሌላ በኩል

[40] ለምሳሌ፣ መዝ 89÷30-35፤ ዮሐ 4÷14፤ 5÷24፤ 6÷37-40፤ 10÷27-30፤ ሮሜ 8÷29-39፤ 11÷29፤ 14÷4፤ 1ቆሮ 1÷8፤ 2ቆሮ 1÷21-22፤ 5÷4-5፤ ኤፌ 1÷13-14፤ 4÷30፤ ፊል 1÷6፤ 1ተሰ 5÷23-24፤ 2ጢሞ 1÷12፤ 2÷19፤ 4÷18፤ ዕብ 6÷17፤ 7÷25፤ 1ጴጥ 1÷3-5፤ 1ዮሐ 2÷18-19፤ 3÷6፤ 5÷12-13፤ ይሁዳ 24::

ግን «በክሕደት» ጽሑፎች[41] የምንጀምር ከሆነ፣ አንድ ሰው ከኢየሱስ ይለያል ብለን ልንደመድም እንችላለን:: ማስጠንቀቂያ:- የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዓላማ ለቃሉ ለመታዘዝ እንጂ፣ ለአስተምህሮ ጠበቃ ለመሆን አይደለም:: በግራ በቀኝ ባለው ክርክር ውስጥ የሚገኘውን ማንኛውንም ምንባብ ችላ ማለት የለብንም::

ዮሐ 10÷31-39

³¹አይሁድ ሊወግሩት እንደ ገና ድንጋይ አነሡ፤
³²ኢየሱስ ግን፣ «ከአብ የሆኑ ብዙ ታላላቅ ታምራትን
አሳየኋችሁ፤ ታዲያ ከእነዚህ ስለ የትኛው ትወግሩኛ
ላችሁ?» አላቸው::
³³አይሁድም፣ «የምንወግርህ፣ ተራ ሰው ሆነህ ሳለ፣ ራስህን አምላክ
በማድረግ፣ የስድብ ቃል ስለ ተናገርህ ነው እንጂ ከእነዚህ ስለ የትኛውም አይደለም»
ብለው መለሱለት::
³⁴ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤



«በሕጋችሁ፣ 'እናንተ አማልክት ናችሁ አልሁ' ተብሎ
አልተጻፈምን? ³⁵የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን
'አማልክት' ካላቸውና፣ በመጽሐፍም ሊሻር የማይቻል
ከሆነ፣ ³⁶ታዲያ 'የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ' ስላልሁ፣ አብ
ለራሱ ለይቶ ያቀደውንና ወደ ዓለም የላከውን፣ ተሳድበሃል ብላችሁ ለምን
ትወነጅሉኛላችሁ? ³⁷አባቴ የሚያደርገውን ባላደርግ አትመኑኝ፤ ³⁸የማደርገው ከሆነ
ግን እኔን ባታምኑኝ እንኳ አብ በእኔ እንዳለ እኔም በአብ እንዳለሁ ታውቁና
ትስተውሉ ዘንድ ታምራቱን እመኑ::» ³⁹እንደ ገናም ሊይዙት ሞከሩ፤ እርሱ ግን
ከእጃቸው አመለጠ::

ኢየሱስን ለመውገር ጥረት ሲያደርጉ ይህ ሁለተኛ ጊዜያቸው ነው::[42] የመጨረሻው በዳስ በዓል ላይ (ዮሐ 8÷59) ከሦስት ወር በፊት ነበር:: ኢየሱስ በቀጥታ መጥቶ፣ «መሲሑ እኔ ነኝ» ወይም «ያህዌ እኔ ነኝ» አላለም:: ሆኖም አንድምታው ግልጽ በመሆኑ አይሁድ እግዚአብሔርን ተሳድበሃል ብለው ሊወግሩት ተነሡ (ከዮሐ 5÷17-18፤ 8÷58-59፤ 10÷30-33 ጋር ያነጻጽሩ):: ኢየሱስ በእርግጥ የእግዚአብሔር ልጅ ባይሆን ኖሮ ያን ማድረጋቸው ትክክል በሆነ ነበር (ዘሌ 24÷16)::

ሮማውያን የሞት ቅጣት የመፈጸም ሥልጣንን ከአይሁድ ላይ ስላነሡ በሕጉ መሠረት ኢየሱስን ሊገድሉት አይችሉም:: በዚህ ጊዜ በጣም ስለ ተናደዱ የሕጉ ነገር አይታሰባቸውም:: እርሱን ለመግደል ተዘጋጅተዋል::

ቍጥር 32-33 ውስጥ ኢየሱስና አይሁድ ስለ ተለያዩ ሁለት ነገሮች የሚናገሩ ይመስላሉ:: ታምራትን ከምስክርነት ጋር ያነጣጥሩ ነበር:: ኢየሱስ ማንነቱን ለመግለጥ ቍርጥ ሐሳብ ያደረገው በንግግር ሳይሆን በተአምራዊ ሥራዎች ነው:: በንግግር ብቻ አምላክ ነኝ ቢል እንደማይቀበሉት ያውቃል:: ስለዚህ ማንነቱን በሚሠራው ሥራ በጕልሕ አሳየ (በቍ 46 ላይ ሸባው የተፈወሰበትን ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ)::

---

[41] ለምሳሌ፣ ኢያ 24÷19-20፤ ነህ 1÷7-9፤ መዝ 95÷7-10፤ ማቴ 10÷22፤ 13÷1-9:18-23፤ 18÷21-35፤ 24÷13፤ ሉቃ 12÷42-46፤ ዮሐ 15÷1-6፤ ሮሜ 11÷20-22፤ 1ቆሮ 9÷24-27፤ 10÷1-13፤ 15÷1-2፤ ገላ 5÷1-4፤ 6÷7-9፤ ቈላ 1÷19-23፤ 1ጢሞ 1÷18-19፤ 4÷1፤ 2ጢሞ 2÷11-13፤ 4÷10፤ ዕብ 3÷1-19፤ 4÷1-13፤ 6÷4-8፤ 10÷26-31:36-39፤ 12÷15-17፤ 2ጴጥ 2÷20-22፤ ይሁዳ 6፤ ራእ 2÷5:7:10:11:17:26፤ 3÷5-12:21፤ 21÷7::



[42] አዲሱ መደበኛ ትርጉም (አመት) «ድንጋይ አነሡ» ሲል ቃል በቃል፣ «ድንጋይ ተሸከሙ» ማለት ነው:: በሰሎሞን መመላለሻ ስፍራ ድንጋይ ላይኖር ይችላል:: ስለዚህ ይህ ገለጣ በመሠራት ላይ ወዳለው የቤተ መቅደስ አካል ሮጠው እያንዳንዳቸው በእቅፋቸው ሙሉ ድንጋይ ተሸክመው መመለሳቸውን ሳያመለክት አይቀርም::

ኢየሱስ ለክርክሩ እንዲሆነው የእስራኤል ዳኞች የልዑል ልጆች[43] የተባሉበትን መዝሙር 82÷6ን አሳሰባቸው:: እግዚአብሔርን ወክለው የሚመሩ በመሆናቸው በእርሱ ሥልጣን ይደገፉ ነበር::

[43] A. Hanson "John's Citation of Psalm 82 Reconsidered" *NTS* 13 (1964-65): 363-367 በሚለው ጽሑፉ ላይ ለዚህ ምንባብ ሌሎች ፋይዳ ያላቸው ትርጓሜዎች አሉ ይላል (ችግር አልባ የሆኑ የሉም):: አይሁድ እንኳ የመዝሙር 82 ሦስት ልዩ ልዩ ትርጓሜዎች አሏቸው:: በባቢሎናውያን ታልሙድ ትራክታቴ በራኮት *Tractate Berakoth* መሠረት እግዚአብሔር ተናጋሪ ነው፤ የእስራኤል ዳኞችም የእርሱ ተወካዮች እንደ መሆናቸው መጠን «አማልክት» ተብለዋል:: እዚህ ላይ የጽሑፉ አካል የተደረገውና (ገንዘብ የተደረገውና) በS.L. Homcy, "'You Are God's'? Spirituality and a Difficult Teat," *JETS* 33/4 (1989): 485-491 በሚለው ጽሑፍ ላይ ድጋፍ ያተረፈውም አተያይ ይኸው ነው:: (ለ) በቁምራን (11 QMelch) በተገኘው ጽሑፍ መሠረት ተናጋሪው የእግዚአብሔር ተወካይ፣ መልአክም የሆነው መልከ ጼዴቅ ነው፤ አድማጮቹም (ተደራውያኑም) የወደቁት (ክፉዎቹ) መላእክት ናቸው:: ኢየሱስ፣ መልከ ጼዴቅ ነበር በማለት Hanso ይህን አተያይ ገንዘቡ አድርጎታል፤ እንደሚከተለው ያስቀምጠዋል:: ኢ-ርቱዕና መካከለኛ፣ ቅድመ ህላዌም በሆነው ቃል በዚያ ለእነርሱ በተናገረው፣ ሰዎች አማልክት ተብለው መጠራታቸው የሚያስኬድ ከሆነ፣ የሰው ልጅ የሚለውን መጠሪያ፣ ሰው ለሆነው ወይም መካከለኛ ባልሆነና ህልዎቱ በቀጥታ በነበረው፣ ለተቀደሰውና በአብ ለተላከው፣ ቅድመ ህላዌም አምላክ ለነበረውና አሁንም ለሆነው ቃል መጠቀማችን የላቀ ትክክለኛ ያደርገናል (A. Hanson, "John's Citation of Psalm 82" *NTS* 11 [1965]: 158-162]. ሐ. በ Tractate *'Aboda Zarah*" እግዚአብሔር በሲና ተራራ ግርጌ ለእስራኤላውያን እየተናገረ ነበር:: J.H. Neyrey "'I Said: You are Gods': Psalm 82:6 and John 10," *JBL* 108/4 (1989): 647-663 በሚለው ላይ ይህን ሦስተኛውን አተያይ ይደግፋል:: መዝሙር 82 ዳኞችን (ወይም መላእክትን ወይም አንዳንዶች እንደሚሉት መልከ ጼዴቅን አያመለክትም ይላል):: ይልቁን የሚመለክተው በሲና ተራራ ግርጌ እስራኤላውያንን ነው ይላል:: ይህ የተለመደው ማድሻሽካዊ ትርጓሜ ነው:: አይሁድ የሚያነጻቸውን ቶራህ ተቀበሉ:: ስለዚህ ሞት አይነካቸውም (እንደ መጀመሪያው አዳም) የሚል እምነት ነበረ:: በመሆኑም አማልክት ተብለው ተጠሩ (መዝ 82÷6):: ነገር ግን የወርቅ ጥጃ ምስል በማምለክ ኀጢአት በመሥራታቸው ይገደላሉ (መዝ 82÷7):: የምክንያት አካሄዱ (ተጠየቁ) አሁንም ከአነስተኛው ወደ ትልቁ ነው:: እስራኤላውያን በሲና ምድረ በዳ ባገኙት ቅድስና አማልክት ተብለው የሚጠሩ ከሆነ፣ በእግዚአብሔር የተቀደሰው ኢየሱስማ የቱን ያህል ይሆን? ኢየሱስ ተቃዋሚዎቹ ያነሡበትን ክስ የመለሰው ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አንድ (እኩል) በማድረግ ነው:: «እኔ ራሴን ከእግዚብሔር ጋር እኩል አላደረኩም፤ እግዚአብሔር እኔን በመቀደስ እኩል አደረገኝ» አለ::



በእግዚአብሔር ሥልጣን በመደገፋቸው «ልዑል» የሚለው የእግዚአብሔር ማዕረግ ተሰጣቸው:: ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ሥልጣን የተቀበልኩ ተራ ዳኛ ነኝ፤ ወይም የእግዚአብሔር ረዳት ነኝ አላለም:: ይህን ከቶ አላለም፤ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ማለት፣ «የእግዚአብሔርን ባሕርይ፣ ስፍራና ሥልጣን እጋራለሁ» ማለት ነው:: በአጭሩ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ነኝ ማለቱ ነው::

እንደገናም የኢየሱስ ክርክር ከአነስተኛው ወደ ላቀው ነው:: የዚህ ዓለም ገዦች አማልክት በመባላቸው ሳይጮኹ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ነኝ በማለቱ ለምን ይቃወማሉ (ከዮሐ 5÷18፤ 10፥33፤ 19÷7:12 ጋር ያነጻጽሩ)? እንዲያውም ይህንኑ አባባሉን ኀጢአት አልባ በሆነ ሕይወቱና በታምራዊ ሥራዎቹ በማረጋገጥ ላይ ነው:: እነዚህ ምድራዊ ገዦች ከእግዚአብሔር የተቀበሉት ቃልን ብቻ ነው:: ያገኙት ነገር እግዚአብሔርን መስማት ብቻ ነበር:: ኢየሱስ ግን እግዚብርሔርን በርግጥ አይቶታል (ዮሐ 1÷8):: ለአገልገሎት የተለየው (የተቀደሰው) በእግዚአብሔር ነው፤ ከሰማይ ወደ ምድር ተልኳል፤ የእግዚአብሔርን ሥራና ታምራትንም ይሠራል:: ስለዚህ በማንኛውም ረገድ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ነኝ የማለት መብት አለው:: ክርክሩ ምክንያታዊ ነው:: የሚያሳዝነው ክርክሩ የቀረበው ሚዛነቢስ ለሆኑ አድማጮች (ተደራስያን) መሆኑ ነው:: ሊይዙት ሞከሩ፤ ነገር ግን ከእጃቸው አመለጠ:: ያመለጣቸውም ዘዴኛ በመሆኑ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር ጥበቃ ስላነበረው ነው:: ጊዜው ገና አልደረሰም ነበር (ከዮሐ 7÷6:30፤ 8፥20፤ 13÷1፤ 19፥28 ጋር ያነጻጽሩ)::

ቍ 35 ውስጥ ቀጥሎ ያለውን ማብራሪያ ሰጠ፤ «መጽሐፍም ሊሻር የማይቻል» ነው:: በጽሑፉ ትርጉም ላይ ምንም ዐይነት ለውጥ የማያስከትል አነስተኛ ጭማሪ ነው፤ ይሁን እንጂ ኢየሱስ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ያለው አተያይ ምን እንደ ሆነ ብዙ ይነግረናል::

ቅዱሳት መጻሕፍት እስትንፋስ እግዚአብሔር ሆነው ጉድለት አልባና ሕጸጽ አልባ መሆናቸውንም ያምናል። እንደ ተናገረው በእውነት ከሰማይ የመጣ ከሆነ፣ ሊታወቅ በሚቻልበት ስፍራ ላይ አለ ማለት ነው።



# ምድብ ዘጠኝ
## ኋለኛው የዮርዳኖስ ማዶ አገልግሎት

**§ 112**
**ኢየሱስ ከኢየሩሳሌም ወደ ዮርዳኖስ ማዶ ሄደ**
**(ዮሐ 10፥40-42)**

40ከዚያም ኢየሱስ፣ ቀደም ሲል ያጠምቅበት
ወደ ነበረበት፣ ወደ ዮርዳስ ማዶ ተመለሰ፤ በዚያም
ሰነበተ፣ 41ብዙ ሰዎችም ወደ እርሱ መጡ። እነርሱም፣
«ዮሐንስ አንድም ታምራዊ ምልክት አላደረገም፤ ነገር
ግን ስለዚህ ሰው የተናገረው ሁሉ እውነት ነበረ» አሉ።
42በዚያም ስፍራ ብዙዎች በኢየሱስ አመኑ።

በቤተ መቅደስ መታደስ በዓል ላይ በኢየሩሳሌም ለሁለተኛ ጊዜ በድንጋይ ሊወግሩት ተቃርበው ሳለ (ዮሐ 10፥31-33)፣ ኢየሱስ ገዳዮቹ ከሚሆኑት ሸሽቶ በስተ ምሥራቅ ወደሚገኘው ዮርዳኖስ ማዶ አመለጠ። ይህ ግዛት በሄሮድስ አንቲጳስ ሥር ነበር። ስለዚህ የኢየሩሳሌም መሪዎች ሕጋዊ በሆነ መንገድ ሊይዙት አይችሉም። ከዚህም በላይ የዚህ ግዛት ኗሪዎች ለመጥምቁ ዮሐንስ ዘላቂ ፍቅር ነበራቸው። ይህ ፍቅራቸው ኢየሱስ የቻርነት ታምሩን ካደረገ በኋላ ወደ እርሱ ተላልፎ ነበር። ስለዚህ ኢየሱስ በሕዝቡ መካከል ያለሥጋት ይኖር ነበር።

**§ 113**
**መንግሥተ ሰማይ ስለ መግባት የቀረበ ጥያቄ**
**(ሉቃ 13፥22-30)**

በሉቃ 13፥21 እና 22 መካከል የዮሐንስን 10፥22-42ን ጣልቃ በማስገባት የሉቃስን የሐሳብ ፍሰት ገተነዋል። ይህ ለሁለቱ ስምምነት የሚያግዝ ቢሆንም እንኳ፣ ለሉቃስ ዐውድ ዳግም ትኩረት መስጠት አለብን። የሉቃስን መጽሐፍ ብቻ ማንበቡ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደምትስፋፋ ኢየሱስ በሰጠው ትምህርት ላይ፣ «ወደ መንግሥተ ሰማይ በሚገቡት ብዙ ሰዎች ናቸው? ወይስ ጥቂት?» የሚል ጥያቄ ማስነሣቱ